‹‹ታዝማ›› -
በልብ ቀዶ ሕክምና ፈር ቀዳጁ ማዕከል
ገጽ 10

የሰፌዱ ጦስ
ገጽ 11

የኮንስትራክሽን ኢግዚቢሽኑን
ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ትብብር
ገጽ 18




አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 264 ግንቦት 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአራት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባካሄደው 32ኛ መደበኛ ስብሰባ በአራት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል።የምርጫ ጉዳዮችንና ንብረት ማስመለስን የተመለከቱ ረቂቅ አዋጆችን ተወያይቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስተላልፏል፡፡

ምክር ቤቱ ትናንት ባካሄደው ስብሰባ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንብረት ማስመለስ አዋጅ፣ የነዳጅ ውጤቶች የግብይት ሥርዓት አዋጅ እና በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አድርጎ ስለማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በቀረበ አዋጅ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በፓርኮቹ ከአምስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ተኪ ምርቶች ተመረቱ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት አስር ወራት ከአምስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት መቻላቸውን የቦሌ ለሚ እና የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርኮች አስታወቁ፡፡

የቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ አንዋር ከማል ለኢፕድ እንዳስታወቁት፤ በፓርኩ ባለፉት አስር ወራት አራት ነጥብ 11 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ተኪ ምርቶችን አምርቷል፡፡

ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ተኪ ምርቶች ለማምረት ታቅዶ አራት ነጥብ 11 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ተኪ ምርቶች መመረታቸውን የጠቀሱት አቶ አንዋር፤ ለተገኘው ውጤት ማበረታቻዎች በአግባቡ በመተግበራቸውና የተለያዩ ማሽነሪዎች ገብተው ማምረት በመቻሉ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

አቶ አንዋር አክለውም፤ በፓርኩ ባለፉት አስር ወራት የተለያዩ ምርቶች ወደ ውጭ በመላክ 39 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን ጠቁመዋል፡፡ በፓርኩ ከሚመረቱት

በፓርኮቹ ከአምስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኅብረተሰብ ተወካዮች ከባለድርሻዎች ጋር የከተማዋን አጀንዳ ለማቅረብ ይወያያሉ

- **የባለድርሻዎች የውይይት መድረክ ተጀምሯል**

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ማህበረሰብ ተወካዮች ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የከተማዋን የሀገራዊ አጀንዳ ለማቅረብ እንደሚወያዩ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ገለጹ፡፡ የባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ ትናንት ተጀምሯል፡፡

በውይይት መድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን፤ በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ከአዲስ አበባ 119 ወረዳዎች የተወጣጡ የኅብረተሰብ

የኅብረተሰብ ተወካዮች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# “የሽግግር ፍትሕና ሀገራዊ ምክክር ሰብዓዊ መብቶችን በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ ናቸው”

- ዳንኤል በቀለ(ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ሽግግር ፍትሕና ሀገራዊ ምክክር ሰብዓዊ መብቶችን በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ ናቸው ሲሉ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ዳንኤል በቀለ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡ የሀገራዊ ምክክሩ እና የሽግግር ፍትሕ ሰብዓዊ መብቶችን ከማስፈን አኳያ እስካሁን ያለፈባቸው ሂደቶች ትክክለኛና ሂደቱን የተከተሉ መሆናቸውን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ዶክተር ዳንኤል በቀለ

“የሽግግር ፍትሕና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የመዲናችን የበጎነት ተቋዳሾች

ቃልኪዳን አሳዬ


ወይዘሮ አበባ ካሳሁን


አቶ ገብረመድህን አያሌው


ወይዘሪት መቅደስ ሳህሉ

በመዲናችን ከመሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ባሻገር የመኖሪያ ቤት እጦት የሰፊውን ህዝብ ሕይወት በእጅጉ እየፈተነው ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ችግሩን በመረዳት የመኖሪያ ቤት እጥረትን ለመቅረፍ በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ አስተዳደሩ የተያያዘው አንዱ መንገድ ለአቅመ ደካሞችና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በጎ ፍቃደኛ ባለሀብቶችን በማስተባበር የመኖሪያ ቤት ግንባታና እድሳትን ማከናወን ነው፡፡

የ2016 ዓ.ም ከተማ አቀፍ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትን በልደታ ክፍለ ከተማ ለአቅመ ደካሞችና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች መኖሪያ የሚሆን ባለ ዘጠኝ ወለል ሦስት ህንጻዎችን ግንባታ በማስጀመር አሀዱ ተብሏል፡፡ የእድሉ ተጠቃሚ የሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎችም አሁን ላይ እያሳለፉት ያለው የኑሮ ሁኔታ ፈታኝ እንደሆነና የቤት ግንበታው ተጠናቆ ወደ ዘመናዊ ቤታቸው እስከሚገቡ ድረስ በጉጉት እየተጠባበቁ እንደሚገኙ ይገልጻሉ፡፡

ወይዘሮ አበባ ካሳሁን የሚኖሩት በልደታ ክፍለ ከተማ ነው፡፡ ስምንት ልጆቻቸውን ለብቻቸው በማሳደግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ልጆቻቸው ገና ህጻናት እያሉ ነበር ባለቤታቸው ወደ ጦር ግንባር እንደዘመተ ያልተመለሰው፡፡ ብቻቸውን ልጆቻቸውን ለማሳደግ ሲሉ ብዙ ውጣ ውረዶች እያሳለፉ እንደሆነ በማንሳት ስለጦርነት አስከፊነት ይናገራሉ፡፡

የባሌቤታቸው እንደወጣ መቅረት ቢያማቸውም እንኳን ሀዘናቸውን ዋጥ አድርገው ለስምንት ልጆቻቸው ሲሉ ከህይወት ጋር ግብግቡን ተያይዘውታል፡፡ የቀን ስራ፣ ጽዳት፣ እንጀራ ጋግሮ መሸጥና ሌሎችንም ስራዎችን ሰርተዋል፡፡ ልጆቻቸውን ለማስተዳደር ላይ ታች ብለዋል፡፡

ከብዙ ልፋትና መከራ በኋላ ልጆቻቸው ነብስ አውቀው የተለያዩ ስራዎችን በመስራት የእናታቸውን ሸክም በመጋራት አለንልሽ ማለትን ቢጀምሩም፤ ኑሯቸውን ፈቀቅ ማድርግ አልቻሉም፡፡ ወይዘሮዋ ያሳለፉትን የህይወት ውጣ ወረድ ተከትሎ ድካምና እርጅና ተጫጭኗቸዋል፤ ተመስገን የሚለው ቃል ግን ካፋቸው አይጠፋም፡፡ ወይዘሮ አበባ የእድሉ ተጠቃሚ በመሆናቸው እጅጉን ተደስተው የተሻለ ኑሮ ሊኖሩ በመሆኑ ተስፋቸው መለምለሙን ይገልጻሉ፡፡

"የምኖርበት ቤት ለበርካታ ዓመታት አገልግሎት ከመስጠቱና ከማርጀቱ የተነሳ በአቅራብያው ከሚገኘው ቤት ላይ ተደግፏል" የሚሉት ደግሞ ሌላኛው የእድሉ ተጠቃሚ አቶ ገብረመድህን አያሌው ናቸው፡፡

አቶ ገብረመድህን በልጅነታቸው ከብቶችን በማገድ ወላጆቻቸውን ያግዙ ነበር፡፡ ከእለታት በአንዱ ቀን ድካም ይዟቸው በአንድ ዛፍ ስር ጋደም ባሉበት መብረቅ መታቸው፡፡ አደጋውን ተከትሎ በደረሰባቸው ጉዳት እግራቸው መታዘዝ አቆመ፡፡ በወቅቱ እግራቸውን ለማዳን የተደረገው ጥረት ባለመሳካቱ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ህይወታቸውን ከዊልቸር ጋር ለመግፋት ቢገደዱም ችግሮችን ተቋቁመው ትዳር ይዘው ቤተሰብ መስርተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ከድሬዳዋ ልብስ አምጥተው በመነገድ ቤተሰቦቻቸውን ያስተዳድሩ እንደነበር የሚገልጹት አቶ ገብረመድህን፤ በየአብያተክርስትያኑ በመዞር በዊልቸር ላይ ሆነው ጧፍ በመሸጥ እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንደሚደግፉ ይናገራሉ፡፡

የቤት ባለቤት የሚሆኑበት እድል በማግኘታቸው መደሰታቸውን እና እዝያው ከለመዱበት አከባቢና ጎረቤቶቻቸው ሳይርቁ ዘመናዊ የመኖሪያ ቤት ሊያገኙ በመሆኑ ደስታቸው ወደር የለሽ እንደሆናባቸው ይናገራሉ፡፡ ይህንን በጎ ተግባር ለማከናወን ለተነሳሱት የመንግስት አመራሮችና የመዲናዋ ባለሀብቶችም ምስጋና ያቀርባሉ፡፡

ሌላኛዋ የእድሉ ተጠቃሚ ወይዘሪት መቅደስ ሳህሉ ሲሆኑ የሚኖሩት ከታላቅ እህታቸው ጋር ነው፡፡ የእለት ወጪያቸውን ለመሸፈን ያገኙትን የቀን ስራ በመስራት ህይወትን ለማሸነፍ ቢፍጨረጨሩም፤ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የሚኖሩበት ቤት ምቹ ባለመሆኑ ክረምቱ በመጣ ወቅት ሰቀቀናቸው ይጨምራል፡፡ ቤታቸውም በውሃ ይሞላል፡፡ ያንንም ቀድተው እየደፉ ኑሮዋቸውን ያስቀጥላሉ፡፡

ወይዘሪት መቅደስ ክረምት በመጣ ቁጥር ዓመቱን ጠብቆ የሚመጣው ሰቀቀናቸው ሊጠፋ በመሆኑ ተስፋቸው ለምልሟል፡፡ የቤቱ ግንባታ ተጠናቆ መኖር እስኪጀምሩ ድረስ ጓጉተዋል፡፡ ያገኙትን ስራ ሰርተው ህይወታቸውን ለመቀየር ዝግጁ መሆናቸውንም ይናገራሉ፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2016 ዓ.ም ከተማ አቀፍ የክረምት በጎ ፍቃድ የቤት ግንባታን ባስጀመሩበት ወቅት እንደገለጹት፤ በክረምት የቤት ግንባታ እና እድሳት መርሀ ግብር 3ሺህ 500 ቤቶችን በመገንባት 17 ሺህ 500 አቅመ ደካሞች እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡


ባለፈው የክረምት እና የበጋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 6ሺ 730 ቤቶች ተገንብተው ለአቅመ ደካሞችና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች መተላለፋቸውን የሚናገሩት ከንቲባ አዳነች፤ ቤቶችን ማደስ የነዋሪዎችን የኑሮ ጫና ማቅለል ብቻ ሳይሆን ዜጎች የተሟላ መጸዳጃ፣ ማብሰያና ሌሎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በተሟሉላቸው ቤቶች ክብራቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ ማድረግ ነው ይላሉ፡፡

የተወሰኑ የቀበሌ ቤቶችን አንስቶ ዘመናዊ ህንጻ በመገንባት በርካታ የከተማይቱ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ተግባር በመዲናይቱ ያለውን መሬት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያግዝ መሆኑንም ከንቲባ አዳነች ይጠቁማሉ፡፡

በበጎ ፍቃድ አገልግሎት የነዋሪዎችን የኑሮ ሁኔታ የማሻሻል ተግባር በልበ ቀና ባለሀብቶች ድጋፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ሌሎችም ይህንን በጎ ተግባር በመቀላቀል ለከተማቸው መዘመን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉም ከንቲባ አዳነች ጥሪ አቅርበዋል።

# የብሔር-ተኝነት መጽሐፍ ለአሁናዊም ሆነ ለወደፊቱ የሀገሪቱ ሁኔታ ጠቃሚ ሰነድ ነው

ቃልኪዳን አሳዬ




አዲስ አበባ፡- በመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር ዴኤታ ብርሃኑ ሌንጂሶ (ዶ/ር) የተጻፈው "ብሔር-ተኝነት" መጽሐፍ ለአሁናዊም ሆነ ለወደፊቱ የሀገራችን ሁኔታ ጠቃሚ ሰነድ ነው ሲሉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አገኘሁ ተሻገር በመጽሐፉ የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ እንደተናገሩት፤ ብሔርተኝነትን ለጋራ ኃይልና ለበጎ ዓላማ ማዋል ከተቻለ ለሀገር እድገት፣ ሰላምና ብልጽግና ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡

መጽሐፉ ብሔርተኝነት በዓለም አቀፍ ሁኔታ ያለው አተያይ ምን እንደሚመስል እንደሚያሳይ ያነሱት አፈጉባኤው፤ ለምርምርና ሌሎች መጽሐፍትን ለመጻፍ ለሚፈልጉ ደራሲያን ግብዓት ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል።

አያይዘውም፤ ኢትዮጵያ አንድነቷ የተረጋገጠና የተጠበቀ ሰላማዊና የበለጸገች እንድትሆን በሕዝቦቿ መካከል የትስስር፣ የትብብርና የአብሮነት ስሜት መጎልበት የግድ ነው፡፡ ብሔርተኝነት በነጠላ ትርክት ሲመራ ከፋፋይ ሆኖ ትስስርን፣ ትብብርንና አብሮነትን ያዳክማልም ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አገኘሁ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ ብሔርተኝነት በጭፍን አመለካከቶች የተወጠረ ነው፡፡ በአንድ በኩል ጉዳዩን በጭፍን ጥላቻና ፍራቻ የማየት አዝማሚያ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሁሉም ነገር መፍትሔ አድርጎ የማየት ዝንባሌዎች ይታያሉ።

በኢትዮጵያ በርካታ የራሳቸው የሆኑ ልዩ ጥበብና መገለጫዎች ያሏቸው ብሔር ብሔረሰቦች መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ አገኘሁ፤ አያሌ የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄዎች የተመለሱት በለውጡ ማግስት እንደሆነ ተናግረዋል።

የፍጹም አንድነት አቀንቃኝ ብሔርተኞች የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት አደጋ አድርጎ የማየት አዝማሚያ እንደሚያሳዩ የገለጹት አፈጉባኤው፤ በሌላ በኩል በብሔር ልዩነት አቀንቃኞች ዘንድ ደግሞ የኢትዮጵያ አንድነትን የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ደፍጣጭ አድርጎ የመመልከት አስተሳሰብ አለ ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በብዙ ዋጋና መስዋዕትነት የቆመች ሀገር መሆኗን ለማወቅ ነጋሪ እንደማያሻ ጠቁመው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመጨፍለቅ ለውጥ የማይመጣ በመሆኑ በመቀራረብ መሥራት ያስፈልጋል ነው ያሉት።

የብሔር-ተኝነት መጽሐፍ ደራሲና የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር ዴኤታ ብርሃኑ ሌንጂሶ (ዶ/ር)፤ ብሔርተኝነት በበጎም ሆነ በመጥፎ ጎኑ ያሳረፈውን ተፅዕኖ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በመንቀሳቀስ ጥልቅ ዳሰሳ፣ ሃሳብ ጫሪና ለውይይት ጋባዥ የሆኑ ምልከታዎችን በመጽሐፉ ውስጥ ማካተታቸውን ገልጸዋል።

ደራሲው አክለውም በመጽሐፉ የብሔርተኝነት አስተሳሰብ ከባድ ተጽእኖ ፈጣሪ ከመሆኑ የተነሳ በርካታ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች ንድፈ ሃሳቡን ወስደው መጠቀማቸውን ጠቅሰው፤ መጽሐፉ በተለዋዋጭ የዓለም ፖለቲካ ውስጥ ብሔር-ተኝነት ቋሚ ርዕዮት ሆኖ ስለመቀጠሉም ያስረዳል ብለዋል።

በተጨማሪም መጽሐፉ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ፅብ አጫሪነትና በሆሎኮስት መነሻነት ስለሚከሰሰው ብሔርተኝነት፤ ቅኝ ገዥዎች ለቅኝ ግዛት፤ ነጻ አውጪዎች ለነጻነት ትግል፣ አምባገነኖች አምባገነናዊ ሥርዓትን ለመገንባት፣ ዴሞክራቶች ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ስለመጠቀማቸው እንደሚያትት ብርሃኑ (ዶ/ር) አብራርተዋል።

መጽሐፉ በአማርኛና አፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች እንደተጻፈና አምስት ዓመታትን እንደፈጀ የገለጹት ጸሐፊው፤ ከመጽሐፉ ሽያጭ በሚገኘው ገቢ በሁሉም ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በወጣቶች ላይ ያተኮሩ ልማቶችን ለማከናወን መታቀዱን አመላክተዋል።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አገኘው ተሻገር፣ የክልል ርዕሳነ መስተዳድር፣ የተለያዩ ተቋማት አመራሮች፣ ደራሲዎች፣ ጋዜጠኞች፣ አትሌቶችና ታዋቂ ግለሰቦችን ጨምሮ ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# ኢትዮጵያ በደን ብቻ ባከማቸችው ካርበን የዓለምን የአየር ብክለት 30 በመቶ ቀንሳለች

## - በመጪዎቹ ሦስት ዓመታት ከ18 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በደን ብቻ ባከማቸችው ሁለት ነጥብ ስምንት ቢለዮን ቶን ካርበን የዓለም አየር ብክለት 30 በመቶ መቀነሷን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ፡፡ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ከ18 ቢሊዮን በላይ ችግኞች እንደሚተከሉ ተመላክቷል፡፡

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ደን ልማትና የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የዘንድሮውን የዓለም አካባቢ ቀን አከባበርን አስመልክተው ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ደን ልማት ዋና ዳይሬክተር አቶ ከበደ ይማም እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በደን መሬቷ ብቻ ሁለት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ቶን ካርቦን አከማችታለች፡፡

ኢትዮጵያ በደን መሬቷ ብቻ ያከማቸቻቸው ካርበን ዓለምን እየበከለ ካለው 35 ቢሊዮን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ውስጥ 30 በመቶ መቀነስ መቻሏን አስታውቀዋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለአካባቢ መልሶ ማገገምና የአየር ብክለትን ለመከላከል ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ በዚህም በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በስምንት ዓመታት 50 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል አቅዳ እየሠራች ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ባለፉት አምስት ዓመታት በተሠራው የአረንጓዴ አሻራ ሥራ ከ32 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል፡፡ በቀሪዎቹ ሦስት ዓመታት ከ18 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል እየተሠራ ሲሆን፤ ይህም ከኢትዮጵያ አልፎ ለአካባቢው ሀገራት አካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ሁሉንም አካባቢ ተደራሽ የሚያደርግ፣ የመሬት መራቆትን የሚገታ፣ በእውቀትና በፖሊሲ የሚመራ መሆን እንዳለበትም ጨምረው ገልጸዋል።

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ለሊሴ ነሜ (ኢ/ር) በበኩላቸው፤ የዓለም አካባቢ ቀን በሀገር አቀፍ ደረጃ የመሬት ማገገም በርሀማነትን እና "ድርቅን መቋቋም" በሚል መሪ ቃል ግንቦት 27ና 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተለያዩ መርሀ-ግብሮች እንደሚከበር አስታውቀዋል፡፡

የዓለም አካባቢ ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ51ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ31ኛ ጊዜ የሚከበር መሆኑን ገልጸው፤ ቀኑ የሚከበረው ንጹህና አረንጓዴ አካባቢ ለሰው ልጆች ያለውን ተቀሜታ ለማስገንዘብ መሆኑን አስታውቀዋል።

የዓለም አካባቢ ቀን የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ፣ በጽዳት ዘመቻ፣ ግንዛቤ በማስጨበጥ እና በተለያዩ ዝግጅቶች በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ይከበራል ብለዋል።

የአካባቢ ጥበቃ ሥራ የአንድ ተቋም ሥራ ብቻ አለመሆኑን ገልጸው፤ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የአካባቢ፣ የውሃ፣ የአፈርና የፕላስቲክ ብክለትን ለመከላከል በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ድዳ ድሪባ በበኩላቸው፤ ብክለትን መከላከል የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ሲሆን፤ በአረንጓዴ አሻራ ብቻ በከተማዋ ያለውን የደን ሽፋን ከሁለት ነጥብ ስምንት በመቶ ወደ 15 በመቶ ማሳደግ መቻሉን አስታውቀዋል፡፡



አርክቴክት ዮሐንስ መኮንን

# የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያን ስር የሰደዱ ችግሮች በመለየት ለምክክር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያን ስር የሰደዱ ችግሮች በመለየት ለምክክር ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተናገሩ፡፡

የኢዜማ ምክትል መሪ አርክቴክት ዮሐንስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሀገሪቱን ስር የሰደዱ ችግሮች በጥናት በመለየት ለምክክር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን የሚያመጣ እና ያሉትን የህልውና አደጋዎች መቀልበስ የሚያስችሉ ጉዳዮችን ለይተው ማውጣት አለባቸው ያሉት አርክቴክት ዮሐንስ፤ጥናት የተደረገበት የተደራጀ ሃሳብ ይዘው በመምጣት ሃሳባቸውን ለውይይት ማቅረብ እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

አርክቴክት ዮሐንስ የሌሎችን ሃሳብ ለማድመጥም ፓርቲዎቹ ዝግጁ መሆን አለባቸው ብለዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ የሀገሪቱን ዋና ዋና አንኳር ችግሮችን በመለየት ለመፍታት እድል እንደሚሰጥ ጠቁመው፤ አንኳር የሚባሉት መሠረታዊ ችግሮች ከተፈቱ ቀሪዎቹ በጊዜ ሂደት እንደሚፈቱ ተናግረዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ በታሪክ አጋጣሚ የተገኘ ትልቅ እድል መሆኑን የተናገሩት አርክቴክት ዮሐንስ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የተገኘው ትልቅ እድል እንዳይመክን በጥንቃቄ በመጠቀም ለሀገርና ለትውልድ የሚተርፍ ትልቅ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

እንደ አርክቴክት ዮሐንስ ገለጻ፤ በምክክሩ ልዩነቶችን የማጥበብ እድል አለ፡፡ ኢትዮጵያ የተሻለች ሀገር እንድትሆን እኛ ያላየነውን ሌሎች ያዩት እንዲሁም ሌሎች ያሰቡት ካለ በሰጥቶ መቀበል መርህ ለመወያየት ምክክሩ ትልቅ እድል ይፈጥራል፡፡

ፓርቲዎች ኮሚሽኑ ገለልተኛ ሆኖ እንዲቆም ግፊት ማድረግ አለባቸው ያሉት አርክቴክት ዮሐንስ፤ ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ችግሮች ቢኖሩም በጋራ እያረሙ ከኮሚሽኑ ጋር አብረው መሥራት አለባቸው ብለዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል ራሄል ባፌ(ዶ/ር) በበኩላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ግጭት እየወሰዱ ያሉ ከፍ ያሉ ሀገራዊ ጉዳዮችን እና የፖሊሲ ለውጥ የሚፈልጉ ጉዳዮችን በአግባቡ በመለየት ለምክክር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በሀገራዊ ምክክሩ ላይ የመልካም አስተዳደር ፣የፍትህ፣የኢኮኖሚ እና መሰል ችግሮች ሊነሱ እንደሚችሉ ጠቁመው፤ ሲሸጋገሩ የመጡ ችግሮችንም እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ማየት እንደሚያስፈልግ አመላከተዋል፡፡

በሀገራዊ ምክክሩ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደ ዜጋ መሳተፍ እንደሚኖርበት ገልጸው፤ በሚደረገው ውይይት መቀጠል ያለበትን መልካም ነገር በማበልጸግ አላስፈላጊ ነገሮችን ፈትቶ መሄድ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

# በመዲናዋ ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑ ተቋማት ከትምባሆ ጭስ ነፃ ሆነዋል

**አመለወርቅ ከበደ**



ወይዘሮ ሙሉእመቤት ታደሰ




አቶ ስዩም ወልዴ

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የሚገኙ ከ70 በመቶ በላይ ተቋማት ከትምባሆ ጭስ ነፃ መሆን ችለዋል ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ለ32ኛ ጊዜ የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የፀረ-ትምባሆ ማጨስ ቀንና በመዲናዋ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች እየተካሄደ ያለውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄ አስመልክቶ ባለስልጣኑ ትናንት መግለጫ ሰጥቷል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሙሉእመቤት ታደሰ እንደገለጹት፤ ተቋሙ ከትምባሆ ነፃ አካባቢን ለመፍጠር በተለያየ መልኩ በከተማዋ የንቅናቄና የቁጥጥር ሥራዎች ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በመዲናዋ የሚገኙ ተቋማት ከትምባሆ ነጻ የሆነ አካባቢ ከመፍጠር አኳያ ለሕግ ተገዥነታቸው ከ40 በመቶ በታች የነበረ ሲሆን፤ አሁን ወደ 70 በመቶ ማደግ ችሏል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዋና ሥራ አስኪያጇ እንደተናገሩት፤ ባለስልጣኑ በመዲናዋ ከትምባሆ የጸዳ አካባቢን ለመፍጠር የፊት ለፊት የውይይት መድረኮች ከተለያዩ አካላት እስከ ብሎክ አደረጃጀት በማድረግ፤ በርካታ የአደባባይ ግንዛቤ ፈጠራዎችንና የፓናል ውይይቶችን በማድረግ የንቅናቄ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡

ከንቅናቄው ባለፈ በቀንና በማታ ፕሮግራሞች በትምህርት ቤቶች፣ በወጣት ማዕከላት፣በምግብ ቤቶች፣ በመዝናኛ ቦታዎችና በተለያዩ ተቋማት የቁጥጥር ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል፡፡

እስካሁን በተሠሩ ሥራዎች ትምህርት ቤቶች ሀገር ተረካቢ እንደመሆናቸው የትምባሆ ጎጂነትን በተመለከተ የነበራቸው ግንዛቤ እያደገ መሆኑን ጠቁመው፤ የተለያዩ ድርጅቶችን ከትምባሆ ጭስ ነፃ ለማድረግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አበረታች ናቸው ብለዋል፡፡

የትምባሆ ምርቶች በዜጎች በተለይም በሕፃናት ላይ እያደረሱ ያለው ተጽዕኖ በተመለከተ በመዲናዋ ሰፊ ጥናት አለመሠራቱን ወይዘሮ ሙሉ እመቤት አንስተው፤ የከተማዎች መስፋፋት፣ የቁጥጥር ሥራው በቀንና በማታ ወጥ አለመሆን በአፈጻጸም ሂደቱ እንደተግዳሮት የሚነሳ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

ባለስልጣኑ ዓለም አቀፍ የፀረ ትምባሆ ቀንን አስመልክቶ በከተማዋ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የንቅናቄ ሥራዎችን እየሠራ በመሆኑ የተለያዩ አካላት መሥሪያ ቤቱ ከትምባሆ ነጻ የሆነ ትውልድ ለመፍጠር የሚያደርገውን ተግባር በመደገፍ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን የመድኃኒት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ስዩም ወልዴ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በትምባሆ ምክንያት በዓለም በየዓመቱ ስምንት ሚሊዮን ሰዎች ሕይወታቸው ያልፋል፡፡

በትምባሆ ውስጥ ወደ ሰባት ሺህ የሚጠጉ ኬሚካሎች መኖራቸውን አመላክተው፤ ከነዚህ ኬሚካሎች 70 የሚሆኑት በቀጥታ ካንሰርን እንደሚያመጡ አስረድተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ችግሩን በመረዳት በትምባሆ ምርት ላይ ቁጥጥር ማድረግ በኅብረተሰብ ጤና ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የዓለም ጤና ድርጅት ያወጣውን ስምምነት ከፈረሙ ሀገራት አንዷ ነች ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በሀገር ደረጃ ትምባሆን በተመለከተ ጠንካራ መመሪያ ቢኖርም ከትግበራው አኳያ ክፍተቶች እንዳሉ የገለጹት አቶ ስዩም፤ በኢትዮጵያ ከትምባሆ ጋር ተያይዞ ያለውን የጤና ችግር በዝርዝር ለማወቅና ችግሩን ለመቅረፍ እየተከናወነ ያለው ጥናት በቅርቡ ይፋ እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

# የ5 አካባቢ ባህላዊ ምግቦችን በባለ5 ኮከብ ሆቴሎች የምግብ ዝርዝር ለማካተት ጥናት ተካሄደ

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወራት በአምስት የኢትዮጵያ አካባቢዎች በሚዘወተሩ ባህላዊ ምግቦች በባለኮከብ ሆቴሎች የምግብ ዝርዝር እንዲካተቱ የሚረዳ ሳይንሳዊ ጥናት መደረጉን የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘጠኝ ወራት የስልጤ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ የኮንሶ እና የዳውሮ አካባቢ ባህላዊ ምግቦች ላይ ጥናት ተደርጓል።

በዘንድሮ በጀት ዓመት በኢትዮጵያ ስምንት አካባቢዎች የሚገኙ ባህላዊ ምግቦችን በሳይንሳዊ መንገድ ለማጥናት እቅድ የተያዘ ሲሆን፤ በዘጠኝ ወራት የአምስት አካባቢዎች ባህላዊ ምግቦች ላይ ምርምር መድረጉን አስረድተዋል፡፡

የጥናቱ ዓላማ በዋናነት በቀጣይ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ባህላዊ ምግቦች በሳይንሳዊ መንገድ በማጥናት ወደ ባለአምስት ኮከብ ሆቴሎች ማምጣት ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ባለፈው ዓመት የሲዳማን፣ የጋምቤላን፣ የሐረሪን፣ የአፋርንና የጋሞ ባህላዊ ምግቦች ላይ ጥናት መደረጉን አስታውሰዋል።

አቶ ይታሰብ እንደገለጹት፤ በተሠሩ ጥናቶች መሠረት ባህላዊ ምግቦች ሆኑ ሌሎች ሀገር በቀል እውቀቶች በስልጠና መልክ ለተማሪዎች እንዲተላለፉ ማድረግ ይገባል።



ባህላዊ ምግቦች

ተቋሙ ሀገር በቀል እውቀቶችን በማጥናት ለተማሪዎች ለማሰልጠን፣ ለሥራ እድል ፈጠራና ከትውልድ ወደትውልድ ለማሸጋገር እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

ምክትል ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ የበርካታ የብሔር ብሔረሰቦች መገኛ እንደመሆኗ የአካባቢውን ባህልና አመጋገብ በማጥናት ለማሰልጠኛ ተቋሙ ግብዓት የሚሆኑት እየተለዩ ነው፤ በዚህ አግባብ ባህላዊ ምግቦች ያላቸውን ይዘትና አዘገጃጀት ላይ በቀጣይም ዝርዝር ጥናት ይደረጋል።

በባህላዊ ምግቦች ዝግጅት ስልጠና ያገኙ ተማሪዎች የሥራ እድል ሊፈጥሩበትና አሠራሩን በማዘመን ምርት ሊያሻሽሉ የሚችሉበት ዕድል አላቸው ያሉት አቶ ይታሰብ፤ ከተለያዩ ሆቴሎች ጋር በጉዳዩ ላይ በትብብር ለመሥራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በተጨማሪ ምክትል ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ በቱሪዝም ዘርፍ ያለው የሰው ኃይል አቅርቦትና የግሉ ዘርፍ የሚፈልገው የሰው ኃይል ቁጥር ላይ ያለመጣጣም ችግር አለ።

አንዳንድ የቱሪዝም ዘርፍ ሙያዎች ላይ ባለሙያዎችን ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ጠቁመው፤ በሆቴል ዘርፍ የቤት አያያዝና ጽዳት የሚባል ሙያ አለ፤ ማሰልጠኛ ተቋማት ሰዎችን አሰልጥነው እንዲያቀርቡ ኢንዱስትሪዎች ቢፈልጉም ሰልጣኞች ለሥራው ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ የሰልጣኞች እጥረት መኖሩን አስረድተዋል።

በተቃራኒው አንዳንድ የቱሪዝም ሙያዎች ላይ ተማሪዎች ስልጠናውን ወስደው የኢንዱስትሪዎች የሰው ኃይል ፍላጎት አነስተኛ በመሆኑ በርካታ ኃይል ያለሥራ የሚቀመጥበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ቀጣሪዎች ለሠራተኞች ተመጣጣኝ ክፍያ ከመክፈል ባለፈ የሚያጋጥማቸውን ቤተሰባዊ ጉዳዮች መቆጣጠር እንዳለባቸው ምክትል ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

# በፓርኮቹ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ውስጥ የጋርመንትና የብቅል ምርቶች በዋነኛነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ገልጸው፤ በፓርኩ ውስጥ ከሚገኙት 19 ኩባንያዎች ውስጥ 14ቱ በምርት ላይ ሲሆኑ፤ የተቀሩት በግንባታ ላይ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡

እንደ አቶ አንዋር ገለጻ፤ 70 በመቶ የሀገሪቱን የብቅል ፍላጎት በኢንዱስትሪ ፓርኩ ባለው ብቅል ፋብሪካ በመሸፈኑ ከውጭ የሚገባው ብቅል ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ተችሏል፡፡ ይህም ከ70 ሺህ በላይ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች ምርጥ ዘር በማቅረብ የሥራ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

በፓርኩ ውስጥ አዳዲስ ባለሀብቶች እየገቡ ይገኛሉ ያሉት አቶ አንዋር፤ መሠረተ ልማት ማመቻቸቱና የተለያዩ ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ መደረጉ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

የአዳማ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ሥራ አስኪያጅ አቶ ጉልላት አበበ በበኩላቸው፤ በፓርኩ በተሠራው ሥራ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ተኪ ምርቶች መመረታቸውን ተናግረዋል፡፡

15 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ መገኘቱን ጠቅሰዋል፡፡

አቶ ጉልላት አክለውም፤ በፓርኩ ለ11 ሺህ ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ እስካሁን ለዘጠኝ ሺህ ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በፓርኩ ከሚገኙ 13 ኩባንያዎች ውስጥ ዘጠኙ ወደ ምርት ገብተዋል ያሉት አቶ ጉልላት፤ የፓኪስታን ኢንቨስተሮች በስፌት(ጋርመንት)ና በጨርቃ ጨርቅ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው በመሆኑ በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ኢንቨስት ቢያደርጉ በአጭር ጊዜ ውጤታማ እንደሚሆኑ ጠቁመዋል፡፡

# የኅብረተሰብ ተወካዮች ከባለድርሻዎች ጋር የከተማዋን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተወካዮች ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሰባሰብ የአዲስ አበባ ከተማ የሀገራዊ አጀንዳ ለማቅረብ እንደሚወያዩ አመላክተዋል፡፡

በሀገር እድገትና ሰላም ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰዎች በምክክሩ ያላቸው ድርሻ በኮሚሽኑ ትልቅ ቦታ እንደተሰጠው የገለጹት ፕሮፌሰሩ፤ኮሚሽኑ የማህበረሰብ ተወካዮች ከባለድርሻ አካላቶቹ ጋር በቀጣዮቹ ቀናት መክረው ለአጀንዳ ስብሰባው የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እንደሚጠብቀው ተናግረዋል።

ኮሚሽኑ ሥራዎችን በአራት ትልልቅ ምዕራፎች በመከፋፈል የቅድመ ዝግጅት ፣የዝግጅት፣የምክክርና የትግበራ እና የክትትል ሂደት በማለት ሥራውን መሥራት መጀመሩን አስታውሰው፤ አሁን የቅድመ ዝግጅት እና የዝግጅት ምዕራፎችን በማጠናቀቅ ወደ ምክክር ምዕራፍ መግቢያ መድረሱን ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽኑ ከ44 ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በቅርበት በመሥራት የዩኒቨርሲቲዎቹን ምሁራንና ሎጅስቲክስ መጠቀም መቻሉን ተናግረው፤ በቀጣይነትም አምስት ትልልቅ ተባባሪ አካላትን የፖለቲካ ፓርቲዎች፣የሃይማኖት ተቋማት፣መምህራንን እና እድሮችን በመለየት ወደዚህ ሥራ ማስገባት መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በ10 ክልሎች እና በሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የተሳታፊዎች ልየታና መረጣ ተካሂዶ የአዲስ አበባ የአጀንዳ ስብሰባና የምክክር ምዕራፍ እየተከናወነ መሆኑን የተናገሩት ፕሮፌሰር መስፍን፤ አንድ ሺህ በሚሆኑ ወረዳዎች ኮሚሽኑ ሥራዎችን መሥራቱን ገልጸዋል፡፡

አጀንዳ በአዋጁ መሠረት ከታች ወደ ላይ የሚሰበሰብ መሆኑን ተናግረው፤ አርብቶ አደሩን፣ አርሶ አደሩን፣ ሴቶችን፣ ወንዶችን፣ አካል ጉዳተኛዎችን፣አረጋውያንንና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ባሳተፈ መልኩ እየተካሄደ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የማህበረሰብ የተቋማት መሪዎችን፣ምሁራንን እና ልሂቃንን በማግኘት በጎንዮሽም የአጀንዳ ስብሰባ እየተካሄደ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በመድረኩ የተሳተፉት ባለድርሻ አካላት በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የሚንቀሳቀሱ ሲቪክ ማህበራት ፣ የሃይማኖት ተቋማት ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣የሴቶች ማህበራት ፣ወጣቶች፣ መምህራን፣የቀድሞ ሠራዊት ፣ሠራተኞች፣ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች፣ የአዲስ አበባ ምክር ቤት፣የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስፈጻሚ እንዲሁም የተለያዩ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ናቸው።

## ማስተካከያ

ረቡዕ ግንቦት 21 ቀን 2016 ዓ.ም አዲስ ዘመን ገጽ አራት ላይ "ሕገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው" በሚል ርዕስ በወጣው ዜና ሦስተኛው አንቀጽ ላይ ...የትክክለኛነት ማረጋገጫ ከተሠራላቸው 10 ሺህ 238 የትምህርት ማስረጃዎች መካከል 1 ነጥብ 6 በመቶ ትክክለኛውን መስፈርት ማሟላታቸውን ገልጸዋል የሚለው የማያሟሉ ሆነው ተገኝተዋል በሚል ተስተካክሎ ይነበብ፡፡

**ስተፈጠረው ስህተት አዲስ ዘመን ይቅርታ ይጠይቃል።**

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅን ለማሻሻል በቀረበ አዋጅ ላይ ነው።

ማሻሻያ አዋጁ ከሕጋዊና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማዕቀፍ ውጪ የቆዩ የፖለቲካ ቡድኖች በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ እና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ፍላጎት በሚያሳዩበት ጊዜ መልሶ መመዝገብ እንደሚያስችል መሆኑ ተገልጾ፤ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንብረት ማስመለስ አዋጅ ላይ መሆኑን ተመልክቶ፤ በተለያዩ አዋጆች ውስጥ ተበታትነው ያሉትን የንብረት ማስመለስ እና አስተዳደር ድንጋጌዎች በአንድ ወጥ ሕግ ውስጥ በማካተት ለአፈጻጸም ምቹ የሆነ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት መቅረቡ ተገልጿል።

የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችንና ገንዘቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ፣ ለማገድ፣ ለመውረስ ወይም ለማስተዳደር የሚያስችል ግልጽና ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ያለው ምክር ቤቱ፤ በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየው በወንጀል የተገኘን ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የደህንነት ስጋት ከመሆኑ በተጨማሪ የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልጸኝነት ያለው፣ ጤናማና ቀልጣፋ እንዳይሆን የሚያደርግ መሆኑ ተጠቁሞ፤ ይህን ወንጀል ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው የነዳጅ ውጤቶችን የግብይት ሥርዓት ለመደንገግ በቀረበ አዋጅ ላይ ሲሆን፤ የነዳጅ ውጤቶች ካላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ አንጻር አቅርቦታቸውን፣ ክምችታቸውን፣ ስርጭታቸውን፣ ዋጋቸውን፣ ጥራታቸውን እና ደህንነታቸውን መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑ ተገልጿል።

ከአስመጪ ጀምሮ እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ ያለው ግብይት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ፣ ፍትሐዊ እና ተደራሽ የሆነ የአቅርቦት ሰንሰለትና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበ ሲሆን፤ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

# "የሽግግር ፍትሕና ሀገራዊ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ሽግግር ፍትሕና ሀገራዊ ምክክር ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምን፣ ፍትሕን እንዲሁም ሰብዓዊ መብቶችን በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚቻልባቸው መሣሪያዎች ናቸው፡፡

የሰብዓዊ መብቶችን እውን ማድረግ የሚቻለው ከግጭት አውድ በመውጣት ለምክክር ቅድሚያ በመስጠት ነው ያሉት ዶክተር ዳንኤል፤ለሀገራዊ ምክክሩና ለሽግግር ፍትሕ ውጤታማነት በየቦታው የሚስተዋለው ግጭት በሰላማዊ መንገድ መፍታት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ እና የሽግግር ፍትሕ በተለይ የሰብዓዊ መብትን ከማስፈን ረገድ ታሪካዊ ሁነቶች መሆናቸውን ገልጸው፤ በግጭት እየተሳተፉ የሚገኙ ወገኖች ከድርጊታቸው ታቅበው በሽግግሩ ፍትሕና በሀገራዊ ምክክሩ መሳተፍ መጀመር እንዳለባቸው አስረድተዋል፡፡

የሀገራዊ ምክክሩንና የሽግግር ፍትሕን ሂደቶች በመተማመን፣ በመሳተፍ እንዲሁም በተገቢው መንገድ መምራት ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከሀገራዊ አጀንዳዎች እራስን ማግለል ሂደቶቹ ትርጉም አልባ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ሁሉም ዜጋ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚኖርበት ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዳንኤል ገለጻ፤ሀገራዊ ምክክሩና ሽግግር ፍትሕ እስካሁን የመጡበት መንገድ የቱንም ያህል አስቸጋሪና ፈታኝ ቢሆንም ያሉ ፈተናዎችን ተቋቁመው አሁን ለደረሱበት ምዕራፍ መድረሳቸው ለቀጣይ ለሚጠበቁ ውሳኔዎች ተስፋ ሰጪ ናቸው፡፡አጀንዳዎቹ አሳታፊና ተዓማኒ እንዲሁም ተግባራዊ ለማድረግ በቀጣይ ባሉ ሂደቶችም አስፈላጊውንና ተገቢውን ሂደት መከተል ያስፈልጋል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪካዊ የሰብዓዊ መብት ማስፈን ሀገራዊ ምክክሩና የሽግግር ፍትህን በተገቢው መንገድ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ነው ዶክተር ዳንኤል ያብራሩት፡፡

ዶክተር ዳንኤል፤በእነዚህ ጉዳዮች ሁሉም በንቃት የሚሳተፍ ከሆነ ለኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፈንታ ጥሩ ሊያደርጉ የሚችሉ ጠቋሚ ነገሮች አሉ ብለዋል፡፡

በሚቀጥሉት ምዕራፎችም የተጀመሩ አበረታች ሥራዎች የበለጠ አጠናክሮ በመቀጠል አሳታፊና ተዓማኒ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው ያሉት ዶክተር ዳንኤል፤ሁሉም ኢትዮጵያውያን ወገኖች በእነዚህ ሁለት ትልልቅ ሀገራዊ አጀንዳዎች ውስጥ ያለመታከት የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የተጣሱ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪ አድርገዋል፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# መከላከያ ሰራዊትና የሀገር ባለአደራነት

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

ሉአላዊነት የአንድ ሀገር የክብር፣ የአይነኬ ስም ነው። እኛ መጠሪያ ስም እንዳለን ሁሉ የሀገራት የክብር ልኬት የልኡላዊነት ድንበራቸው ነው። ሁሉም ሀገራት በዚህ ስም በኩል ሀገርና ታሪክ ያቆዩ ናቸው። ይህ የክብር ስም የሀገር ባለአደራ ከሆነው የመከላከያ ሰራዊት ጋር የተስማማ የአንድ ሳንቲም መንታ ገጽታ መሆኑ ደግሞ ሌላው ውበቱ ነው።

ኢትዮጵያ የሚለው የነጻነትና የእኩልነት፣ የፍትህና የሚዛናዊነት ስም በዚህ እውነት በኩል ተንጸባርቆ ብኩርናን ያገኘ ነው። ማናቸው ላለን እነዛ የነጻነት አድባሮች፣ የሰብዐዊነት ውሀ ልኮች፣ በብዙሀነት ለምልመው፣ በታሪክ አሽተው፣ በአብሮነትና በክብር ፊተኝነትን ያገኙት ሀበሾች ናቸው የምንባለው የሀገር መከታ በሆነ የመከላከያ ሰራዊታችን ነው።

አለም ላይ የጀግንነት ስም እያገኙ ከመጡ ጥቂት የሰላም አርበኞች መሀል የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አንዱ ነው። መነሻውን ሀገርና ህዝብ አድርጎ የተለያዩ ግዳጆችን በብቃት በመወጣት የሀገርና ህዝብን ክብር በማስጠበቅ ረገድ የተዋበ ስም ጽፏል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለየ አመራርና ተደራሽነቱ በሰፋ ሀገር ተኮር ፍልስፍና ከነበረበት ልቆ የታየበት ሁኔታ አለ።

ራሱን በእውቀት እና በሀገር ፍቅር ስሜት አርቆ፣ በተለያዩ ስልጠናዎችና በዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ዳብሮ ቁመናውን ከፍ ያደረገ ፤ ከሀገር አልፎ ለሌሎች የአለም ሀገራት ምሳሌ እስከመሆን የደረሰበትን የቅርብ ጊዜ ታሪኩን ማንሳት ይቻላል።ከተለያዩ የአለም ሀገራት ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ፣ ሰላም ተኮር እሳቤዎች ላይ በማተኮር፣ ከጦርነት በፊት ሰላም በሚል መርህ በሰፋና በገዘፈ መረዳት ውስጥ የሀገር ባለውለታነቱን አስመስክሯል።

ሀገራችን ችግር ውስጥ በነበረችባቸው ጊዜያቶች እንዲሁም አሁን ባለንበት ሁኔታ ዋጋ በመክፈል የፊተኝነት ድርሻውን እየተወጣ ይገኛል። ይሄ በሞት የተሰላ የሀገር ፍቅር ውለታ ወታደር ሲሆን ለሀገር የገባውን ቃል በተግባር የማሳየት ታማኝነት ነው። ይሄ ታማኝነት ወደፊትም የሚቀጥል ሀገርና ህዝብ እስካሉ ድረስ በሰራዊቱ ልብ ውስጥ የሚኖር ነው።

ሉአላዊነት የአንድ ሀገር እና ህዝብ የማንነት ቀለም ነው። መከላከያ ሰራዊት የሚለው ስም ደግሞ ይሄ ቀለም እንዳይደበዝዝና ደምቆ እንዲቀጥል የሚያደርግ ባለአደራ ነው። የሀገርን ዳር ድንበርና የህዝቦችን ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ ሚናው የላቀ ነው። ይህ ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚስማሙበት የጋራ እውነታ ነው።

ለሀገር የከፈለውን የአካልና የህይወት መስዋዕትነት በመጣንባቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች መሀል አረጋግጠናል። ይህ በማንም ሳይሆን በመከላከያ ሰራዊት ብቻ የሚከፈል የሉአላዊነት ክፍያ ነው። ሀገርን ነቅቶና በቅቶ በመጠበቅ እኛ ሰላም ወጥተን እንድንገባ ራሱን የሰጠ ባለውለታችን ነው።

ከዳር ድንበር ማስጠበቁ ጎን ለጎን ከሀገር ለሀገር በሆነ መነሻ ሀሳብ ህዝብ እያገለገለ የሚገኝባቸው በርካታ ማህበራዊ ተሳትፎዎችም አሉት። ከአርሶ አደሩ ጋር አብሮ በማረስና በመጎልጎል በምርት ጊዜም ምርት በመሰብሰብ ረገድ ሚናውን አሳይቷል። የአቅመ ደካሞችን ቤት በመስራትና በማደስ በተፈለገበት በየትኛውም ቦታ ላይ በንቃት በመገኘት አስፈላጊነቱን በተግባር በማሳየት ላይ ይገኛል።

በአንድ ሀላፊነት ላይ ብቻ ያረጋ እኔ የህዝብ ነኝ በሚል ስሙ ራሱን ለሀገርና ህዝብ ሰጥቶ እየደከመ ያለ ሁለገብ ባለሙያ ነው።ባለው የአመራርነት ጥበብ፣ የጦር ክህሎት፣ ጀግንነትና የዲሲፕሊን ልህቀት የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በሌሎች ሀገራት በኩል ተመራጭና የአብረን እንስራ ጥያቄ እየቀረበለት ይገኛል። ከጥበብ እና ክህሎት ጋር መከላከያ ሰራዊት መሆን ብዙ ጊዜ የማይቻል ከተቻለም ለአንዳንዶች ብቻ የሚቻል የጥልቅ ስልሳሌ ነጸብራቅ ነው ።

አንድ ሰራዊት ክህሎትን ከዲስፕሊንና ከእውቀት ጋር ካላጣመረ በስተቀር ዘመናዊና የጦር መሳሪያ ስለታጠቀና በሎጀስቲክ ውስጥ ስላለፈ ብቻ ብርቱና አስተማማኝ አይሆንም።የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ደግሞ ብዙዎች ተመኝተው ባጡት የስነልቦና ከፍታ እና የዲሲፕሊን ልህቀት ውስጥ ከእውቀት እና ከስልሳሌ ጋር የታደለ ሆኖ ከፊት የሚቀመጥ ሰራዊት ነው። አሁን ባለው ወታደራዊ አቋም ለየትኛውም ተልዕኮ ብቁ እንደሆነ የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው። በተግባር ተፈትኖም አቅሙን ያስመሰከረ ጀግናና ብልሀተኛ የሚል ስምን ያተረፈ ሰራዊት ነው።

ሰላምን ከማስከበር እና የሀገርን ሉአላዊነት ከማስጠበቅ ባለፈ በተለያዩ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በስፋት በመሳተፍ አለኝታነቱን ያሳየ እና እያሳየ ያለም ሰራዊት ነው። ከሰሞኑ ደግሞ 61ኛውን የአፍሪካ ቀንን በማክበር ግዝፈቱ እስከየት እንደሆነ አሳይቷል። በመከላከያ የውጪ ግንኙነትና ወታደራዊ ትብብር ዋና ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት የተዘጋጀው ይህ ዝግጅት አፍሪካን ያሞካሸ፣ አንድነትን የፈጠረ፣ መጪውን ጊዜ አቃፊነት ባለው ወታደራዊ ስርዐት አብሮ ለመስራት ያስተሳሰረ ነበር።

መነሻውን የአድዋ ሙዚየም ያደረገው የአፍሪካ ቀን አምባሳደር ጀማሊዲን ሙስጠፋን እና አምባሳደር ግሩም አባይን ጨምሮ ተቀማጭነታቸው በአፍሪካና ከአፍሪካ ውጪ የሆኑ የአፍሪካ፣ የእስያ፣ የአውሮፓ ወታደራዊ አመራር አምባሳደሮችን በመጋበዝና በማሳተፍ ስለአፍሪካ የአንድነትና የአብሮነት ትስስር አውግቷል።

በዝግጅቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የመከላከያ የውጪ ግንኙነትና ወታደራዊ ትብብር ዋና ዳይሬክተር ሜጀር ጀነራል ተሾመ ገመቹ ‹የአፍሪካ አንድነት ትብብርና የአፍሪካ በጋራ መቆም ለፓን አፍሪካኒዝም ወሳኝ እንደሆነ እና ወታደራዊ ተቋማትም ትልቅ ድርሻ አላቸው› ሲሉ በንግግራቸው አስተላልፈዋል። ቀጥለውም ‹ነጻና አንድነቷ የተጠናከረ አፍሪካን መፍጠሪያ ጊዜው አሁን ነው› ሲሉ ንግግራቸውን ቋጭተዋል።

‹ኢትዮጵያ በተለያዩ የአፍሪካ ክፍሎች ያሉ ቅኝ ገዢዎችንና የአፓርታይድ አራማጆችን በመዋጋት ንቁ ተሳትፎ እንዳደረገች በማስታወስ፣ አህጉራዊ ተቋማት ግባቸውን እንዲመቱ ያላሰለሰ ሚና እየተጫወተች በመሆኗ ሚናዋን አጠናክራ እንድትቀጥል የአደራ መልዕክት ያስተላለፉት ደግሞ አምባሳደር ጀማሉዲን ሙስጠፋ ናቸው። በኢትዮጵያ የሴራሊዮን ወታደራዊ አታሼ ብርጋዴር ጀነራል አቡበከር ኩንቴ በበኩላቸው ‹የበአሉ መከበር በአፍሪካ ነጻነትና ተግዳሮቶች እልባት የሚሰጥ በመሆኑ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ጋር በጋራ ለመስራት እድል የሚሰጥ ነው› ሲሉ ተናግረዋል።

አቃፊ በሆነ መርህ አፍሪካን በአንድ አላማና ግብ ማስተሳሰር የዝግጅቱ ዋና አላማ ሆኖ የሚነሳ ሲሆን ‹የአፍሪካ ቀን በአፍሪካ ታሪክ ውስጥ ያለው ድርሻ› በሚል ርዕሰ ሀሳብ ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቦ ውይይትና አቅጣጫ ተቀምጦበታል። አፍሪካ ነጻነቷን ካወጀችበት ማግስት ጀምሮ የፈነጠቀው የነጻነት ጮራ አፍሪካ ቀኗን እንድታከብር እድል እንደሰጣት እንዲሁም የዚህ ቀን መከበር በአፍሪካ ታሪክ ውስጥ ስላለው ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያወሳል።

ከጥናታዊ ጽሁፉም ሆነ ከዝግጅቱ ላይ የተወሰዱ አጠቃላይ አበይት ቁም ነገሮች በርካታ ሲሆኑ አፍሪካን በመተማመን፣ በአንድ በጎ አላማ ማስተሳሰር የሚለው ግን የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። ሀሳቡን እውን ለማድረግ ዲፕሎማሲና የጋራ መርህ እንደሚያስፈልግ የተጠቆመ ሲሆን የጋራ ተጠቃሚነት የሚስተዋልበት የአብሮነት ማዕቀፍም ቀጣዩ የቤት ስራ እንደሆነ በመተማመን ተቋጭቷል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በሁሉም መልኩ የነቃና የበቃ እንዲሆን በተለያዩ ስልጠናዎች በኩል እያለፈ ነው። ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳው ዘመኑን የዋጀ የኮማንዶና የአየር ወለድ ስልጠናዎች ናቸው። በወታደራዊና ባህር ሀይል ኮማንዶ፣ በጸረ ሽብር፣ አየር ወለድ፣ እንዲሁም በተለያዩ ስልጠናዎች ብቁ ሙያተኞች እየወጡ እንደሆነ የመከላከያ ኮማንዶና አየር ወለድ ዕዝ አዛዥ ሌተናል ጀነራል ሹማ አብደታ ተናግረዋል።

ቀጠናዊና አለም አቀፍ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ የአሰልጣኞችን አቅም ለማሳደግ ወደተለያዩ ሀገራት ተልከው ልምድ እየቀሰሙ፣ ከተለያዩ ሀገራትም አሰልጣኞችን በማምጣት የልምድ ልውውጥ በማድረግ የሰራዊቱን ቁመና በማሳደግ ላይ እንደሚገኙ አክለዋል።

ሌላው የመከላከያን ስም አጉልተው ካስጠሩ ወቅታዊ ጉዳዮች መሀል የመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አንዱ ነው። ከተጀመረ ሰላሳ አምስት አመት የሆነው ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል በትውልዱ ጥረት ተጠናቆ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት ከሰሞኑ ለምርቃት በቅቷል።

ይሄም ‹ሰው ራዕይ ካለውና ህዝብን ማዕከል አድርጎ ስራዎችን ከጀመረ ጊዜ ይወስድ ይሆናል እንጂ ትውልድ ይጨርሰዋል› በሚል የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ንግግር የተመረቀው ሆስፒታል በቀጣይ ሀገርና ማህበረሰብን በማገዝ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ተጠቁሟል። ለሰራዊቱ ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡም ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ የተናገሩት ደግሞ የጦር ሀይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ብርሀኑ ጁላ ናቸው።

ከረጅም ጊዜ በኋላ ተገንብቶ ስራ የጀመረው ይሄ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ግዙፍና በውስጡም ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎችን ከብቁ ባለሙያዎችና አገልግሎት ጋር የያዘ መሆኑ አሁን ላለው ትውልድ ትሩፋቱ ላቅ ያለ ነው። መከላከያ ሰራዊት በቀጣይም ከሰላምና ከዳር ድንበር ማስጠበቁ ጎን ለጎን እንዲህ ባሉ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ በመሆን በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ሚናውን እንደሚወጣ እናምናለን።

ሀገር መልክ ካላት ወይም ደግሞ በሆነ አንድ ሀገርኛ መልክ እንመስላት ካልን መከላከያ ሰራዊትን ነው የምትመስለው። ከብሄርና ከጎሳ፣ ከማንነትና ከዘረኝነት ጸድቶ ኢትዮጵያዊነትን ብቻ ባለ እውቀትና አስተውሎት ከትላንት ወደዛሬ የመጣ ወደነገም የሚሄድ ፋና ወጊ አለኝታችን ነው። ይህ ስም፣ ይሄ ቀለም በሀገር ፍቅር ዳብሮ በሉአላዊነት የቆነጀ የሁላችን መልክ ነው። ስለሀገር ነፍሱን አስይዞ፣ ጨርቅ ማቄን ሳይል ስለእኛ በዱር በገደል ሲዋደቅ የኖረ የሰላም ዋስትናችን ነው።

እንዲህ ላከበረን አካልና ነፍስ ከልብ ወዲያ ስጦታ የለም። ‹‹እናመሰግናለን›› በምትል ላመል አንደበት ውለታውን ስንዘክር እንኖራለን። አንዳንድ ነፍሶች እንዲህ ናቸው ስለሌላው ኖረው የሚያልፉ። ስለሌላው ክብርና ሰላም ራሳቸውን በመከራ ውስጥ የሚያሳልፉ። የኩራትና የልዕልና፣ የነጻነትና የአይበገሬ ምንጫችን የሆነው መከላከያ ሰራዊት ከህዝብ ለህዝብ በሆነ ሚናው እየተወጣ ላለው ሃላፊነቱ እያመሰገንን በቀጣይም አኩሪና አስተማማኝ እንደሚሆን እምነቴ ነው ።

**ሀገር መልክ ካላት ወይም ደግሞ በሆነ አንድ ሀገርኛ መልክ እንመስላት ካልን መከላከያ ሰራዊትን ነው የምትመስለው። ከብሄርና ከጎሳ፣ ከማንነትና ከዘረኝነት ጸድቶ ኢትዮጵያዊነትን ብቻ ባለ እውቀትና አስተውሎት ከትላንት ወደዛሬ የመጣ ወደነገም የሚሄድ ፋና ወጊ አለኝታችን ነው**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የማዕድን ዘርፉ አዳዲስ ዕድሎችንና ተጨማሪ ሀብት ይዞ እየመጣ ነው››

-አቶ ሚሊዮን ማቲዮስ -የማዕድን ሚኒስቴር ድኤታ

ስምስም መንግሥቱ

ኢትዮጵያ እምቅ የሆነ ያልተካ የምድር ውስጥ በረከት ያላት ሀገር ነች።ይሁን እንጂ ለዘመናት ያህል የተፈጥሮ ፀጋዋን ሳትጠቀምበት ኖራለች።ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን ማዕድን ከግብርና ቀጥሎ የኢትዮጵያን ብልጽግና እንደሚያረጋግጥ ታምኖበት በብዙ ተግዳሮቶችም ውስጥ ቢሆን ውጤት ለማምጣት እየተሰራ ነው።

**የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም የማዕድን ዘርፉ የገጠሙትን ፈተናዎች፣ ፈተናውን ለመሻገር የተሰሩ ሥራዎች፣ ዘርፉ በአሁኑ ወቅት የሚገኝበትን ደረጃ እና ቀጣይ ሥራዎች በተመለከተ ከማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ ጋር ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ።**

**አዲስዘመን፤ የማዕድን ዘርፉ እንደ ሀገር ከተመረጡ አምስት ዋና ዋና ዘርፎች ውስጥ አንዱ መሆኑ ይታወቃል። የዘርፉ አስተዋጽኦ እንዴት ይገለጻል? እስካሁን ዘርፉ እንደሀገር ያመጣውን አበርክቶ ቢያብራሩልን።**

**አቶ ሚሊዮን፤** የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ለረጅም አመታት በአንድ ዘርፍ ላይ ተንጠልጥሎ የቆየ መሆኑ ይታወሳል። አሁን ላይ ግን የብዝሐ ዘርፍ ኢኮኖሚ እንደሚያስፈልግ በመንግሥት በኩል እምነት በመያዙ ካለፉት አራትና አምስት አመታት ጀምሮ የተለያዩ የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ለማልማት ጥረት በመደረግ ላይ ነው።

ከዚህ በፊት ትኩረት ያላገኙ ዘርፎች ትኩረት እንዲያገኙ ተደርጎ ብዝሐ ዘርፍ የኢኮኖሚ ልማትን እየተከተልን እንገኛለን። ከዚህ አንፃር ከአምስቱ ዘርፎች አንዱ የማዕድን ዘርፍ ይጠቀሳል። በሚቀጥሉት አስር አመታትም ኢትዮጵያ ለምታስበው አጠቃላይ የልማትና የብልጽግና ጉዞ ዘርፉ ሀብት በመፍጠርና ለሌሎች የልማት ዘርፎችም ሀብት በማመንጨት እንዲያገለግል ነው የሚጠበቀው።

ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ ሀገር ናት። አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ስኩዌር ካሬ ሜትር የቆዳ ስፋት አላት። እስካሁን ባለው መረጃ በብዙ ሀገሮች አንድ ወይንም ሁለት አይነት የአለት መአድን ነው የሚገኘው። እንደ መታደል ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ሶስቱም አይነቶች ነው ያሏት። ከሳተጎመራ የሚፈጠረው ቮልካኒክ፣ በመሸርሸር ሂደት ደግሞ ከብዙ ሚሊዮን አመታት በኋላ እንደገና ሴዲመንታሪ ወይንም ንብርብር የሚባለው አለት አይነት ይፈጠራል።

ሌላው ደግሞ በሙቀት ግፊት የሚፈጠረው ሞታሞርፊክ የሚባለው አለት ነው። በዚህ መነሻም ኢትዮጵያ ከከበሩ ማዕድናት ጀምሮ ለግንባታ፣ለኤሌክትሪክ ኃይል፣ ለግብርና፣ ለኢንደስትሪ፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች ግብአት ሆነው የሚያገለግሉ ከጋዝ እስከ ጂኦተርማል ድረስ ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ የተለያዩ የማዕድን ሀብቶች ያላት ሀገር ናት። ከዚህ አንጻር ለሀገር ተጨማሪ ሀብት ለመፍጠር የማዕድን ዘርፉ ወደፊት እንዲመጣ መደረጉ ትክክለኛ እይታ ነው።

በሚቀጥሉት አመታትም ብዙ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቃል። ዘርፉ የፍለጋና የልማት ምዕራፎች አሉት። የፍለጋ ምዕራፍ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል። የሚወስደው ጊዜም አስር አመትና ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል። በፍለጋው የሥራ ሂደት የኢኮኖሚ አዋጭነቱ ከተረጋገጠ በኃላ ነው ሥራው ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ የሚሸጋገረው።

በፍለጋው ሥራ ላለፉት አመታት በተከናወኑት ሥራዎች ወደ ልማት ምዕራፍ የተሸጋገሩ አሉ።



ወደልማት ሊቀየሩ የሚችሉ እድሎች እንዳሉም ማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ አንጻር በወርቅ፣ በጂኦተርማል፣ በፖታሽ፣ ጭምር ወደሀብትነት የሚቀየሩ ትልልቅ እድሎች ናቸው በእጃችን የሚገኙት።

የማዕድን ዘርፉ ወደፊት ሲመጣ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ላይ የሚያስከትለው ተግዳሮት ደግሞ አለ። መንግሥት ጠንከር ብሎ ሰላምና ፀጥታን ማስከበር ካልቻለ ዘርፉ ለፀጥታ ስጋት ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይሄን ተቋቁመው ያላቸውን የማዕድን ሀብት ተጠቅመው የለሙ ሀገራት አሉ።

በኢትዮጵያ በኩልም ቢሆን ከሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ጀምሮ የአስፈጻሚ ተቋማትን መዋቅራዊ አቅም በመፈተሽ፤ እስከ ክልል ድረስ ሊደግፍ የሚችል አሰራር ተዘርግቶ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

በአሁኑ ጊዜም በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈትቤት ብሄራዊ የማዕድን ልማት ምክርቤት ተቋቁሞ እየሰራ ይገኛል። ይህ ከፌዴራልና ከክልሎች የተውጣጡ አካላት የተካተቱበት ምክርቤትም በየወሩ በመገናኘት ሥራዎችን ይገመግማል። ከፀጥታ በተያያዘ እና እንደ መብራት፣ መንገድ የቴሌኮም አገልግሎት ያሉ መሠረተልማትን ከማሟላት እንዲሁም የፋይናንስና የማትጊያ ሥርዓትን ምቹ ከማድረግ አንጻር፣ ያሉትን ችግሮች በመፍታት ለልማቱ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያግዝ ምክር ቤት ተቋቁሞ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው።

የዘርፉን ልማት ለማፋጠንም ሆነ ለልማቱ እንቅፋት የሚሆኑትን ለመፍታት የማዕድን ሚኒስቴር ከሚደርገው ጥረት ጎን ለጎን በርካራ አካላትም አጋዥ ሆነው እየሰሩ ነው።ችግሮችን መፍታት የሚቻለው በቅንጅት መስራት ሲቻል በመሆኑ በፌዴራል የሚፈታውን በፌዴራል፤ ክልሎችም የየራሳቸውን ሚና በመውሰድ የበኩላቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ።በመወጣት ድርሻቸውን ይወስዳሉ። ይህም በመሆኑ ጠንከር ያለ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ በመሆኑ በኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፉ አዲስ እድል እና ተጨማሪ ሀብት ይዞ እየመጣ ነው።

በአሁኑ ጊዜም የወርቅ ማዕድን ልማቱን የሚያፋጥኑ የትላልቅ ኩባንያዎች ግንባታም በመከናወን ላይ ይገኛል። ለምሳሌ፤ የፋይናንስ ድጋፍ አግኝተው ወደ ግንባታ ሥራ ከገቡት መካከልም በኦሮሚያ ክልል ወለጋ ቱሉካፔ አካባቢ የተጀመረው ግንባታ ይጠቀሳል። ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ኩሙሩክ የግንባታ ቁሳቁስ እየተጓጓዘ ነው። በኩሙሩክ የሚገነባው በኢትዮጵያ ትልቁ የወርቅ ፋብሪካ ሲሆን፣ በየአመቱም ዘጠኝ ቶን ወርቅ የማምረት አቅም ይኖረዋል። ይህ ፋብሪካ ኢትዮጵያ እስከዛሬ በባህላዊም ሆነ በተለያየ መልክ ስታመርት የነበረውን ወርቅ አንድ ፋብሪካ ብቻውን ያመርታል ማለት ነው።

ይሄ ለኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ ነው። አዲስ ሀብትም ይዞ ነው የመጣው። የወርቅ ፋብሪካውን ግንባታ በአንድ አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ነው የታቀደው። ጋምቤላ ክልል ከሁለት ወር በኋላ ሥራ የሚጀምር ፋብሪካ ግንባታ ተጠናቅቋል። ትግራይ ክልልም ወደ ግንባታ ለመግባት ቅድመ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ነው።

በሌሎች የማዕድን ዘርፎች ላይም እንዲሁ እየተሰራ ነው። በጥቂት ወራት የሚመረቀው ሰሜንሸዋ በለሚ አካባቢ የተገነባው ሲሚንቶ ፋብሪካ ከ30 እስከ 40 በመቶ የሲሚንቶ አቅርቦት ፍላጎትን ለመሸፈን የሚያስችል ነው። በአጠቃላይ እየተከናወነ ያለው ሥራ የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚወስኑ ትላልቅ አቅሞች ናቸው። ለግብርናው ግብአት የሚውል ማዳበሪያም እንዲሁ የማዕድን ዘርፉ አበርክቶ እንዲኖረው እየተሰራ ነው።

በማዕድን ዘርፉ የሚያጓጉ እድሎች ናቸው ያሉት። የማዕድን ፍለጋው ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድና ከፍተኛ ካፒታልም የሚጠይቅ ቢሆንም፤ በፍለጋ ሂደት ሀብቱ ተገኝቶ ወደ ምርት ሊሸጋገሩ ያሉ ትልልቅ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ሊወስኑ የሚችሉ የልማት አውታሮችን ለመገንባት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው።በዚህ ሁኔታ ተጠናክሮ የማዕድን ልማቱ ከቀጠለ ከአስር አመቱ የልማት እቅድ በፊት ቀድሞ ለኢንደስትሪውም ሆነ ለግብርናው ዘርፍ የሚሆን ሀብት ማመንጨት ይቻላል። ይህን ለማሳካትም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈትቤት የተቋቋመው ብሄራዊ የማዕድን ምክርቤት ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው።

በአስር ወራት ከአጠቃላይ የማዕድን ልማት ዘርፍ ወደ አራት መቶ ሃያስምንት ሚሊዮን ዶላር (428ሚሊዮን ዶላር) ገቢ ለማግኘት አቅደን እየተንቀሳቀስን ነው። ከዚህ ውስጥም ወደ 3ሚሊየን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተችሏል።ይህ በመቶኛ ሲሰላ 75 በመቶ ይደርሳል። ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻፀርም ብልጫ ያለው አፈፃፀም ነው የተመዘገበው።

ይሄ ውጤት የተገኘው በአንድ ሚኒስቴር መስሪያቤት ብቻ ሳይሆን፣ ደጋፊ አደረጃጀት በመፈጠሩና ሥራዎችም በየወሩ በመገምገማቸው ጭምር ነው። ስለዚህ ትክክለኛውን መስመር ይዘን ነው እየተጓዝን ያለነው። የበለጠ ውጤታማ ለመሆን የመሠረተልማት አቅርቦት ወሳኝ ነው።በዚህ ረገድም በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የማዕድን ዘርፉ ባለፉት ጥቂት አመታት በህገወጥ አዘዋዋሪዎች፣ በግብይት ችግር ፣ በፀጥታና ተያያዥ ጉዳዮች ፈተና ውስጥ እንደነበር ይታወቃል። ፈተናዎቹን እንዴት መሻገር ተቻለ?**

**አቶ ሚሊዮን፤** በጣም መሠረታዊ ጥያቄ ነው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ባለፉት አመታት በዘርፉ ላይ ያጋጠሙት ተግዳሮቶች በሌሎች አፍሪካ ሀገራትም በተመሳሳይ የሚያጋጥሙ ናቸው። የወርቅ ልማቱ ለዘመናት በባህላዊ መንገድ ነው ሲመረት የቆየው። የአመራረት ሥርዓቱን ለማዘመን ጥረቶች እየተደረጉና የተሻለ ገቢም እየተገኘ ባለበት በዚህ ወቅት ልማቱ ላይ የመሰማራት ፍላጎቱ እየጨመረ መጥቷል። በህገወጥ ድርጊት ውስጥ የታጠቁ ኃይሎች ጭምር ናቸው ሲሳተፉ የነበረው። ህገወጥነት በመስፋፋቱ ይሄን የማስተካከል ሥራ ለመሥራት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። እስካሁን ድረስ በፋብሪካ ደረጃ ወርቅ እያመረተ ያለው ሜድሮክ ኩባንያ ብቻ ነው። ብሄራዊ የማዕድን ምክርቤት ለማቋቋም ምክንያት የሆነውም አንዱ እንዲህ ያለውን የህገወጥ ተግባርን ለመከላከል ነው።

ሌላው ችግሩን ለመሻገር የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ ምን ይመስላል የሚለውን ማየት ነበር። ችግሮቹን ነቅሶ በመለየት ወደ መፍትሄ መግባትም አቅጣጫ ተወስዷል።የማዕድን ዘርፉ በጣም ሩቅ በሆነ አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ ከፍተኛ የፀጥታ ኃይሎችን ማሰማራት ይጠይቃል። የፖለቲካ አመራሩንና ማህበረሰቡን ማሳተፍ የግድ ይላል። ይህን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት በየጊዜው ያልተቆራረጠ ድጋፍ እንደሚያስፈልግና ሥርዓት ውስጥም መግባት እንዳለበት ታሳቢ ተደርጎ ነው እየተሰራ ያለው። በዚህ መልኩ ነው ያጋጠሙትንም ሆነ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመቀልበስ ጥረት ሲያደረገት ቆይቷል። ይህ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

**አዲስ ዘመን፡- ብሄራዊ የማዕድን ምክርቤቱ እስካሁን ባከናወናቸው ተግባራት በተጨባጭ ምን ውጤቶች አስገኘ?**

**አቶሚሊዮን፡-** የክልል ምክትል ፕሬዚዳንቶች የምክርቤቱ አባላት ናቸው። ምክርቤቱ የሚገመግማቸው ሁሉ በክልሎችም አጀንዳ ሆነው ይነሳሉ። በመሆኑም ተመሳሳይ መድረኮችን ፈጥረው ሥራው እስከታች እንዲወርድ በማድረግ ህገወጦችን የመከላከሉንና ሥርዓት የማስያዙን ተልዕኮ ይወጣሉ።

ሥርዓት ማስያዝ ያስፈልጋል የሚል አቋም በመንግሥት ደረጃ ከላይ እስከታች እየተያዘ ሲመጣ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ፤ በየደረጃው ችግሮች እየተስተካከሉ መጥተዋል። ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በአንድ ክልል ላይ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ ይልቅ ምክቤቱ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ አካላትን ያቀፈ በመሆኑ አንድ ላይ መጥተው የሚያስፈጽሙት የተሻለ ይሆናል። እያንዳንዱ የሰራውን ሥራ በተጠያቂነት ነው የሚፈጽመው። በዚህ መልኩ እየተከናወነ ያለው ሥራ ለማዕድን ዘርፉ ትልቅ አቅም መፍጠር ችሏል ።

**አዲስዘመን፡- በአጠቃላይ አሁን ካለው**

**ወደ ገጽ 8 ዞሯል**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የማዕድን ዘርፉ አዳዲስ ዕድሎችንና...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

**ተጨባጭ ሁኔታ ከማዕድን ዘርፉ ምን እንጠብቅ?**

**አቶ ሚሊዮን፤** ቤንሻንጉል፣ ወለጋ፣ ጉጂ፣ ጋምቤላ፣ ትግራይ፣ አማራ ውስጥ በርካታ የማዕድን ሃብቶች አሉ። ትላልቅ የሚባሉ ባለሀብቶችንም ወደ ዘርፉ ለመሳብ እየተሞከረ ነው። አስቸጋሪ የሚባሉ ምዕራፎች አልፈን አስተማማኝ የሆነ ምፍ ላይ ነው የምንገኘው። እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም አምስት ስድስት ፋብሪካዎች ላይ ብቻ ጠንከር ያለ ሥራ መሥራት ከተቻለ፤ ውጤታማ መሆን ይቻላል። ኢትዮጵያ እንደ አፓል ያሉ በዓለም ላይ በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈለጉ የማዕድን ሀብት ያላት ናት። ከዓለም የኢነርጂ ፍላጎት ሽግግር ጋርም ጋር በማስተሳሰር ሥራዎች እየተሰሩ በመሆኑ ውጤቱ ለሀገር የሚበቃ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ በዘርፉ ፍላጎት እያሳዩ ያሉት ኩባንያዎች የትኞቹ ናቸው? በምን ያህል መጠንስ መሳብ ተችሏል? የኩባንያዎቹ ፍላጎት ልማቱ ላይ ወይንስ ፍለጋው ላይ የሚለውንም አክለው ቢገልጹልን?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የካናዳ፣ የአሜሪካን፣ የእንግሊዝ፣ የኖርዌይ፣ አውስትራሊያ፣ ቻይና፣ህንድ፣ በአጠቃላይ ከምዕራብም ከምሥራቅም ትላልቅ የሚባሉ ኩባንያዎች ናቸው በኢትዮጵያ ማዕድን በማልማት ላይ የተሰማሩት። ኩባንያዎቹ ከፍለጋ አልፈው ወደ ግንባታ ምዕራፍ የተሸጋገሩ ናቸው።

የአብዛኞቹ ኩባንያዎች ፍላጎት በፍለጋ የተረጋገጠ ሀብት ላይ መሰማራት ነው። በርካቶቹ እየተሰማሩ ያሉት ከሶስት አመት እስከ 15 አመት የፍለጋ ምዕራፋቸው ተጠናቅቆ የመጨረሻ ደረጃ የደረሱትን የማዕድን ዘርፎች ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በማዕድን ዘርፍ በተግዳሮት ከሚነሱት አንዱ ለአካባቢ ጥበቃና የአካባቢ ማህበረሰብን ተጠቃሚ ከማድረግ ጋር ያለው ክፍተት ነው። በዚህ በኩል ያለውን ሁኔታ ቢገልጹልን?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ልማቱ የአካባቢን ማህበረሰብ ካላቀፈና ተጠቃሚ ካላደረገ ዘላቂነት አይኖረውም። ይሄ በህግም ጭምር የተደነገገ ነው። የማህበረሰብ ልማት ፈንድ አለ። ከአካባቢውም ሮያሊቲ ይሰበሰባል። ለክልል ነው ፈሰስ የሚደረገው። የማዕድን ፍለጋም ሲከናወን የመሬት ግብር ክፍያ ይፈፀማል። ወደ ማልማት ሥራ ሲገባ ደግሞ ከፍተኛ ግብር ነው የሚከፈለው።

በአጠቃላይ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሊደግፉ የሚችሉ ግብር፣ የአካባቢ ማህበረሰብ ፈንድ፣ ሮያሊቲ ክፍያዎች አሉ ማለት ነው። በአካባቢው ላይ የሚሰማራው አልሚ ወይንም ኩባንያ ለማህበረሰቡ ትምህርት፣ ውሃና ሌሎችንም አገልግሎት በማቅረብ ያግዛል። የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ በተገኘ የመቆፈሪያ መሣሪያ የመጠቀም ሁኔታ ይስተዋላል። በባለሙያም የታገዘ ባለመሆኑ ጉዳቱ ያመዝናል። የሚፈለገውን ማዕድን ለማግኘትም አላስፈላጊ የሆነ ኬሚካል የመጠቀም ሁኔታም ይኖራል። ስለዚህም እነዚህ ችግሮች በቀጣይ እየተቀረፉ ይሄዳሉ።

የማህበረሰብ ተጠቃሚነት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በዘርፉ የተሰማሩት ያሉባቸው የክህሎት ማነስ፣ የገበያ ትስስርና ሌሎች ክፍተቶች ተለይተው መፍትሄ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ነው። አነስተኛ ማዕድን አምራቾችን አቅም ለማሳደግና ተጠቃሚነታቸውን ሊጨምር የሚችል ሥራ ለመሥራት ፕሮጀክት ተቀርጿል። በተጨማሪም የጌጣጌጥ ማዕድንን በተመለከተ ስትራተጅክ ዶክመንት ተዘጋጅቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገሪቱ የሚያስፍልጋትን የብረት ግብዓት በሀገር ውስጥ ለመተካት እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ አንጻር የብረት ማዕድን ክምችት ባለባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን ቢገልጹልን?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የብረት ማዕድን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለያየ መልኩ ነው የሚገኘው። ትግራት ክልል ሽሬ፣ አማራ ክልል ሰቆጣ፣ መካነሰላም፣ ወለጋ ቢቅላል፣ ጋምቤላ ጉጂ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የብረት ክምችት አለ።

የብረት ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ ባለሀባቶቹ ባይሰሩ እንኳን በራስ አቅም እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚያስፈልግ እምነት ተይዟል። በሚኒስቴሩ ሥር ያለው የጂኦሎጂ ኢኒስቲትዩት ጉጂ አካባቢ የጥናት ሥራ አከናውኗል። በጥናት በተከናወነው የመለየት ሥራም አካባቢው ላይ ጥራት ያለው የብረት ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። በጋምቤላ ክልልም በተመሳሳይ የብረት ማዕድን ክምችት ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- የማዕድን ፍለጋ ሥራ ጊዜን የሚወስድና ከፍተኛ የገንዘብ አቅምም ይጠይቃል። እንዲህ ያለውን ችግር ለመፍታት ምን አይነት የመፍትሄ እርምጃዎች ናቸው እየተወሰዱ ያሉት?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** በራስ አቅም ለመንቀሳቀስ ፍላጎቱና ጥረቱ አለ። ካለው የቆዳ ስፋትና ከፍተኛ የሀብት ክምችት አንጻር ግን በመንግሥት አቅም ለማከናወን ከፍተኛ መዋዕለነዋይ ይጠይቃል። ሀብቱ ያለበትን ማመላከት ይቻላል። ሆኖም ግን ኢኮኖሚያዊ አዋጭ መሆኑን ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ሰፊ ሥራና የገንዘብ አቅም ያስፈልጋል። በመንግሥት አቅም ለይቶ ማቅረብ ቢቻል ግን የተሻለ እንደሆነ ይታመናል። እስካሁን ግን የኩባንያዎችን ብቃት መሰረት አድርገን ነው ፍለጋው እየተከናወነ ያለው ።

**አዲስ ዘመን፡- የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናት ገበያ ላይ አዋጭ የሚሆኑት እሴት ተጨምሮባቸው ሲቀርቡ እንደሆነ ተደጋግሞ ይነሳል።እሴት በመጨመር በኩል እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ካሉ ቢነግሩን ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** እሴት ጨምሮ ለገበያ ለማቅረብ በተቻለ መጠን ጥረት እየተደረገ ነው። ግን አሁንም ገና ነው። የተጠናከረ ሥራ ያስፈልጋል። ከዩኒቨርስቲዎችና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች እንዲሁም በግላቸው ልምድ ካካበቱት ጋር በቅርበት እየሰራን እንገኛለን። እንዲህ ያለው ሥራ ህግ በማውጣትና ጫና በማሳደር ብቻ ሳይሆን፤ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራም ጎን ለጎን በማስኬድ የሚሰራ ነው። ማህበረሰቡ በቂ ግንዛቤ ሲኖረው የሚፈለገው ውጤት ላይ መድረስ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን ፡- የወርቅ ሃብታችን በበርካታ ተግዳሮቶች ውስጥ መቆቱ የሚታወስ ነው።በአሁኑ ወቅት ያለው ለውጥ ምን ይመስላል?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ባለፉት ጊዜያት በወርቅ ልማቱ ላይ ከፍተኛ ፈተናዎች ነበሩ። ኮንትሮባንድ ከፍተኛው የዘርፉ ፈተና ነው የነበረው። ፍቃድ የሚሰጡት ክልሎች በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ጋር የማስተሳሰር ችግሮች ነበሩባቸው። አንዳንድ አካባቢዎች የባንክ አገልግሎት አለመኖር እንደቅሬታ የሚነሳበት ሁኔታም ነበር።እነዚህን ሁሉ ችግሮች ማስተካከል የግድ ይል ነበር።በዚህ ረገድ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ጉጂ ላይ ተጨማሪ የባንክ ቅርጫፎች እንዲከፈቱ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እስከ አምስት ኪሎግራም ወርቅ ለሚያስገባ አልሚ 60 በመቶ ክፍያ ይፈጽማል። እየፈፀመ ያለው ክፍያ ከዓለም ገበያ ከፍ ያለ ነው። ጉድለቱን መንግሥት ነው እየሸፈነ ያለው። ይህም ሆኖ በሚፈለገው መጠን ወርቅ ወደ ባንክ እየገባ አይደለም። ህገወጥ ግብይቱም አልቆመም። ይሄን ማረም የሚቻለው፤ ቁጥጥሩን በማጠናከር ነው። ሥራም እየተሰራ ነው።ውጤቶች ይመጣሉም ብለን እናስባለን።

**አዲስዘመን፤ የማዕድን ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት መቅረቡ ይታወሳል። አዋጁ አሁን በምን ደረጃ ላይ እንደሆነና አጠቃላይ የአዋጁን ይዘት ቢገልጹልን?**



**አቶ ሚሊዮን፡-** ረቂቅ አዋጁ በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ማስተካከያ እየተደረገበት ይገኛል። በቅርብ እንደሚፀድቅ ይጠበቃል። የአዋጁ አጠቃላይ ይዘት፤ የማዕድን ሀብት በአይነትም በብዛትም በመጨመር የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የማሳደግ ተልዕኮ ያለው ነው። ከዚህ አንጻር አዋጁ ከመንግሥት ምን ይጠበቃል የሚለውን የሚመልስና የተሻለ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች ለመሳብ የሚያስችል ነው።በተጨማሪም የወጭ ንግዱንም የበለጠ ለማሳደግ፣ ተኪ ምርቶችንም በሀገር ውስጥ ለመተካት፣ በአጠቃላይ ስትራቴጂክ የሆኑ ሀብቶችን ለማልማት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል ነው።ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ኢንዱስትሪዎች እንዴት እንደሚመሩ፣ የፍለጋ ፍቃድም እንዴት እንደሚያገኙና ወደ ልማት እንዴት እንደሚሸጋገሩ በግልጽ ያሳያል።

**የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ ለመተካት እየተከናወኑ ባሉት ተግባራት እስከ 60 በመቶ በሀገር ውስጥ መተካት ተችሏል**

**አዲስ ዘመን፡- የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ያለባቸውን የኃይል አቅርቦት ችግር ለመፍታት የድንጋይ ከሰል ልማት ላይ ሥራዎች መጀመራቸው ይታወሳል። ሥራው በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የድንጋይ ከሰልን ሲሚንቶ ፋብሪካዎች በስፋት የሚጠቀሙ ቢሆኑም የብረትና ሌሎች ፋብሪካዎችም ይፈልጉታል። ኢትዮጵያ ከአራት እስከ ስድስት መቶ ሚሊዮን ቶን የሚገመት የድንጋይ ከሰል ሀብት አላት። የጥራት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ አንድ የስትራተጅክ ዶክመንት ተዘጋጅቷል።

የድንጋይ ከሰል ልማትን ከኢንደስትሪዎች ጋር እንዴት ማስተሳሰር እንደሚቻልም የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ ለመቀመር ባለሙያዎች ወደ ህንድ ተልከዋል። የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ ለመተካት እየተከናወኑ ባሉት ተግባራት እስከ 60 በመቶ በሀገር ውስጥ መተካት ተችሏል። የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ማሽን ዳውሮ ላይ ግንባታው ተጠናቅቋል። ቤንሻንጉል ጉሙዝ ላይ ቀድሞ ሥራ የጀመረ አለ። ሌሎችም በሥራ ላይ ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በቆይታችን ያላነሳናቸው ነጥቦች ካሉ እድሉን ወስደው በዚሁ ብናበቃ**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት ፀጋ ያደላት ሀገር ናት። በፍለጋ ምዕራፍ አልፈው ወደ ልማት ምዕራፍ የተሸጋገሩትን በምናይበት ጊዜ ወደተጨባጭ ሀብት መቀየር የሚያስችሉ የልማት ምዕራፎች ላይ ነው የምንገኘው። በነዚህ የልማት ሥራዎች ተጠቃሚው ህብረተሰቡ በመሆኑ ያሉትን እድሎች ተገንዝቦ የበኩሉን ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል። አመራሩም ጠንከር ብሎ መሥራት ይጠበቅበታል በማለት ሃሳን እቋጫለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ባህላዊ መድሃኒትን የማሳደግ ጅምር

አስናቀ ፀጋዬ



የባህላዊ መድሃኒት ሲነሳ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቻይና፣ ህንድ፣ ታይላንድና ጃፓንን የመሳሰሉ ሀገራት በግንባር ቀደምትነት አብረው ይነሳሉ። እነዚህ ሀገራት ባህላዊ መድሃኒትን ለራሳቸው ከማምረት አልፈው ለተቀሩት የአለም ሀገራትም አበርክተዋል። በዚህም የራሳቸውን ኢኮኖሚ ከማሳደግ አልፈው በዘመናዊው ህክምና ከሚታዘዘው መድሃኒት በተጨማሪ ባህላዊ መድሃኒቶችን ለገበያ በማቅረብ ለአለም ህዝብ ጤና የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

እነዚህ ሀገራት በባህላዊ መድሃኒት በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ያተረፉት ባህላዊ መድሃኒቶቻቸውን በሳይንሳዊ መንገድ መርምረው ጥራታቸውን፣ ደህንነታቸውንና ፈዋሽነታቸውን አረጋግጠው ለገበያ በማቅረባቸው ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ መድሃኒታቸውን በአለም አቀፍ ደረጃ በሚገባ ስላስተዋወቁም ዛሬ መድሃኒታቸው በስፋት አለም ላይ ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው።

ኢትዮጵያም ብትሆን ሀገር በቀል የባህላዊ መድኃኒት ቅመማ እውቀት ያለባትና ለመድሃኒትነት የሚሆኑ እፀዋት በስፋት ሚገኙባት ሀገር ናት። ይሁንና በኢትዮጵያ የባህላዊ መድሃኒቶች እውቀት በሳይንሳዊ ምርምር የተደገፈና ልዩ ልዩ የሙከራ ሂደቶችን አልፎ ለገበያ የሚቀርብ አይደለም። የባህላዊ መድሃኒት እውቀቶችም ቢሆኑ ከአዋቂው ውጪ ሌላው አያውቃቸውም። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ከባህላዊ መድሃኒት ዘርፍ እምብዛም ተጠቃሚ አይደለችም።

እንዲያም ሆኖ ግን ባህላዊ መድሃኒት በሳይንሳዊ መንገድ ተረጋግጠው ለገበያ እንዲቀርቡ የሚያስችሉ ስርአቶች በመንግስት በኩል ተዘርግተው እየተሰራባቸው ይገኛል። የባህል መድሃኒት ለህክምና የሚያቀርቡ አካላትም ፍቃድ አግኝተው እንዲሰሩ የማድረግ ጅምር እንቅስቃሴዎች አሉ። የባህል መድሃኒቶች በዘመነ መልኩ ተመርተው ፈዋሽነታቸውና ደህንነታቸው በሚመለከተው አካል ተረጋግጦ ወደገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ ሂደት ግን አሁንም ገና ብዙ ስራዎች እንደሚቀሩ መረጃዎች ያሳያሉ።

ዶክተር ግዛው በቀለ የግሪን ኬር ናቹራል መስራችና ዋና ስራ አስፈፃሚ ናቸው እርሳቸው እንደሚናገሩት ኩባንያቸው ስራውን በኢትዮጵያ ከጀመረ ሰባት አመታትን አስቆጥሯል። በነዚህ አመታትም በርካታ ስራዎችን አከናውኗል። በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ባህላዊ ህክምና እውቀት ወደ ገበያ እንዲወጣና ህብረተሰቡ ከዘመናዊው ህክምና ጎን ለጎን በባህላዊ ህክምናም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። የኢትዮጵያ ባህላዊ ህክምና በበጎ መልኩ የሚታይ ባለመሆኑ ይህ አመለካከት እንዲቀየር ህብረተሰቡን የማስተማርና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎችንም ሰርቷል፤ እየሰራም ይገኛል።

ከዚሁ ስራ ጎን ለጎን ኩባንያው በተለይ ለመከላከያ ሰራዊት አባላት፣ እድሚያቸው እስከ አስራ አራት አመት ለሚደርሱ ህፃናትና ታዳጊዎች እንዲሁም ለአቅመ ደካሞች ነፃ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ማህበራዊ ሀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። የተደበቀው ባህላዊ መድሃኒትና እፀዋት እንዲታወቅ በማድረግ ረገድም ሰፊ ርቀት ተጉዟል። በዚህም በርካታ በባህል ህክምና አገልግሎት ውስጥ ያሉ ሰዎች ተገቢው እውቀት ኖሯቸው ህክምናውን ሳይደብቁ ለህብረተሰቡ እንዲሰጡ አስችሏል። በህክምና ሂደት ችግሮች ሲያጋጥሙ ተጠያቂነት እንዲኖርም እየሰራ ይገኛል።

ኩባንያው በካናዳ ስራውን እያከናወነ በነበረበት ግዜ ፍቃድ ያለውን የፀጉርና የቆዳ ቅባት ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ ያለው የገበያ ሁኔታ በደምብ ስለሚታወቅ በቀጥታ ወደ ማከፋፈል አልገባም። ከዚህ ይልቅ ሰዎች ምርቱን ተረድተው እንዲገዙና እንዲጠቀሙ የማስተማርና የማስገንዘብ ስራ ሰርቷል። ይህም ሰዎች ለከፈሉበት ባህላዊ መድሃኒት የሚገባቸውን የጤና ጥቅም ለማግኘት አስችሏቸዋል።

ዋና ስራ አስፈፃሚው እንደሚሉት የቡና ዘይት በአለም አቀፍ ገበያ ለተለያዩ የቆዳ በሽታዎች ህክምና በጣም ተፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል። ይህን ገበያ ይበልጥ ለማሳደግ ደግሞ ኩባንያው ረጅም አመት ፈጅቶበታል። የቡና ዘይትን አምርቶ ለገበያ ለማቅረብም በርካታ ቡና ተጠቅሟል። ህብረተሰቡ ከዚህ የቡና ዘይት ምርት በልዩ ልዩ መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆንም ኩባንያው ዘይቱን እዚሁ አምርቶ ከሀገር ውስጥ ገበያ አልፎ ለአለም አቀፍ ገበያም ጭምር እንዲተርፍ እየሰራ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት ኩባንያው ከ100 ኪሎ ቡና 5 ሊትር የቡና ዘይት ማምረት ችሏል። ይህ ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ የቡና ዘይት ከሚያመርቱ ሀገራት ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ ነው። ይህ መጠን ወደ ገንዘብ ሲቀየር የ1 ሊትር የቡና ዘይት ወጋ 1 ሺ ዶላር ያወጣል። ኢትዮጵያ በ300 እና 400 ዶላር ወደ ውጪ የምትልከው ጥሬ ቡና በዘይት መልክ በማምረት ቢላክ ወደ 5 ሺ ዶላር ሊጠጋ ይችላል። የቡና ዘይትን በስፋት በማምረትና ለሀገር ውስጥና ለውጪ ገበያ በማቅረብ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ለማምጣት ኩባንያው ፐርፐዝ ብላክ ከተሰኘውና በግብርና ላይ ከሚሰራው ድርጅት ጋር ተፈራርሟል።

በዚህ ቡናን በዘይት መልክ አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ሂደት አንደኛ አምራቹ ገበሬ ምርቱን በመሸጥ ገቢውን ማሳደግ ይችላል። ሁለተኛ ህብረተሰቡ የቆዳና ተያያዥነት ያላቸው የጤና እክሎች ሲያጋጥመው ዘይቱን እንደ አንድ ተፈጥሯዊ የመድሃኒት አማራጭ እንዲጠቀም ያስችለዋል። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ምርቱ ከሀገር ውስጥ አልፎ ለውጪ ገበያ ሲቀርብ ለሀገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ የውጪ ምንዛሬ ያስገኛል።

የቡና ዘይት በኢትዮጵያ ብዙም ጥቅሙ ላይታወቅ ይችላል። በሌላው ሀገር ግን እጅግ የታወቀና በርካታ የጤና ጥቅሞች ያሉት ነው። በዚሁ ምክንያት ኩባንያው ከተባበሩት አረብ ኢምሬትስ በኩል የቡና ዘይቱን አምርቱልን ጥያቄ ቀርቦለት ነበር። ነገር ግን ይህን ጥያቄ ወደ ጎን ትቶ የቡና ዘይትን በኢትዮጵያ አምርቶ ለገበያ እያቀረበ ይገኛል። ይህም ከቡና ዘይቱ ከሚገኘው የውጪ ምንዛሬና ከሚሰጠው የጤና ጥቅም ባለፈ የኢትዮጵያን ባህላዊ መድሃኒት የማሳደግና ለተቀረው አለም የማስተዋወቅ ጅምር ስራ ነው።

እንደ ዋና ስራ አስፈፃሚው ማብራሪያ ኩባንያው እስካሁን በሀገር በቀል እፀዋት ዙሪያ ለበርካታ ሰዎች ትምህርት ሲሰጥ ቆይቷል። ነገር ግን ትምህርቱ በቂ ባለመሆኑ ከኢትዮጵያ ባህላዊ መድሃኒት ጋር በተያያዘ በዘርፉ እውቀት ያላቸውን ሰዎች በማሰባሰብ ያላቸውን እውቀትና ልምድ የሚያካፍሉበትን ፕሮግራም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ለማስጀመር እቅድ ይዟል። ሰዎች ከመታመማቸው በፊት በሽታ መከላከል ላይ ትኩረት ተደርጎ እንዲሰራ ጥረት እያደረገም ይገኛል።

በተለይ ህብረተሰቡ ለምግብነት የሚያውላቸው እፀዋቶች ዙሪያ ጥልቀት ያለው እውቀት እንዲኖረው ግንዛቤ የመፍጠርና ራሱን ከበሽታ የሚከላከልበት ሁኔታ እንዲፈጠር የግንዛቤ ባስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል። ባህላዊ መድሃኒቶች ዘምነውና ሳይንሳዊ ሂደቶችን አልፈው ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎችንም ያከናውናል። ኢትዮጵያ ባህላዊ መድሃኒትና ህክምና ቱሪዝሟን እንድታሳድግም የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ኩባንያው በቡና ዘይት የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችን ለማከም ጥቅም ላይ ከማዋሉ በፊት ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ፍቃድ አግኝቷል። ይህም በዚህ ዘርፍ ፍቃድ ያገኘ የመጀመሪያው ኩባንያ ያደርገዋል። በተመሳሳይ የላብራቶሪ ፍተሻዎችን አልፎ ከኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን የመድሃኒት ማረጋገጫ ፍቃድ አግኝቷል።

ዘመናዊ መድሃኒቶች መነሻቸው ባህላዊ መድሃኒቶች ናቸው። ስለዚህ ባህላዊ መድሃኒቶች ከዘመናዊ መድሃኒቶች ጎን ለጎን ጉዳት በማያስከትል መልኩ በህክምና ባለሞያዎችና በባህላዊ ሀኪሞች ንግግር መሰረት ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል። ኩባንያውም የበባህላዊ ህክምና አገልግሎት ለህብረተሰቡ የሚሰጠው የህክምና ወረቀት ተቀብሎና ታካሚው ከዚህ በፊት የነበረውን የህክምና ታሪክ መርምሮ ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የፋርማሲ ትምህርት ቤት የፋርማሲዩቲካል ኬሚስትሪና ፋርማኮግኖሲ ትምህርት ክፍል ሃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ቢኒያም ጳውሎስ እንደሚገልፁት የባህላዊ ህክምና በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያስቆጠረና ሁነኛ የጤና ችግሮች መፍትሄ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ቢሆንም ለዘርፉ እምብዛም ትኩረት ባለመሰጠቱ የታሰበለትን ግብ እየመታ አይደለም።

በኢትዮጵያ የባህላዊ ህክምና እውቀት የተደበላለቀ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት እውቀቱን ለማጎልበት የሚያስችሉ እድሎች በሃገሪቱ ባለመመቻቸታቸውና ህክምናው የሚሰጠው በባህላዊ ሃኪሞች ፍላጎት ብቻ በመሆኑ ነው። ባህላዊ ሃኪሞቹ ህክምናውን ለገቢ ምንጭነት ብቻ መጠቀማቸውና እውቀቱንም ከቤተሰቦቻቸው በዘለለ ለሌሎችም የማስተላለፍ ልምዳቸው ደካማ በመሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ በየግዜው የሚተላለፈው የባህላዊ ህክምና እውቀት የተመዘገበና የጠራ አይደለም።

በማህበረሰቡ ዘንድ ከባህላዊ ህክምና ጋር በተያያዘ የተሳሳተ ግንዛቤ በመኖሩ ባህላዊ ሃኪሞችን የማግለልና የተለያዩ ስያሜዎችን የመስጠት ችግሮች በመኖራቸው እውቀቱ በጥቂት ባህላዊ ሃኪሞች ብቻ ተገድቦ ቀርቷል። አሁን ባለው ሁኔታም ወጣቱ ትውልድ ህክምናውን ተቀብሎ የመተግበርና እውቀቱን የማስቀጠል አዝማሚያው እየቀነሰ መጥቷል።

በሃገሪቱ በርካታ ቁጥር ያላቸው ለባህላዊ መድሃኒትነት የሚያገለግሉ እፀዋቶችና የተለያዩ ባህላዊ እውቀቶች መኖራቸው ህክምናውን ለማሳደግ እንደ መልካም አጋጣሚ የሚታዩ ቢሆንም ለህክምናው በበቂ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ባለመሆኑ የታሰበውን አገልግሎት መስጠት አልተቻለም። በዘመናዊና ባህላዊ ህክምና ሃኪሞች መካከል ትውውቅ ባለመኖሩና ተግባብተው የሚሰሩበት ሁኔታ ባለመፈጠሩ ለባህላዊ ህክምና እድገት አንዱ ተግዳሮት ሆኗል።

ባህላዊ መድሃኒቶችን ለማሳደግ በመንግስትም ሆነ በግል የሚደረገው ጥረት አነስተኛ መሆኑንና ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፣ የባህላዊ ህክምና መመሪያዎችና ደንቦች በበቂ ሁኔታ አለመዘጋጀታቸው፣ አንዳንድ የባህላዊ ሃኪሞች ሞያቸውን በድብቅ ማከናወናቸውና ሌሎችም የባህላዊ ህክምና ተጨማሪ ተግዳሮቶች ናቸው።

ረዳት ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት የባህላዊ ህክምናን በሚፈለገው መጠን በማሳደግ ከዘመናዊ ህክምና ጎን ለጎን አገልግሎት ለመስጠት ህክምናውን ተቋማዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በበላይነት የሚቆጣጠረውን አካልም መለየት ይጠይቃል። በዘርፉ ተሰማርተው አገልግሎት እየሰጡ ላሉ ሃኪሞችም እውቅና መስጠት ይገባል።

የባህላዊ ህክምና መድሃኒቶች በተለይም ፈዋሽነታቸው እንዲረጋገጥ ሳይንሳዊ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ሊቀርብላቸው ይገባል። የባህላዊ ህክምናና መድሃኒት እውቀቶችን ለመጠበቅ የሚያስችል አስገዳጅ የህግ ማእቀፎችን በማዘጋጀትና ህክምናው በመደበኛ የትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ተካቶ በዘርፉ ያሉ ሃኪሞች ትምህርት እንዲያገኙ በማድረግ ህክምናውን የበለጠ ማሳደግ ይቻላል።

ለባህል ህክምና መንግስት የሚያደርገው ድጋፍ ተጠናክሮ የማይቀጥል ከሆነና በዘመናዊ ህክምና ውስጥ ያሉ ባለሞያዎችም ለህክምናው ሳይንሳዊ ድጋፍ በማድረግ መድሃኒቶቹ እውቅና እንዲያገኙ ካልሰሩ ህክምናው እውቀቱ ባላቸው ግለሰቦች እጅ ብቻ ቀርቶ የታሰበለትን አስታዋፅኦ ሳያበረክት ሊጠፋ ይችላል። ይሁን እንጂ ለባህላዊ ህክምና በሚፈለገው ልክ ትኩረት በመስጠት ከዘመናዊ ህክምና ጋር አጣጥሞ ማስኬድ የሚቻል ከሆነ በሃገሪቷ የተሻለ የህክምና ስርዓት መፍጠር የሚቻልበትና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ እድል ይኖራል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ‹‹ታዝማ›› - በልብ ቀዶ ሕክምና ፈር ቀዳጁ ማዕከል

**አንተነህ ቸሬ**

የልብ በሽታ በዓለም አቀፍ ደረጃ በገዳይነታቸው እጅግ አደገኛ ከሆኑ በሽታዎች መካከል በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል። ሕክምናው እጅግ የሰለጠኑ ባለሙያዎችንና ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ መሆኑ ደግሞ የበሽታውን አሳሳቢነት የበለጠ አስጊና የከፋ ያደርገዋል። በሽታው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገራት የሚያስከትለው ችግር ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› የሚያሰኝ ነው።

በኢትዮጵያ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚከሰት ሞት በእጅጉ ጨምሯል። ከእነዚህ በገዳይነታቸው እጅግ አደገኛ ከሆኑ በሽታዎች መካከል አንዱ ደግሞ ይሄው የልብ በሽታ ነው። ችግሩ እንዲህ የተንሰራፋና ስር የሰደደ ሆኖ ሳለ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የልብ ቀዶ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ኢትዮጵያውያን የልብ ታማሚዎች ሕክምናውን በፍጥነትና በጥራት የሚያገኙበት የልብ ሕክምና ተቋም አልነበረም።

ይህ ሁኔታ ያሳሰባቸው ሀገር ወዳዱ የልብ ሐኪም ዶክተር ፍቅሩ ማሩ፣ ከሌሎች ግለሰቦችና ተቋማት ጋር በመተባበር ከልብ ቀዶ ጥገና ውጭ ያሉ የልብ ሕክምናዎችን የሚሰጥ ‹‹አዲስ የልብ ሕክምና ሆስፒታል›› (Addis Cardiac Hospital) የተባለ ተቋም አቋቁመው ወገናቸውን ማገልገል ጀመሩ። ሆስፒታሉ በሚሰጣቸው የልብ ሕክምናዎች (የልብ ምርመራ፣ የልብ ሕመምተኛ ክትትል፣ የልብ ባትሪዎችን የመትከል፣ የጠበቡ የልብ የደም ስሮችን ማስፋት…) የበርካታ ዜጎችን ስቃይ በማስቀረት ሕይወታቸውን መታደግ ቢችልም፣ ከልብ ሕክምና ባሻገር የልብ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ይህን ተግባር ሊያከናወን የሚችል የሕክምና ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ነበር።

በዚህም መሠረት ዶክተር ፍቅሩ ማሩ ከ‹‹አዲስ የልብ ሕክምና ሆስፒታል›› ጋር በመተባበር ያቋቋሙት ‹‹ታዝማ የውስጥ ደዌና የቀዶ ሕክምና ልዩ ማዕከል›› (TAZMA Medical and Surgical Specialized Center) በ2004 ዓ.ም የልብ ቀዶ ሕክምና እንዲጀምር አደረጉ።

የማዕከሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አስቻለው ዓለማየሁ እንደሚገልፁት፣ የማዕከሉ መቋቋም ዋና ዓላማ የልብ ቀዶ ሕክምናን በሀገር ውስጥ በመስጠት በበሽታው የሚሞቱ ዜጎችን ሕይወት መታደግና ለሕክምናው ወደ ውጭ ሀገራት የሚደረገውን ጉዞ በማስቀረት ታካሚዎችን ከእንግልት ማዳን ነው። ይሁን እንጂ ማዕከሉ ሥራውን ሲጀምር የልብ ቀዶ ሕክምና ሙያን የተማሩ ኢትዮጵያውያን በሀገር ውስጥ ስላልነበሩ፣ የልብ ቀዶ ሕክምናው ከስዊድን በሚመጡ ባለሙያዎች ይሰጥ ነበር። እነዚህ ባለሙያዎች በየዓመቱ ለሶስትና ለአራት ጊዜያት ያህል ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የልብ ቀዶ ሕክምናዎችን ሰጥተዋል።

ይህ አገልግሎት የልብ ቀዶ ሕክምና ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች እፎይታን የፈጠረ ቢሆንም፣ አገልግሎቱን የሚፈልጉ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ፣ በልብ ቀዶ ሕክምና የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን ሐኪሞችን ማፍራት እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነበር። ከስዊድን በመምጣት የልብ ቀዶ ሕክምና ያከናውኑ የነበሩ ባለሙያዎች ከልብ ቀዶ ሕክምናው ባሻገር ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በዘርፉ ብቁ እንዲሆኑ የእውቀትና ልምድ ሽግግር ተግባር አከናውነዋል።

የልብ ቀዶ ሕክምናውን በውጭ ባለሙያዎች የማከናወኑ ተግባር የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ እስከተከሰተበት ወቅት ድረስ ቀጥሎ ነበር። ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በኋላ የልብ ቀዶ ሕክምናው ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች መከናወን ጀመረ።

ይህ ወቅት ከኢትዮጵያ የሕክምና ታሪክ ወሳኝ ምዕራፎች መካል አንዱ ሆኖ ተመዝግቧል። እጅግ ውስብስብየሆነውንናበኢትዮጵያውስጥበኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ይደረጋል ተብሎ ያልተገመተውን የሕክምና ዓይነት በብቃት ማከናወን ለዜጎች ተስፋ፣ ለሀገርም ኩራት ነው። በወቅቱ የሕክምና ባለሙያዎቹ ቁጥራቸው እጅግ በጣም ጥቂት ቢሆንም የልብ ቀዶ ሕክምናን በውጭ ሀገራት ተምረው የመጡ ኢትዮጵያውያን ሐኪሞች ነበሩ። እነዚህ ባለሙያዎች እውቀታቸውን ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እያጋሩ ያከናወኗቸው የልብ ቀዶ ሕክምናዎች ለታካሚዎች፣ ለተቋሙና ለኢትዮጵያ ትልቅ ትርጉም ያላቸው ተግባራት ነበሩ።

‹‹ታዝማ›› የውስጥ ደዌና የቀዶ ሕክምና ልዩ ማዕከል ሁሉንም የሕክምና ዓይነቶች በጥራት የሚሰጥ ተቋም ቢሆንም፣ በልብ ቀዶ ሕክምና ዘርፍ የሚሰጣቸው ሕክምናዎችና ያስመዘገባቸው ስኬቶች፣ ተቋሙን በሀገሪቱ በዘርፉ ፈር ቀዳጅና ብቸኛ እንደሚያደርጉት ዋና ሥራ አስኪያጁ አቶ አስቻለው ይገልፃሉ።

‹‹ታዝማ ኢትዮጵያ ውስጥ ይከናወናሉ ተብለው የማይገመቱ ውስብስብ የልብ ቀዶ ሕክምናዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በስኬት አከናውኗል። የልብ ቀዶ ሕክምና በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ብቻ እንዲከናወን ያደረገ የመጀመሪያው ተቋምም ነው። እነዚህ ሕክምናዎች ኢትዮጵያን በዘርፉ በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ ፈር ቀዳጅ እንድትሆን በማስቻል ሀገር አኩርተዋል፤ ሕይወት ታድገዋል። ከኤርትራ፣ ከሱዳን፣ ከሶማሊያና ከጅቡቲ የመጡ ዜጎችም ወደ ማዕከሉ በመምጣት እነዚህን የሕክምና አገልግሎቶች አግኝተዋል› ሲሉ አብራርተዋል።

‹‹ታዝማ›› ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በስኬት ካከናወናቸው የልብ ቀዶ ሕክምናዎች መካከል ልብና ሳምባ ሥራቸውን አቁመው ከልብ ወደ ሰውነት የሚወስደውን ትልቁን የደም ቱቦ የመቀየር (Bentall Procedure)፣ ትልቁን የልብ የደም ቧንቧ በድጋሚ የመቀየር (Redo Bentall)፣ ልብና ሳምባን ተክቶ ከሚሰራው ማሽን ውጭ ልብ መደበኛ ሥራውን እየሰራ የሚከናወን የልብ የደም ስር ቅያሬ (Off-Pump Coronary Artery Bypass Surgery - CABG)፣ ‹‹ፐልመሞነሪ ኢንዳይርቴሬክቶሚ›› (Pulmonary Endarterectomy) እና ‹‹አርተሪዎ ቬንቲኩላር ሴፕታል ዲፌክት ሪፔይር›› (Arterioventricular Septal Defect Repair) ይጠቀሳሉ። እነዚህ ሕክምናዎች በኢትዮጵያም ብቻ ሳይሆን በምስራቅ አፍሪካም ጭምር ለመጀመሪያ ጊዜ የተከናወኑ ውስብስብ የልብ ቀዶ ሕክምናዎች ናቸው።

አካላዊ መቀራረብና መነካካት እጅግ አስፈሪና እንደ ተዓምር በሚቆጠርበት በዚያ የኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት ‹‹ታዝማ›› አገልግሎቱን እንዳላቋረጠ የሚያስታውሱት አቶ አስቻለው፣ ማዕከሉ በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅትም ሕይወት የመታደግ ተግባሩን በከፍተኛ ጥንቃቄና ኃላፊነት ሲያከናውን እንደነበር ይገልፃሉ።

‹‹ታዝማ›› የውስጥ ደዌና የቀዶ ሕክምና ልዩ ማዕከል የልብ ቀዶ ሕክምና ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በውጭ ባለሙያዎች ከ500 በላይ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ደግሞ ከአንድ ሺ 200 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የልብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት ሰጥቷል። በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች የልብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት ካገኙ ዜጎች መካከል 440 የሚሆኑት ሕፃናት ናቸው።

ከልብ ቀዶ ሕክምና በተጨማሪ በሌሎች የውስጥ ደዌና የቀዶ ሕክምና ዘርፎች በሰጣቸው ሕክምናዎች ደግሞ ከ132ሺ በላይ ለሚሆኑ ታካሚዎች አገልግሎት ሰጥቷል። ‹‹ታዝማ›› የልብ ቀዶ ሕክምናዎች በሀገር ውስጥ እንዲሰጡ በማድረጉ ዜጎች ወደ ውጭ ሀገራት ተጉዘው ለሕክምና ሊያወጡት የነበረውን ከ15 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ማዳን ተችሏል።

‹‹ታዝማ›› በአሁኑ ወቅት ከ100 በላይ ቋሚ ሠራተኞች ያሉት ሲሆን፣ የልብ ቀዶ ጥገና ሕክምናዎችን በሀገር ውስጥ በማከናወን ጥራት ያለው ሕክምና በመስጠት እና በዘርፉ የሰለጠነ ሰው ኃይል እንዲኖር በመትጋት ሀገራዊ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል። በዓመት ከ400 በላይ የልብ ቀዶ ጥገናዎችን ያደርጋል። የኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን ቁጥር ለማብዛትና አቅማቸውን ለማጎልበት የሚያስችሉ ሥራዎችን ለማከናወን ከሌሎች የሕክምናና የትምህርት ተቋማት ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችን ተፈራርሞም እየሰራ ይገኛል።

ማዕከሉ ከሕክምና ሥራው ባሻገር ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን አከናውኗል፤ እያከናወነም ይገኛል። በዚህ ረገድ በትምህርትና በጤና መስኮች ያደረጋቸው ድጋፎች ተጠቃሽ ናቸው። ለዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል እና ለቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ልዩ ልዩ የሕክምና ቁሳቁስን እንዲሁም አቅም ለሌላቸው ወገኖች ለሚደረጉ የምገባ መርሃ ግብሮችና ለአገልግሎት መስጫ ተቋማት የገንዘብ ድጋፎችን አድርጓል። በተለይም ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የልብ ቀዶ ሕክምና እንዲጀምር በከፍተኛ ወጪ የተገዛውን ልብና ሳምባን ተክቶ የሚሰራውን ማሽን (Cardiopulmonary Bypass Machine) ማበርከቱ ጎልቶ ሊጠቀስ የሚችል የ‹‹ታዝማ›› በጎ ተግባር ነው። ከዚህ በተጨማሪም መማር እየፈለጉ አቅም ላጠራቸው ተማሪዎችም የትምህርት ቁሳቁስን አበርክቷል። ማዕከሉ በሀገራዊ ጥሪዎች ላይም ንቁ ተሳታፊ ነው።

አቶ አስቻለው ‹‹ማዕከሉ ከልብ ቀዶ ሕክምና በተጨማሪ ሌሎች ሕክምናዎችንም ይሰጣል። ሁሉም ዓይነት የውስጥ ደዌ ሕክምናዎች (የስኳር፣ የጨጓራ፣ የነርቭ እና ሌሎች ቀዶ ጥገናዎች) በሰብ ስፔሻሊስቶች ይሰጣሉ።›› ሲሉ ጠቅሰው፣ የልብ ቀዶ ሕክምናው ግን በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ አገልግሎት ነው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ጥራት ያለው ሕክምና በመስጠት፣ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን በማፍራት እና ለውጭ ሕክምና ሊወጣ የነበረን የውጭ ምንዛሬን በማስቀረት ስኬታማ ነው። ሕሙማን ወደ ውጭ ሀገራት ሳይሄዱ በራሳቸው ቋንቋ እየተግባቡ፣ በቤተሰባቸው መሐል ሆነው፣ በራሳቸው ወገን ሲታከሙ ለታካሚዎች፣ ለተቋሙና ለሀገር ትልቅ ትርጉም አለው።

‹‹ታዝማ›› በተሰማራባቸው የሕክምና መስኮች፣ በተለይም በልብ ቀዶ ሕክምና ዘርፍ፣ በርካታ ስኬቶችን ሲያስመዘግብ ሁሉም መንገድ አልጋ በአልጋ ሆኖለት አይደለም። ማዕከሉ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ተስፋ መሆን የቻለው ለሚያጋጥሙት ችግሮች ሳይበገር በፅናት በመጓዙ ነው።

የአላቂ እቃዎች እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዲሁም የቦታ ችግር የማዕከሉ የሥራ መሰናክሎች እንደሆኑ አቶ አስቻለው ይናገራሉ። ‹‹የልብ ቀዶ ሕክምና ለማከናወን በግብዓትነት የሚያገለግሉ እቃዎች በአስመጭዎች ዘንድ ስለማይታወቁና ዋጋቸውም ውድ ስለሆነ እቃዎቹን ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል። እነዚህን እቃዎች በበቂ ሁኔታ ማግኘት ከተቻለ ማዕከሉ አሁን ከሚሰራው የበለጠ ሥራ በመሥራት ብዙ ወገኖችን መርዳት ይቻላል›› ይላሉ።

መንግሥት ለ‹‹ታዝማ›› የሚያደርገውን ድጋፍ በተመለከተ፣ የመንግሥት ድጋፍ ለማዕከሉ ሥራዎች ጉልበት እንደሆኑለት የሚጠቁሙት ዋና ሥራ አስኪያጁ፣ ‹‹መንግሥት ለማዕከሉ ሥራዎች ድጋፍ ያደርጋል። የልብ ቀዶ ሕክምናው የሚከናወነውም መንግሥት እነዚህ ግብዓቶች በልዩ ፈቃድ እንዲገቡ በመፍቀዱ ነው። የልብ በሽታ በዓለም ላይ ተላላፊ ካልሆኑና በገዳይነታቸው በዋናነት ከሚጠቀሱት በሽታዎች መካከል አንዱ ነው። መንግሥትም ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ቢሆንም ከችግሩ ስፋት አንፃር ተጨማሪ ትኩረት መስጠትና ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል›› በማለት ያስገነዝባሉ።

‹‹ታዝማ›› የውስጥ ደዌና የቀዶ ሕክምና ልዩ ማዕከል ላከናወናቸው ሀገር የሚያኮሩ የሕክምና ተግባራትና የበጎ አድራጎት ሥራዎች ከተለያዩ አካላት ምስጋና ተቸሮታል፤ እውቅናዎችንም አግኝቷል። ከእነዚህም መካከል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ /ዶክተር/ ለማዕከሉ መስራች ለዶክተር ፍቅሩ ማሩ የሰጡት እውቅናና ምስጋና በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በ2014 ዓ.ም ‹‹ሕክምና ትጉህነትን፣ ርኅራኄንና ሥነ-ምግባርን ብሎም ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደምን የሚሻ ሞያ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ሀብቷን አፍስሳ የምታፈራቸው የሕክምና ባለሞያዎች በቅንነት ሲያገለግሏት ማየት ተስፋን ይሰጣል። እርስዎም የሕክምና ተግባርዎን ሲከውኑ ዕውቀትዎን ሳይቆጥቡ፣ ያለመታከት ላበረከቱት አስተዋፅዖ እና ስለሰጡት ትኅትና የተመላበት አገልግሎት ከልብ የሆነ ምስጋናዬ ይድረስዎ!›› በማለት ለዶክተር ፍቅሩ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ማዕከሉ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ከተለያዩ የጤና ዘርፍ የሙያ ማኅበራት፣ ከአአቢሲንያ የጥራት ሽልማት፣ ከክፍለ ከተሞች፣ ከትምህርት ተቋማትና ሌሎች ድርጅቶች ምስጋናና እውቅና ተሰጥቶታል።

በልብ ቀዶ ሕክምና በአርዓያነትና በስኬታማነቱ የሚጠቀሰው ‹‹ታዝማ›› የውስጥ ደዌና የቀዶ ሕክምና ልዩ ማዕከል፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን ተልሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነና ጥራቱን የጠበቀ ሕክምና መስጠት የሚችል ተቋም ለመሆን እየተጋ ይገኛል። ‹‹ማዕከሉ ሁሉም ሰው ለልብ ቀዶ ሕክምና ከሀገር ውጭ እንዳይወጣና እንዳይጉላላ የማድረግ እቅድ አለው። መንግሥትን በመጠየቅና በራሳችን በምናደርጋቸው ጥረቶች ሰፊ ቦታ በማግኘት አሁን ካለው የበለጠ ቁጥር ያለውን ታካሚ ተደራሽ ለመሆንም እየሰራ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በቂ ባለሙያዎችን በማፍራት የልብ ንቅለ ተከላ ማድረግ የሚችልና የምርምር ሥራዎችን የሚያከናውን ተቋም እስከ መገንባት የዘለቀ የረጅም ጊዜ እቅድም አለው›› በማለት ዋና ሥራ አስኪያጁ አቶ አስቻለው ዓለማየሁ ስለ ‹‹ታዝማ›› የወደፊት እቅዶችም ገልጸዋል።



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር
The Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia

ሚያዚያ 12፣ 2014

ለዶ/ር ፍቅሩ ማሩ

ሕክምና ትጉህነትን፣ ርኅራኄን እና ሥነ ምግባርን ብሎም ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደምን የሚሻ ሞያ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ሀብቷን አፍስሳ የምታፈራቸው የሕክምና ባለሞያዎች በቅን ሲያገለግሏት ማየት ተስፋን ይሰጣል።

እርስዎም የሕክምና ተግባርዎን ሲከውኑ ዕውቀትዎን ሳይቆጥቡ፣ ያለመታከት ስላበረከቱት አስተዋጽዖ እና ስለ ሰጡት ትኅትና የተመላበት አገልግሎት ከልብ የሆነ ምስጋናዬ ይድረስዎ።

ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

ፖሊቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## የሰፌዱ ጦስ

አስመረት ብስራት



የተወለዱባት ቀዬ እጅግ ነፋሻማ በተፈጥሮ የተዋበች መንደር ነበረች። በተራሮች የተከበበችው መንደር ብዙም ሰፊ የሚባል የእርሻ መሬት ባይኖርም ባለቻቸው መሬት ጥሩ ምርትን የሚያገኙ ገበሬ ቤተሰቦች መካከል ነበር ያደጉት። በቀየዋ በየቦታው የፈለቁት ምንጮች የአካባቢዋን ልምላሜ ያደመቁ ነበሩ። ቤቶቹ የተጠጋጉና የቀረው መሬት ደግሞ የእርሻ በመሆኑ የተነሳ ከብቶችን ለማስጋጥ እንኳን ተራራውን ወጥተው ሌላ መንደር መሄድ ግድ ይላቸው ነበር።

ውሃ እንደ ልብ የሆነባት ይህች መንደር በየጓሮው የተተከሉት የጓሮ አትክልቶች ሁሌም አረንጓዴ ሆና እንድትኖር አድርገዋታል። ዛሬ በዶሴ አምዳችን የምንቃኛቸው ወጣቶች ከዚህች ውብ መንደር የወጡ የገበሬ ልጆች ናቸው።

ቤተሰቦቻቸው በአናት በአናቱ ልጆች በመውለዳቸው ልጆቻቸውን ባለቻቸው መሬት ለማስተዳደር ተሳናቸው። ሕፃን እያሉ በእረኝነቱም እና በመላላክ ጭምር ቢያድጉም ከፍ ሲሉ ግን የቤተሰቦቻቸውን የእርሻ መሬት ከመቀራመት ይልቅ ከተማ ገብቶ መሥራት ምርጫቸው አደረጉ። ወጣቶቹ ከተማ ከገቡ በኋላ ያገኙትን ሥራ ሰርተው በጋራ በማደር ጥሪት ለማጠራቀም ይታትሩ ጀመር።

በየእለቱ ለእድገት የሚጥሩት እነዚህ ወጣቶቸ ያች ውብ መንደራቸው በዓይናቸው ላይ እየተሽከረከረች ናፍቆት ቢቀጣቸውም ጠንከር ብሎ በመሥራት የተሻለ ሰው ለመሆን ይጥሩ ነበር። ስኬት ለማግኘትም አሉ የተባሉ በአቅማቸው ሊሰሯቸው የሚችሉ ሥራዎችን በሙሉ ለመሥራት መሞከር የየእለት ተግባራቸው ነበር።

### ሠራተኛቹ ወጣቶች

ወጣቶቹ ከተወለዱባት ቀዬ ከወጡ በኋላ ባይተዋርነት እንዳይሰማቸው በጋራ አንድ ቤት ተከራይተው ይኖሩ ጀመር። አብረው ወጥተው አብረው መግባት ልዩ ምልክታቸው እስኪሆን ደረስ ሳይለያዩ ይውሉ ነበር። የሸክም ሥራ ሲሰሩ እንኳን እየተጋገዙ አብረው ነበር የሚውሉት። ደስታቸውም ሀዘናቸውም በጋራ የሆኑት እነዚህ ልጆች ከቅርርባቸው የተነሳ የአንድ እናት ልጆች እንጂ ከተለያየ ቤተሰብ የተገኙ አይመስሉም ነበር። የሰሩትን ሰርተው በሚያገኟት ገንዘብ የሚቃመሱትን ገዝተው ወደ ማደሪያቸው በጊዜ ይገቡ ነበር። መተጋገዛቸውን የተመለከተ ሰው በሙሉ ነፋስ መካከላችሁ አይግባ እያለ ይመርቃቸው ነበር።

ከተማውን ሲለምዱት ግን የተሻለ የሥራ አማራጭ መመለከት ፈለጉ። በዚህም አጋጣሚ የተወለዱበት አካባቢ ልጆች የሚሰሩበት ወፍጮ ቤት ሰው እንደሚፈልግ ተነገራቸው። ወፍጮ ቤት ውስጥ እህል አበጥሮ አስፈጭቶ ደንበኞች ጋር የማድረስ ሥራና፤ ከወፍጮ ቤቱ ጎን ለጎን እንጀራ ጋግሮ የማስረከብ ሥራ ነበር በክፍት የሥራ ቦታነት ያገኙት።

በዚህም ወጣቶቹ ከወፍጮው አረፍ ሲሉ እንጀራ ለተረካቢዎች በማድረስ ሥራ ላይ ይሰማራሉ። ይህ ሥራ ምግብና መኝታም ስለሰጣቸው ያገኙትን ገንዘብ ለማጠራቀም ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸው ነበር። ለለውጥ የተነሱት ወጣቶች ገቢያቸውን ከፍ የሚያደርግላቸው ምንም ወጪ የሌለበት ሥራ በማግኘታቸው ደስተኛ ሆነው ነበር።

ማልደው ተነስተው እስከ ምሽት ሲሰሩ የሚወሉት ወጣቶች እጅግ በጣም ታታሪ ስለነበሩ ሶስቱንም አዲሱ አሰሪያቸው ወደ ቸው ነበር። በዚህም የተነሳ ቀደመው በወፍጮ ቤቱ ሲሰሩ የነበሩት ወጣቶች ይቀኑባቸው ጀመር። በዚህም የተነሳ በጣም የሚወደዱት ጓደኛሞች መካከል አንዳንድ ነገር እያነሱ እንዲጣሉ ያደረጓቸው ጀመር።

### የጠቡ መነሻ

በትንሹም በትልቁም መኳረፍ ልማዳቸው የሆኑት የቀድሞ ጓደኛሞች የነበረ ፍቅራቸው ቀዝቅዞ ፊት መነሳሳት ጀመሩ። ከሶስቱ ጓደኛሞች መካከል በእድሜ አነስ የሚለው ልጅ በየሰበቡ ስለሚናገሩት ቅያሜው በዝቶ ጥሏቸው ለመሄድ ተነሳ።

ልጁ እንጀራ እንዲያደርስ ተልኮ ሲመለስ እግረ መንገዱ አንድ ወፍጮ ቤት ሥራ መኖሩን ይጠይቃል። ያኔ ሰዎቹ እንጀራ መጋገሪያ ቤት ሥራ መኖሩን ነግረውት ሳይመልስ በዛው ተቀጥሮ ያድራል። ያ ወጣት እንጀራ ሊያደርስበት ይዞት የወጣውን ሰፌድ እንኳን ሳይመለስ በዛ እንደወጣ ይቀራል።

በእለቱ ልጁ ከመጥፋቱ በላይ ሰፌዱን ይዞ መቅረቱ ያንገበገበው አሰሪያቸው ጓደኞቹን ሰፌዱን ካላስመለሳችሁ ከሥራ አባርራችኋለሁ በማለት ያስፈራራቸዋል። ልጁ ማንም ሰው ሳያየው ሹልክ ብሎ ልብሱን መውሰዱን የጠፋው የደሞዝ ሰሞን በመሆኑ ለክፍያ ሲል ወደ ወፍጮ ቤቱ ባለመመለሱ ሁሉም ተናደዱበት።

ስልክ ሲደውሉለት አላነሳም ማለቱ ያበሳጫቸው ጓደኞቹ ከበፊቱ ፀባቸው በላይ አሁን ሳይናገር መሄዱ እጅግ በጣም አንገበገባቸው። በዚህም ምክንያት የልጁን መገኛ ማፈላለግ ጀመሩ። በእረፍት ቀናቸው እሁድ እለት እየተነሱ ቂም የያዙበትን አብሮ አደግ ጓደኛቸውን ለመፈለግ ታየ የተባለበት ቦታ በሙሉ ረገጡ።

ከብዙ ፍለጋ በኋላ እነሱ ከሚሰሩበት ወፍጮ ቤት በቅርብ ርቀት የሚገኝ እንጀራ መጋገሪያ ውስጥ የሚሰራ ተወዳጅ ሠራተኛ መሆኑን ሰሙ፤ ስለዚህ ከጓደኞቹ ተለይቶ ሌላ ሥራ ከመግባቱም በላይ እነሱን በወሰደው ሰፌድ ምክንያት ከአሰሪያቸው ጋር ፊትና ጀርባ እንዲሆኑ ማደረጉ ሆዳቸውን አሻክሮታል።

### መዘዘኛው ሰፌድ

ልጁን እንዳገኙት ይዘው ከመጠየቅ ይልቅ ተዘጋጅተውና ቀን ጠብቀው መመለስ መርጫቸው ያደረጉት ጓደኛሞቹ ቢምረው(አንዱአለም) ዓለሙ ይግዛው፣ አቤው(መኮንን) ያለው ፈለቀ ልጁን የሚጎዱበትን አማራጭ በሙሉ መመልከት ጀመሩ። ከብዙ ሃሳብና እቅድ በኋላ አንድ ቀን በቀጥታ ሄደው ከጓደኛቸው ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ጀመሩ።

ቀኑ ግንቦት 12 ቀን 2014 ዓ.ም ነበር። በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ቴስ ሰፈር እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ ጓደኛቸው ግንቦት 3 ቀን 2014 ዓ.ም ሰፌድ ወሰደብኝ በሚል ምክንያት አብሮ አደግ ጓደኛሞቹ መሀል አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር።

በወቅቱ ጓድኛሞቹ መቀያየማቸወን የሰሙ ሌሎች የትውልድ ቀያቸው ልጆች ይሄን አለመግባባት በእርቅ ለመጨረስ በሂደት ላይ ነበሩ። ቂም የተያያዙት ጓደኛሞች ግን አስታረቂን ወደጎን በማለት ዱላ፣ አካፋ እና ድንጋይ በመያዝ ወደ ልጁ የሥራ ቦታ በመሄድ ቤቱ ላይ ድንጋይ በመወርወር እንዲወጡ ካደረጉ በኋላ ጨካኝነታቸውን እና ነውረኝነታቸውን በሚያሳይ ሁኔታ 1ኛው ተከሳሽ ድንጋይ ወርውሮ ሟች አወቀ መቆየቴን ቅንድቡን ሲመታው 2ኛው ተከሳሽ በአካፋ ማጅራቱን መቶ በመጣል ሕይወቱ እንዲያልፍ ያደረጉ በመሆኑ በፈፀሙት በዋና ወንጀል አድራጊነት ከባድ የሰው መግደል ወንጀል እንዲያዙና ክስ እንዲቀርብባቸው ሆኗል።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ወንጀል ፈጻሚዎቹን ድርጊቱን ከፈፀሙበት ቦታ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው ሲሆን ወጣቶቹ ጓደኛቸውን በጭካኔና ነውረኝነት በተሞላው መልኩ መግደላቸውን የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል። የተከሳሾቹ የእምነት ክህደት ቃል፤ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል፤ የፎረንሲክ ምርመራውን አካቶ ማስረጃውን ያጠናቀረው ፖሊስ በፈፀሙት አስነዋሪ ተግባር የተነሳ በዋና ወንጀል አድራጊነት ከባድ የሰው መግደል ወንጀል እንዲያዙና ክስ እንዲመሰርትባቸው በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዓቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦባቸዋል።

### የዓቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዓቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦባቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት በዚህ መልኩ የክስ ዝርዝር አቅርቧል።

በዓቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ ላይ 1ኛ ቢምረው(አንዱአለም) ዓለሙ ይግዛው፣ 2ኛ አቤው(መኮንን) ያለው ፈለቀ የተባሉ ተከሳሾች ግንቦት 12 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ቴስ ሰፈር እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ ግንቦት 3 ቀን 2014 ዓ.ም ሰፌድ ወሰደብኝ በሚል በአንድ የዓቃቤ ሕግ ምስክር እና በተከሳሾች መሀል አለመግባባት ተፈጥሮ፣ ይሄን አለመግባባት በእርቅ ለመጨረስ በሂደት ላይ እያለ ተጠርጣሪዎች ዱላ፣ አካፋ እና ድንጋይ በመያዝ ወደ አንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሥራ ቦታ በመሄድ ቤቱ ላይ ድንጋይ በመወርወር እንዲወጡ ካደረጉ በኋላ ጨካኝነታቸውን እና ነውረኝነታቸውን በሚያሳይ ሁኔታ 1ኛ ተከሳሽ ድንጋይ ወርውሮ ሟች አወቀ መቆየቴን ቅንድቡን ሲመታው 2ኛ ተከሳሽ በአካፋ ማጅራቱን መቶ በመጣል ሕይወቱ እንዲያልፍ ያደረጉ በመሆኑ በፈፀሙት በዋና ወንጀል አድራጊነት ከባድ የሰው መግደል ወንጀል በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዓቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦባቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል።

### ውሳኔ

**በክርክሩ ሂደትም 1ኛ ተከሳሽ በማረሚያ ቤት ሆኖ፣ 2ኛ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲቀጥል ተወስኖ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ 1ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክር አቅርቦ ያሰማ ቢሆንም በዓቃቤ ሕግ የቀረበበትን ክስ መከላከል ባለመቻሉ፣ 2ኛ ተከሳሽም የመከላከያ ምስክር ባለማቅረቡ ፍርድ ቤቱ በተከሳሾች ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት የቅጣት ውሳኔ በማሳረፍ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ2ኛ ተከሳሽ ላይ በሌለበት በ20 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ‹‹እንተዛዘብ›› ከተባለማ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ከህይወት ልምዳችን ደጋግመን እንዳየነው በየትኛውም አጋጣሚ ከለውጥ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮች ይኖራሉ። ልብ ብለን ካስተዋልነው ደግሞ አንዳንድ ለውጦች ልክ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ናቸው። ለሁለቱም በእኩል አይመዝኑም። አንዱን ወገን አስደስተው ሌላኛውን ማሳዘን፣ ማስከፋታቸው አይቀሬ ይሆናል።

ይህ እውነት በተለያዩ የህይወት አጋጣሚዎች ሲስተዋል ያየነው ሀቅ ነውና ለምን ስንል የምንሟገትበት አይደለም። እንዴት ካልን ደግሞ ለአባባሉ ብዙ ማሳያዎች በመኖራቸው በክርክሩ ልንረታ እንችላለን።እኔ ግን ለአሁኑ የማነሳው ይህን መሰሉን ሀቅ የሚጋፋውን አይደለም። እንደ ክፍተት የምጠቁመው ከለውጦች ጋር ተያይዞ ክስተቶች ሲኖሩ ሆን ተብለው ስለሚፈጠሩ ችግሮች እንጂ ።

መከረሚያውን በከተማችን የኮሪደር ልማቱ ቀን ተሌት እየተሰራ ነው።ይህ አጋጣሚ ደግሞ ብዙ ነገሮችን መለስ እያልን እንድናስብ አስችሎናል። አሁን አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናነቷ እንደሚመጥናት ሆኖ በልኳ ልትታይ የቆረጠች ይመስላል። መቁረጥ ሲባል ደግሞ እንዲሁ በሃሳብ ብቻ አልሆነም። ትናንት በክፉ እሳቤ እጅ ሲጠቀምባት፣ ጥርስ ሲነከስባት የኖረ ታሪኳን በሥራ ልትሽረው ተነስታለች። ዛሬ ይህን የጀመሩ እጆች እረፍት አልባ ናቸው። ዕቅዱን የወጡ አእምሮዎችም ስለ ትግበራው ስኬት በፈጣን ሩጫ ላይ ይገኛሉ።

ወደቀደመው ሃሳቤ ልመለስ። ከእንዲህ መሰሉ ለውጥ ጋር ተዳምረው ሊፈጠሩ ወደሚችሉት ችግሮች የከተማችን የኮሪደር ልማት አሁን ብዙ መልኮችን እያሳየን ነው። እግረ መንገዱን ደግሞ የሚያስተዛዝቡን እውነታዎች ያጋጥሙን ይዘዋል ።

አንዳንዴ የአንዱ አጋጣሚ ለሌላው ክፉና ደግ ገጽታ አለው። አንዱ ‹‹ጎድሎብኛል›› በሚለው ነገር ሌላው ደግሞ አጋጣሚው ሲሳይ ሆኖት ፈገግታው ሲበራ፣ ውስጡ ሀሴት ሲያደርግ ይስተዋላል።

ይህ እውነት እንደየሁኔታው ይለያይ እንጂ በየአጋጣሚው ልናልፍበት መገደዳችን አልቀረም። የኮሪደር ልማቱ በተጀመረ ማግስት ራስ ወዳድነታቸውን ያሣዩን አንዳንድ ባለታክሲዎች ዛሬም ድረስ በማንአለብኝነት ዘልቀዋል። እንዲህ አይነቶቹ ሁሌም መነሻና መድረሻቸው የግል ጥቅምና ትርፋቸው ብቻ ነው።

እነዚህ ወገኖች አጋጣሚው ዛሬም ድረስ ሲሳይ ሆኖላቸዋልና መንገዱን እያሳበቡ ከታሪፍ በላይ ያስከፍላሉ። በስራው እያመሀኙ አንዱን በአንዱ ይደርባሉ። ባሻቸው ቦታ ጭነው ከፈለጉት ስፍራ ቢያወርዱ ‹‹ለምን ?››ባይ ጠያቂ የላቸውም ። አብዛኞቹ እንደበታቸው የተገራ ድርጊታቸው የታረመ አይደለም።

በእንዲህ አይነቶቹ ማንነት ብዙኃኑ ቢያማርርም ዳግም አገልግሎታቸውን ከመጠቀም ሌላ ምርጫ የለውም። ዛሬ በትንሹ ያሳዩትን ሙከራ ነገ በእጥፍ አሻሽለው ያስቀጥሉታል። ይህ እውነት እስካሁን እያስተዛዘበ አብሮ አዝልቆናል። ለምን የሚል የሕግ አካል መርምሮ የሚያስቀጣ ደንብና መመሪያ አለመኖሩ ደግሞ ትርፍን ከኪሳራ አጨባብጧል።

የኮሪደሩ ልማት መካሄድ ከጀመረ ወዲህ ድንገቴ የመንገድ መዘጋትና የአቅጣጫ መቀየር ጉዳይ የተለመደ ሆኗል። መንገዱ ደግሞ ጠዋት አልያም ከደቂቃዎች በፊት ያለምንም ችግር ያለፉበት ሊሆን ይችላል። እንዲህ ባጋጠመ ጊዜ አርፍዶ ሥራ መድረስ፣ አምሽቶ ከቤት መግባት ብርቅ አይደለም።

ይህ ይሆን ዘንድ የልማት ሥራው ባህሪ ወሳኝነት አስገድዶ ነው ብለን እንገምት። እንዲህ አይነቱን ዋጋ መክፈልም የዜግነት አንዱ መገለጫ ስለመሆኑም ግድ ይበለን። አስቀድሞ መረጃ ባለመኖሩ ምክንያት ለሚደርሰው እንግልት ግን ኃላፊነቱን የሚወስድ አካል ሊኖር ይገባል።

ሌላው የሚያስተዛዝበን ጉዳይ ከዚሁ መንገድ መዘጋጋት ጋር ተያይዞ የሚፈጠረው ወከባና ጥድፊያ ነው። አንዳንዴ በስፍራው የሚገኙ የሕግ አካላትና ደንብ አስከባሪዎች እግረኞችን በእጅጉ ሲያዋክቡና ሲያመናጭቁ ይስተዋላል። እርግጥ ነው ባልተገባና ባልተፈቀደ የሥራ ቦታ ላይ መራመዱ አግባብ ላይሆን ይችላል። ማንም ግን ይህን እውነት አስቀድሞ እንዲያውቀው ካልሆነ ስፍራው ላይ መገኘቱ ብቻ ጥፋተኛ አያስብለውም።

በድንገት ከቤቱ የወጣ ሰው በክፉና ደግ አጋጣሚዎች ሊራመድ ይችላል። በተለይ በሄዱበት መንገድ አለመመለስ ግድ በሆነ ጊዜ ልምድና ቅልጥፍናው ያላቸው ፈጥነው አማራጭ መውሰዳቸው አይቀርም። ይህን ማድረግ የማይቻላቸው አረጋውያንና አቅመ ደካሞች ደግሞ ለብዙ ችግሮች ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ። አስቀድሞ በቂ የመረጃ ልውውጥ ቢኖር ግን በመጠኑም ቢሆን ችግሩን መቅረፍ በተቻለ ነበር።

ሰፊ የኮሪደር ልማት በሚካሄድባቸው ስፍራዎች የቀድሞዎቹ መሠረተ ልማቶች እየተወገዱ በሌላ የመተካታቸውን ጉዳይ እያየነው ነው። ይህ መሆኑ ዘመናዊነትን፣ ጊዜ ወለድ አዲስነትን በተግባር ለማመላከት እማኝ ሆኗል። ይህኛው በጎነት እንዳለ ሆኖ በጎንዮሽ የሚባክኑ፣ የሚዝረከረኩ ንብረቶች የሌሎች ሲሳይ መሆናቸውን ማየቱ ደግሞ በእጅጉ የሚያስቆጭ ነው።

ብረታ ብረቶችን መለቃቀም መተዳደሪያቸው ያደረጉ አንዳንዶችን ጨምሮ አሁን ላይ የሥራ መደባቸውን ቀይረው ጭምር በለቀማው የሚሰማሩ ጥቂቶች ጠቃሚ ንብረቶችን እየተሻሙ ስለመሆኑ ልብ ይሏል። አሁን ቀድሞ በብረት ተዘግተው የነበሩ የመንገድ ላይ ቱቦዎች በልማቱ ምክንያት ተነስተው መልካቸው ተቀይሯል።

በስፍራው የነበሩ የብረት መዝጊያዎች ታዲያ በቀላሉ ከፈላጊዎቻቸው መዳፍ ለመግባት የሚያግዳቸው አልተገኘም። እነዚህ ከፍተኛ ወጪ የተደረገባቸው ንብረቶች በሌሎች በመተካታቸው ሂደት ቀድሞ የነበረው ሀብት ሁሉ ይጣል፣ ይወገድ ማለት አለመሆኑ ግልጽ ነው።

የአጋጣሚውን ክፍተት የሚሹት አንዳንዶች ግን ሁሌም ዓይንና እጃቸው ፈጣን ስለመሆኑ አይተን ታዝበናል። በኮሪደሩ ልማት እንደተስተዋለው ጠዋት ያለፉበትን መንገድ ሲመለሱ እንደነበረ ላይራመዱበት ይችላሉ። ይህ ፈጣን የሥራ ሂደትም ለብዙዎቻችን አዲስና እንግዳ መምሰሉ አይቀርም። ለአሰሪው አካል ግን ቀድሞ የተያዘ ሃሳብ ነውና የዕቅድ ክንውኑ ሆኖ ይመዘገባል።

ከዚሁ ተያይዞ ግን በመንገዱ ሁሌም እንደልማዳቸው ስለሚራመዱ አቅመደካሞችና አካልጉዳተኞች እንቅስቃሴ ማሰብና መጠንቀቁ የግድ ይላል። አሁን ላይ ለሥራ አመቺነት ሲባል ተከፍተው የሚተው ጥልቅ ጉድጓዶች በተለይ ለእነዚህ ወገኖች ስጋት መሆናቸው አልቀረም።

ከኮሪደሩ ግንባታ በኋላ ቀድመው የነበሩ የመንገድ ላይ አገልግሎቶች ከነጭራሹ ጠፍተዋል ባይባልም በተለይ አነስተኞቹ ሳስተው፣ ተፋዘዋል ለማለት ያስደፍራል። ዛሬ ከቤት ሲወጡ ድንገት ውሃ ጥም ቢያቃጥል፣ ሽንት አጣድፎ ቢይዝ፣ አረፍ ይሉበት አማራጭ አይገኝም።

አይበለውና ከዚህም የከፋ ሕመም ቢኖር መፍትሔው ቅርብ አይደለም። እንደትናንቱ መንገድ ላይ ካሉ መገበያያዎች ዕለታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን የሚገዙበት አማራጭም የለም። እርግጥ ነው የተጀመረው የልማት ይዘት ሰፋ ያለና ውጤቱ የተለየ ነው። አንዳንዴ ደግሞ የግድ ናቸው ለሚያስብሉ አሳሳቢ ፍላጎቶች ጊዚያዊ አገልግሎትን መፍጠሩ ይጠቅማል እንጂ አይከፋም።

እጅግ ፈታኝ ነው ባይባልም የልማቱ ለውጥ የአንዳንድ ሰዎችን አስቸጋሪ ባህሪ ጭምር አሳይቶናል። እንደ ትራንስፖርቱ ሁሉ የኮሪደር ልማቱ የመንግሥት ሠራተኞችን የፐብሊክ ሰርቪስ አጠቃቀም በውስን መልኩ ለውጦታል። አገልግሎቱ ብዙኃኑን ባማከለ ስፍራ እንዲሆን ሲደረግም የአውቶቡሶቹ የቀድሞ መነሻና መድረሻዎች መቀያየራቸው አልቀረም።

ችግሩ እንዲህ መሆኑ ላይ አይደለም። ብዙ ጊዜ ተጠቃሚ ሠራተኞች ወንበር ለማግኘት ፈጥነው ከቢሮ በመውጣት ሰልፍ ይይዛሉ። አሁንም ችግሩ ይህ አይደለም። አሳዛኙ ጉዳይ ሰአታቸውን አክብረው በአግባቡ ተራቸውን በሚይዙት ሀቀኞች ላይ የሚፈጽሙት በደል እንጂ ።

የእነሱ ያለሰአት ወጥቶ መደርደር ሳያንስ ያለአንዳች ይሉኝታ ሌሎች ባልንጀሮቻቸውን ከፊት ያስገባሉ። የመንቀሳቀሻ ሰአት ደርሶ ጉዞ ሲጀመር ታዲያ ሕገወጦቹ ያሻቸውን ወንበር አማርጠው ምቾታቸውን ለማጣጣም የሚቀድማቸው የለም ። አስቀድመው የቆሙት ታማኞች ግን ውስጥም ገብተው መንገዳቸውን እንደቆሙ ይጨርሱታል።

ወዳጆቼ! እንተዛዘብ ከተባለ የኮሪደር ልማቱ አጋጣሚ ሰበብ የሆናቸውን ጥቂቶች ተግባራት ለይቶ መደርደር ይቻላል። ለሁላችንም የሚበጀው ግን ችግሮቻችንን እያስተዋልን ፣ መፍትሄውን ማስቀመጡ ላይ ቢሆን ይመረጣል። ይህ ጊዜ አልፎ ሌላው ታሪክ ሲተካ በሥራዎቻችን መኩራትና ማፈር ይኖራልና።

# ዓለም አቀፍ

## ጄፍ ቤዞስ የዓለማችን ቁጥር አንድ ቢሊየነር ሆነ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ላለፉት ወራት የዓለማችን ቁጥር አንድ ባለጸጋነት ደረጃን ተቆጣጥረው የነበሩት ፈረንሳዊ የፋሺን ኩባንያ ባለቤት በርናርድ አርናውልት በጄፍ ቤዞፍ ተበልጠዋል።

በርናርድ አርናውልት በኩባንያዎቻቸው የቦርድ አመራር ውስጥ ልጆቻቸውን ማስገባታቸውን ተከትሎ የድርጅቶቻቸው የአክስዮን ዋጋ ቀንሷል፡፡

በአርናውልት አዲስ ውሳኔ ምክንያት የ6 ነጥ 7 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ያጡ ሲሆን፤ በአጠቃላይ አዲሱ ዓመት ከገባ ጊዜ ጀምሮ ገቢያቸው እየቀነሰ መምጣቱን ዩሮ ኒውስ ዘግቧል፡፡

በተቃራኒው የአማዞን ኩባንያ መስራች እና ባለቤት አሜሪካዊው ጄፍ ቤዞስ የፈረንጆቹ 2024 ከገባ ጀምሮ 28 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝቷል ተብሏል፡፡

የሀብታቸው መጠንም 205 ቢሊዮን ዶላር የደረሰ ሲሆን፤ ፈረንሳዊ አርናልውት ደግሞ 203 ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም ሌላኛው አሜሪካዊ እና የቴስላ ኩባንያ ባለቤት ኢለን መስክ በ202 ቢሊዮን ዶላር በሶስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል፡፡

የፌስቡክ እናት የሆነው ሜታ ኩባንያ መስራች እና ባለቤት ማርክ ዙከርበርግ ደግሞ በ169 ቢሊዮን ዶላር አራተኛው የዓለማችን ባለጸጋ ናቸው፡፡

ከጎግል መስራቾች መካከል አንዱ የሆኑት ላሪ ፔጅ በ156 ቢሊዮን ዶላር አምስተኛ እንዲሁም የማይክሮሶፍት ኩባንያ መስራቹ እና ባለቤቱ ቢልጌት በ152 ቢሊዮን ዶላር በስድስተኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ችለዋል፡፡



## እስራኤል ጦርነቱን የምታቆም ከሆነ “ሙሉ ስምምነት” ስመፈጸም ዝግጁ መሆኑን ሀማስ ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እስራኤል ጦርነቱን የምታቆም ከሆነ “ሙሉ ስምምነት”ለመፈጸም ዝግጁ መሆኑን ሀማስ ገለጸ።

ሀማስ ይህን መግለጫ ያወጣው እስራኤል በደቡባዊ ጋዛ እያካሄደች ያለውን ጥቃት ባጠናከረችበት ወቅት ነው። ሀማስ ጦርነቱ እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ በተጨማሪ ድርድሮች ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት እንደሌለው ለአደራዳሪዎቹ ገልጿል።

ነገርግን ሀማስ እንደገለጸው፤ እስራኤል ጦርነቱን የምታቆም ከሆነ ግን ታጋቾችን በእስረኞች መለወጥን ጨምሮ “ሙሉ ስምምነት” ለማድረግ ዝግጁ ነው።

በግብጽና በኳታር አደራዳሪነት ሲካሄድ የነበረው የእስራኤል እና የሀማስ የተኩስ አቁም ድርድር እንዳላቸው ሌላኛቸው ያቀረቡትን ቅድመ ሁኔታ ውድቅ በማድረጋቸው እስካሁን አልተሳካም።




“ሀማስ እና የፍልስጤም ኃይሎች ወረራ፣ ከበባ እና የዘር ማጥፋት እየተካሄደ ባለበት ወቅት የተኩስ አቁም ድርድር ላይ አንሳተፍም” ብሏል ሀማስ ባወጣው መግለጫ።

የእስራኤል ጦር በፈጸመው ጥቃት በጋዛ እና በግብጽ መካከል ያለውን የፊላደልፊን መተላለፊያ ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሯል።

የፊላደልፊ ኮሪደር በተደጋጋሚ የጦር መሳሪያ ለማስገባት ለሚጠቀምበት ሀማስ እንደዋና የህይወት አስትንፋስ ሲያገለግል ነበር። አሁን ላይ በፊላደልፊ መተላለፊያ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እየተቆጣጠረ ያለው የእስራኤል ጦር ነው።

ጋዛን ከግብጽ ጋር የሚያገናኘውን የየብስ መተላለፊያ እስራኤል እስካሁን በቀጥታ ሳትቆጣጠረው ቆይታለች።

የእስራኤል ታንኮች ሰሞኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ራፋ መሀል ከተማ ሰንጥቀው ገብተዋል። እስራኤል ራፋን ለማጥቃት የወሰነችው የሀማስ የመጨረሻ ምሽግ ይገኝባታል በሚል መሆኑን መግለጿ ይታወሳል።

እስራኤል፣ ሀማስ ባለፈው ጥቅምት ድንበር በመጣስ ከባድ የተባለ ጥቃት ማድረሱን ተከትሎ እየፈጸመች ባለው ጥቃት እስካሁን በርካቶች መገደላቸውን የጋዛ ጤና ሚኒስቴር አስታውቋል።

## ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# «ኦብሰሲቭ ኮምፐልሲቭ ዲስኦርደር»

### ክፍል አንድ

«ኦብሰሲቭ ኮምፐልሲቭ ዲስኦርደር» ምንድን ነው? ከነባራዊ ዓለም ጋር የማይጣጣም በጎ ተጽዕኖ የሌለው፤ አሉታዊ ስሜትን የሚፈጥር፤ የሚያሸማቅቅ፤ የሚያስፈራ፤ የሚያስጨንቅ አፍራሽ ሃሳብ በተከታታይና በተደጋጋሚ በእዝነ ህሊናው በማሰብና ለዚህም ምላሽ ለመስጠት በመጣጣሩ ምክንያት የሚፈጠር የጭንቀት ዓይነት ነው። ኦብሰሲቭ ኮምፐልሲቭ ዲስኦርደር ዘርን፣ ጾታን፣ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ ባሕልንና የኢኮኖሚ ደረጃን ሳይለይ ህብረተሰቡን በመላ የሚያጠቃ ነው።

ይህን መሰል የተዛባና ፍጹም አሉታዊና አፍራሽ ተጽዕኖ ያለውን ሃሳብ የሚያስበው ሰው በራሱ የሚቀበለው አይደለም። በገዛ ሃሳቡ ከመሸማቀቁ፤ ከመፍራቱ ከመጨነቁም ባሻገር ሃሳቡን በራሱ የሚቀበለው አለመሆኑ ተጠቂው ከራሱ ጋር ግጭት ውስጥ እንዲገባ ምክንያት የሚያጣራ ይሆናል።

የዚህ ዓይነቱ የአስተሳሰብና የስሜት ችግር በሰውየው ላይ ከታየ ኦብሰሲቭ ኮምፐልሲቭ ዲስኦርደር ((Obsessive compulsive disorder) ለተባለ የአዕምሮ ሕመም እንደተጋለጠ መረዳት ይቻላል። የኦሲዲ ችግር ያለበት ሰው አእምሮው ሌላ ነገር ማሰብ እስኪሳነው ድረስ የማይፈለጉ አስፈሪና አሳፋሪ በሆኑ አፍራሽ ሃሳቦች ተሞልቶ ቀኑን በሙሉ በጭንቀት ይገፋል።

«ኦሲዲ» በችግሩ ተጠቂ ዘንድ የማይፈለግና ለመቆጣጠር የሚያስቸግር ሃሳብ በእዝነ ህሊናው እየተመላለሰ መጨነቁና ይህንኑ ችግር ለማስወገድም ተፈጥሮዓዊ የአዕምሮው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ምላሽ የመስጠት ዑደት ያለው አዕምሮን በጭንቀት የሚያውክ የጤና ችግር ነው።

የኦሲዲ የራሱ መገለጫ ባህሪያት አሉት። ኦሲዲ በሁለት መሠረታዊ ነገሮች ይገለፃል። እነዚህም ኦብሴሽንና ኮምፐልሽን በመባል ይታወቃሉ። የአሜሪካን ሳይካትሪስት አሶሴሽን ሁለቱን ነገሮች እንዲህ ሲል ያብራራቸዋል።

የመጀመሪያው ኦብሰሺን ሲሆን፤ የችግሩ ተጠቂ የሆነው ሰው የማይፈልጋቸውና የማይወዳቸው ነገር ግን የማይቆጣጠራቸው እና የማያቆማቸው ሃሳቦችና ምስሎች በአዕምሮው ውስጥ ተደጋግመው ያለማቋረጥ መከሰት፣ በአእምሮው የሚመላለሱበት እነዚህ ሃሳቦችና ምስሎች በነባራዊ ዓለም ያሉ ችግሮች ተባብሰውና ተጋነው የታዩበት ብቻ ሳይሆን የችግሩን ተጠቂ እውነተኛ አስተሳሰብን የማይወክሉ መሆኑ፣ የችግሩ ተጠቂ የሆነው ሰው እነዚህን ኦብሰሺን ሃሳቦች ወደ አእምሮው የሚመጡትን ለመከላከልና ለመጫን የሚሞከር መሆኑ ነው።


አብዛኛው ሕጻን ያልሆነ የኦሲዲ ችግር ተጠቂ በኦብሰሺን ሃሳብ ውስጥ ባልሆነበት ጊዜ እነዚህ ምስሎች ድንገት የተፈጠሩ እንጂ የራሱ ትክክለኛ ማንነት መገለጫ ሃሳብ አለመሆናቸውን የሚያውቅ መሆኑ ነው።

ሁለተኛው ኮምፐልሺን ሲሆን፤ የኮምፓልሺን ባህርያት ደግሞ ኦብሴሺን በአእምሮ በሚከሰትበት ጊዜ ያለማቋረጥ የተግባራዊና አእምሯዊ ምላሽ በመስጠት የሚደረግ ኦብሴሺንን የመከላከል ተፈጥሯዊ ተግባር ነው። ይህ ምላሽ በጊዜው የተከሰቱ ኦብሴሺንን ለማቃለል ወይም የተፈራው ነገር እንዳይከሰት ለመከላከል የሚወሰድ ርምጃ ሲሆን በጣም የተጋነነና በተደጋጋሚ የሚደረግ ነው።

በአጠቃላይ የኦሲዲ ተጠቂ ሊያስበው፤ ሊፈጽመውና ሊደርስበትም የማይፈልገው ሃሳብ ወደ አእምሮው በመምጣትና ይህንን አስጨናቂ ሃሳብም ለመከላከል ከራሱ ጋር ከሚያደርገው የማያባራ ትግል ጋር በተያያዘ የሚፈጠር የጭንቀት ስሜት ውስጥ ተውጦ የሚሰቃይ ሰው ነው።

ከዚህም በተጨማሪ በኦሲዲ ለሚፈጠረው ኦብሴሺን የሚታይም ሆነ የማይታይ አጸፋዊ ምላሽ (ኮምፓልሺን) ይኖራል። በሌላ በኩል በተጠቂው አእምሮ የሚመላለሰው ሃሳብ ወይም ምስል የኦሲዲ ኦብሰሺን ካልሆነ (እየተፈለገ የሚታሰብ ከሆነ) መጨነቁ ቢኖርም ግን ከላይ በተገለጻው መልኩ ይህን ሃሳብ ለመከላከል የሚደረገው ኮምፓልሺን አይኖርም።

ኦሲዲ በራሱ ኡደት አለው። በኦሲዲ የጭንቀት ችግር ውስጥ ኦብሰሺንና ኮምፓልሺን እርስ በእርሱ ተደጋጋፊ ናቸው።




በስዕሉ ከላይ እንደሚያመለክተው የኦሲዲ ተጠቂው በኦብሴሺን ምክንያት ከሚፈጠረው ጭንቀት ጊዚያዊ ምላሽ በመስጠት (ኮምፓልሺን) እፎይታ የሚያገኝ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ተጠቂውን ለሌላ ኦብሴሺንና ጭንቀት እንዲጋለጥ ያደርገዋል። ከችግሩም ለመውጣት ሃሳቡን በመጫንና ጭንቀቱን ለመገላገል ምላሽ በመስጠት በተጠቂው በኩል የሚወሰደው ርምጃ የችግሩን መጠን አባብሶ ከዚያም አልፎ ችግሩ አቅም ፈጥሮ እየከረረ በመሄድ በተጠቂው ውስጥ የችግሩ ዑደት ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ያደርገዋል።

## ከአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# የቢሮው ስልጣንና ተግባር

በባለፈው እትማችን በከተማ ፕላን ምንነት፣ በከተማ ፕላን ዝግጅትና የነዋሪዎች ተሳትፎ፣ በከተማ ፕላን ዓይነቶችና ተዋረድ እና በስፓሻል ፕላን ዝግጅት ዘርፍ ዋና ዋና ተግባራት ዙሪያ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ ከኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ያገኘነውን መረጃ ይዘን መቅረባችን የሚታወስ ነው:: በአሁኑ እትማችን ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ቢሮ ስልጣንና ተግባር ምን እንደሆኑ እናስነብባችኋለን:: መልካም ንባብ::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ 20(ሃያ) የተናጠል ስልጣንና ተግባራት አሉት:: እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል::

1. የከተማ አስተዳደሩን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ አፈፃፀም ይከታተላል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤ ይገመግማል፤ ይመዝናል፤ ደረጃ ያወጣል፤ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
2. የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. የአካባቢ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ ያፀድቃል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
5. የፕላን ዝግጅትና አተገባበር የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፤ ያሰራጫል፤
6. በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት የሕዝብ ተግባቦትና ሥርጸት ሥራዎችን ያከናውናል፤ ተደራሽ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ ሰነድና ሥርጭት ቋት ያደራጃል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤
7. የከተማው አስተዳደር ከተማ ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤
8. በሚያመነጫቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ከተማ ፕላኖች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳዮች እንዲካተቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
9. የከተማ ፕላን በሚጥስ ማናቸውም አካል ላይ በሕግ መሠረት ርምጃ ይወስዳል፤ ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
10. ከተማ ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስችል መሠረታዊ የከተማ ካርታ ከሳተላይት ምስሎች ከሀገሪቱ ጂኦዴቲክ ካርታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤
11. የፀደቀ ፕላን በሕግ መሠረት እንደየአግባቡ ያሻሽላል፤ ያጣጥማል፤
12. የፕላን፣ የዲዛይንና የግንባታ ፈቃድ ደረጃዎችን አፈፃፀም የሚመለከቱ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት እንዲያቀርቡ የመስክ ምልከታ እና ጥናት በማድረግ ሪፖርት ያቀርባል፤
13. የከተማውን ዝርዝር የሥነ-ሕዝብ ጥናትና ትንበያ ያካሄዳል፣ ውጤቱንም ለከተማው አስተዳደር አካላትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ በከተማው ውስጥ ይፈፅማል፤ ያስፈፅማል፤
14. የከተማውን ዓመታዊ አጠቃላይ የምርት ዕድገት ለማስገኘት የሚያስፈልገውን የካፒታልና የምርታማነት ዕድገት መነሻዎችን ይገምታል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤
15. የከተማውን የምርት ዕድገት ግቦች የፖሊሲና የሕግ ሪፎርም ርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንትና የወጪና የገቢ ንግድ ከተማ አቀፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
16. ከአጠቃላይ ከተማ አቀፍ ምርት የኢንዱስትሪ፣ የአገልግሎት ዘርፎችና የከተማ ግብርና የተናጠል ድርሻን ይለያል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤
17. የከተማውን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች መካከል የሚኖረውን የግብዓት አቅርቦት ፍላጎት ይተነትናል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤
18. ከሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማድረግ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የፖሊሲና የሕግ ሪፎርም ርምጃዎችን የሚዘረዝር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ የዘርፍ ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
19. ተዋረዳዊ አደረጃጀት ያላቸው የከተማው አስተዳደር አጠቃላይ ፕላን ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ በየበኩላቸው የሚፈፅሟቸውን ተግባራት የሚያሳይ የተቀናጀ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፕላን አፈፃፀም መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
20. በጸደቀው ስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በአስፈጻሚ ተቋማት የሚከናወኑ ነባርና አዲስ የካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድን አፈፃፀም ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል::

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ህልምን የማወቅ መንገዶች

አስናቀ ፀጋዬ

ህልሙን ያወቀ ሰው የቱ ጋር እንዳለ ያውቃል። ወዴት እንደሚሄድ ይረዳል። የሆነ ቀን ተነስቶ ‹‹እኔ በቃ እድሜዬ ዝም ብሎ አለፈ! ጊዜዬ ዝም ብሎ ነጎደ!›› አይልም። ወዴት እንደሚሄድ ያውቃል። መድረሻና መነሻውን ያውቃል። መንገዱን ጀምሮታል። ህልም አለዋ! ለምሳሌ በልጅነታችን በጣም ደስ የሚለን የማንረሳው ጊዜ የበዓል ሰሞን ነው። በዓል ሲደርስ ጨዋታው፣ ደስታው ወደር የለውም። ልብስ ይገዛልናል፣ የምንፈልገው ነገር ይደረግልናል። አንረሳውም። ካደግን በኋላ ግን በዓል ትዝም አይለንም። አናጣጥመውም።

ለምሳሌ የዛሬ ዓመት ያከበራችሁት በዓል ትዝ ይላችኋል? ምንም ትዝ አይላችሁም። የዛሬ ሃያና ሰላሳ ዓመት ያከበራችሁትን በዓል ግን በደንብ ታስታውሱታላችሁ። ትልቅ ስትሆኑ በዓል ትርጉም አይኖረውም። ከበዓል በላይ ግን ትርጉም የሚሰጣችሁ ህልም ነው። ለልጅነት ትርጉም የሚሰጠው በዓል ነው፤ ለትልቅነት ደግሞ ህልም ነው።

ህልም ሲኖርህ ብዙ ነገርህ ይቀየራል። ለምሳሌ ማንነትህ ይቀየራል። ህልም ጥቅሙ ህልሙን አሳደህ እንድትይዘው አይደለም። አንተ እንድትቀየር ነው። ለህልሙ ስትል የሆነ የምትለውጠው ማንነት አለ። ውስጥህ የሆነ ነገር ይገነባል። ሚሊየር መሆን እኮ ጥቅሙ ሚሊዮን ብሩ አይደለም። ሚሊየን ብርማ ሎተሪ የደረሰው ሰውም ያገኘዋል። ከዓመታት በኋላ ግን ከስሮ ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። ግን ሚሊየነር መሆን ጥቅሙ አንተ ሚሊየነር ለመሆን ስትል የጊዜ አጠቃቀምህ፣ የገንዘብ አያያዝህ፣ ከሰዎች ጋር ያለህ ግንኙነት ይቀየራል።

ለምሳሌ አይታችሁ ከሆነ የከሰረ ነጋዴ እንደምንም ብሎ ወደ ገንዘቡና ወደ ቢዝነሱ ይመለሳል። ለምን? የረገጠውን ደረጃ ያውቀዋል። ዝም ብሎ አየር ላይ ፊጥ ብሎ አልወጣም። ደረጃውን ወጥቷል። መንገዱን ተጉዞታል። ህልም ሲኖርህ አንተ ትቀየራለህ። ማንነትህ ይቀየራል። አመለካከትህ፤ ለነገሮች ያሉህ እይታ ይቀየራል። ህልም አለሃ! የሰው ልጅ ለህልሙ ሲል ራሱን መቀየሩ አይቀርም።

ህልም ሲኖርህ ደስ የሚለው ነገር አንተ ትቀየራለህ። ህልም አቅማችንን እንድንጠቀም ያደርገናል። ከውስጣችን የሚወጣ የሆነ ኃይል አለ። ዓላማና ህልም ሲኖርህ ትባንናለህ፤ ትነቃለህ። የምትንቀውና የምትበልጠው ሰው በጣም እየተቀየረ ከሆነ የሆነ የሚያሮጥ አላማ ይዟል ማለት ነው። የሆነች ህልም ይዟል ማለት ነው። ሌላውን ተውትና ቋንቋ መልመድ ትፈልጋላችሁ እንበል። አረበኛ፣ እንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛ... ወዘተ ሊሆን ይችላል። ግን የቋንቋ ትምህርት ቤት ገብታችኋል አልቻላችሁም። ሞክራችኋል፤ ብዙ ነገር አልተሳካላችሁም። ‹‹እኔ ለምንድን ነው ግን ቋንቋ የማይገባኝ›› ልትሉ ትችላላችሁ። ህልም የላችሁም።

ለምሳሌ ግን ‹‹አስር ሺ ዶላር ይከፈልሃል ቶሎ ቋንቋውን ቻልና ትቀጠራለህ›› ብንባል ደሞዛችን 1 ሺ ዶላር ወይም ከዛም ያነሰ ከሆነ ለዛ ገንዘብ ስንል እንባንናለን። በአንድ ጊዜ ከአልበርት አንስታይን በላይ አይምሯችን ይመጥቃል ቋንቋዋን ለመቻል። ለምን? ደሞዝ አላታ! ህልም አለና! አንዳንድ ጊዜ አይታችሁ ከሆነ አረብ ሀገር ሳይሄዱ ኢትዮጵያ ተቀምጠው የአረብኛ ፊልም ለማየት ሲሉ አረብኛ ቋንቋ የቻሉ ሰዎች የሉም? በርግጠኝነት ብዙ ሰው ታውቃላችሁ። አብዛኛዎቹ ሰዎች እንግሊዘኛ ቋንቋስ የሚችሉት እንዴት ነው? ዘፈን ለመስማት ሲሉ፣ የሚወዱትን ፊልም ለማየት ሲሉ ነው።

አያችሁ! በትንሽ ነገር እንኳን ህልምና አላማ ሲኖረን አቅማችንን እንጠቀማለን። ስለዚህ ወዳጄ! ከማንም አንሰህ አይደለም፤ ህልም ስላላስቀመጥክ ነው። ጥልቅ መሻት ሲኖርህ አቅምህን የምትጠቀመው ወደህ ሳይሆን ተገደህ ነው። ምክንያቱም ልሞክር አትልም። ማሳካት አለብኝ ነው የምትለው። ውሃ ቢጠማህ ‹‹እንደው ካገኘው ልሞክር ካላገኘው ችግር የለውም›› አትልም። ‹‹መጠጣት አለብኝ›› ትላለህ ለመኖር ስትል። ህልም



እንደዛ ነው። ጥልቅ መሻት እንደዛ ነው። አቅሜን መጠቀም አለብኝ ትላለህ። ህልማችንን ለማወቅ የሆነ ደረጃ ድረስ ለመምጣት ግን እነዚህ ተከታዮቹ ሶስት ነጥቦች ላንተ ወሳኞች ናቸው።

የመጀመሪያው ደስታ የሚሰጥ፣ ጥሩ ስሜት የሚፈጥርና የሆነ ጊዜ አድጎ ሞያ ሊሆን የሚችል ተግባር/passion/ ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ሰው በቤቱ የሆነ ምግብ ሰርቶ፣ ኬክ አዘጋጅቶ ‹‹አንተ እንዴት ይጣፍጣል፤ አንተማ የሆነ ሬስቶራንት ብትከፍት፣ ምግብ ቤት ብትከፍት›› የምትሏቸው ሰዎች አሉ። በቃ ማብሰል ለነዚህ ሰዎች ደስታ የሚሰጣቸው ነገር ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰው ደግሞ የሂሳብ ጥያቄ ሲሰራ የሆነ ጨዋታ የሚጫወት ይመስላል። በጣም ያስደስታል። አንዳንዱ ደግሞ ሲናገር አፍ የሚያስከፍት አለ። ይህም ፓሽን ነው። አያችሁ ይህ ደስ ብሏሁ የምታደርጉትና በፍቅር የምትሰሩት ነገር ነገ አድጎ ሞያ ልታደርጉት የምትችሉት ነገር ይሆናል።

ሁለተኛው ደስ ብሏችሁ የምታደርጉት ነገር ትንሽ አደግ ብሎ ገንዘብ ማምጣት ሲጀምር ሞያ / profession/ ይሆናል። ለምሳሌ ያ ምግቡ በጣም ቆንጆ ነው የምትሉት ሰው ወይም የምትሏት ሴት ተቀጥራ ሼፍ ብትሆን፣ ምግብ አብሳይ ብትሆን አሁን ሞያዋ ገንዘብ እያመጣላት ነው። ስለዚህ ሞያ ሆነ ማለት ነው። ያ ሒሳብ በጣም የሚሰራው ልጅ የሒሳብ መምህር ቢሆን ወይም ተመርቆ ኢንጂነር ቢሆን አሁን ሞያተኛ ሆነ ማለት ነው። አያችሁ! በነፃ ብትሰሩት እንኳን የሚያስደስታችሁ ነገር ገንዘብ ሲያመጣ ሞያ ይሆናል።

ሶስተኛውና በጣም ወሳኙ የመኖር አላማ/ purpose/ ነው። አሁን ከገንዘብ ከፍ ያለ ነገር ሲያመጣላችሁ ነው የመኖር አላማ የሚባለው። ያቺ ምግብ የምታበስለዋ ሴት ‹‹እኔ የከተማው ሕዝብ ሁሉ መመገብ እፈልጋለሁ በሬስቶራንቴ›› ብትል ትልቁ አላማዋ ነው። ግዙፍ የመኖር አላማ ሆነ። ያ የሒሳብ መምህር ወይም ኢንጂነር ‹‹አብዛኛውን ሰው ሒሳብ እንዲወድ አደርገዋለሁ›› ካለ ከገንዘብ በላይ ትልቅ ህልም አስቀመጠ። ትልቅ አላማ አስቀመጠ። በነገራችን ላይ ዓለምን የቀየሩ ሰዎች ተለቅና ገዘፍ ያለ ህልም ስላላቸው ነው።

ህልም እንዲኖርን የግድ ሞያዬን አላወኩትም ብለን መጨነቅ የለብንም። ትልቁ ቦታ አልተያዘም። ሁሉም ሰው የሚሻማው መሃል ላይ ላለው ነው። አይታችሁ ከሆነ እታች ያለውን ሁሉም ይንቀዋል። መሃሉን ሁሉም ይፈልገዋል። ትልቁን ይፈሩታል። ለምሳሌ አካውንታንት ለመሆን፣ ሽያጭ ሠራተኛ ለመሆን ወይም ደግሞ የሆነ ቦታ ለመቀጠርና ፀሐፊ ለመሆን የሚፈልገው ሰው በጣም ብዙ ነው። ብዙ ሺ ሰው ተሰልፎ ታያላችሁ። ሥራ አስኪያጅ ለመሆን የሚወዳደረው ግን በጣት የሚቆጠር ነው። ለምን መሰላችሁ? አብዛኛው ሰው ትልቁን ነገር ማሰብ ይፈራል። ደስ የሚለው ግን ትልቁ ቦታ አልተያዘም።

ስለዚህ ወዳጄ! ለሰማዩ ትወረውራለህ፤ ቢያንስ እኮ ጣራውን ትነካለህ። ህልም አሩጠን የምንይዘው ሊሆን ይችላል። ወይ ደግሞ እየኖርን የምንገልጠውም ህልም አለ። ምን መሰላችሁ፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ዶክተር መሆን እፈልጋለሁ ወይ ኢንጂነር መሆን እፈልጋለሁ ወይም ደግሞ የሆነ ነገር ማሳካት እፈልጋለሁ፣ የካምፓኒ ሥራ አስኪያጅ መሆን እፈልጋለሁ ካለ የሆነ ቀን የሚያሳካው፣ አሩጦ የሚይዘው እንደሆነ ያስባል። አንዳንድ ሰው እንደዚህ ዓይነት ህልም ያወጡና ልክ ሲያሳኩት የሕይወት ትርጉም ይጠፋባቸዋል። ‹‹ሃብታም መሆን እፈልግ ነበር ሆንኩ፣ ማግባት እፈልግ ነበር አገባሁ፣ ዶክተር መሆን እፈልግ ነበር ሆንኩ ግን ትርጉም አጣሁ›› ይላሉ።

ህልም ደግሞ የምትኖረውን ማድረግ ነው። በቃ እኔ የምደሰተው ሰዎችን ስረዳ ነው፣ የሰዎችን ሕይወት ስቀይር ነው፣ የማይቆም ህልም አለኝ ስትል ደግሞ የምታሮጠው ብቻ ሳይሆን የምትኖረው ህልም ይኖርሃል። በመጨረሻ ‹‹ህልም የለኝም እኮ፣ ግራ ገብት ብሎኛል፣ እንደው ህልሜን ባውቀው›› የሚሉም አሉ። ህልም የለኝም የሚል ሰው እነዚህን ሶስት ጠቃሚ ነገሮች ቢያደርግ ህልሙን የማግኘት እድሉን ያሰፋል።

የመጀመሪያው እጅህ ላይ ላለው መታመን ነው። አሁን እየተማርክ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ወጥረህ በደንብ ተማር። ሥራ እየሰራህ ሊሆን ይችላል። አሁን ያለህበት የተቀጠርክበት ቦታ ላይ በትጋት ሥራ። ህልም ለጠንካሮች የሚሰጥ የፈጣሪ ፀጋ ነው። በጣም ስትጠነክር፣ ስትበረታ አሁን እንዲህ ደግሞ ባደርገው ብሎ አይምሮህ ራሱ ይነግርሃል። ፈጣሪህ ራሱ መንገድ ይጠቁምሃል። ለምን? እጅህ ላይ ላለው ታምነሃላ! አያችሁ በጣም ስንጠነክር ሕይወት ትገባናለች፤ አዲስ ነገር እንረዳለን። በቃ አሁን እየበረታሁ ነው እንዲህ ባደርግ እንላለን።

ሁለተኛው የራስን ሪከርድ ለመስበር መጣር ነው። መቼም ሁላችንም የራሳችን ሪከርድ አለን። ገንዘብ የማስቀመጥ ሪከርድ ሊኖረን ይችላል። ለምሳሌ 10 ሺ ብር የማስቀመጥ ሪከርድ ያለው ሰው 100 ሺ ብር ለመድረስ መሞከር፣ 100 ሺ ያስቀመጠ ሚሊዮን ለመድረስ፣ ሚሊዮን ያስቀመጠ መቶ ሚሊዮን፣ ቢሊዮን...፣እያለ የራሱን ሪከርድ ለማሻሻል መጣር። በእውቀትም ሪከርድህን መስበር ትችላለህ። እኔ የተማርኩት ዲፕሎማ ነው ካልክ እስከ ዲግሪ ማስኬድ፣ ህልምህ ከትምህርት ጋር የሚገናኝ ከሆነ ለምን ማስተርስ አልይዝም፣ ለምን ዶክትሬት ዲግሪ አልይዝም፣ ለምን ፕሮፌሰር አልሆንም፣ ለምን እንዲህ አላደርግም እያልክ የራስህን ሪከርድ ማሻሻል መጨመር አለብህ።

በቃ አሁን ተቀጥሬ የምሰራበት ቦታ ላይ ዝም ብዬ አካውንታንት ልሆን እችላለሁ ከዛ ግን ሱፐርቫይዘር እሆናለሁ፣ ቀጥሎ የብራንች ማናጀር፣ ከዛ በኋላ የአጠቃላይ ማናጀር እሆናለሁ ማለት አለብህ። አየህ! የራስህን ሪከርድ እየሰበርክ ህልምህን ማሳደግ ትችላለህ። ኃይሌ ገብረስላሴ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ የደረሰው እኮ ሪከርዱን እያሻሻለ ነው። እንዴት? ከላችሁ መጀመሪያ ወንድሜን መቅደም አለብኝ ብሎ ተነሳ። ሁሌም በጠዋት እየተነሳ የመሄደው ጉዞ ረጅም ነው። ወንድሜን መቅደም አለብኝ ብሎ ሲቀድመው፣ ከትምህርት ቤቴ፣ ከአካባቢዬ፣ ከክልሌ፣ ከሀገሬ፣ ከዓለም ሲል የራሱን ሪከርድ እየበጣጠሰ ምን ያህል ስኬታማ እንደሆነ ታውቃላችሁ። አንተም ሪከርድህን መስበር የምትጀምረው ከራስህ ነው። ስለዚህ የራስህን ሪከርድ አሻሽል። የእውቀት፣ የገንዘብ፣ የሥራ ሪከርድህን አሻሽል። ያኔ ህልም ይኖርሃል።

ሶስተኛውና የመጨረሻው ሁሌም ራስን መጠየቅ ነው። ‹‹የኔ ትልቁ ህልም ምንድን ነው?›› በል። በነገራችን ላይ በዚህ ዓለም የትኛውንም ጥያቄ ከጠየቅን መልስ አለው። ግን ሳንሰለች ደጋግመን መጠየቅ አለብን። እኛ ጥያቄውን ከጠየቅን በኋላ እጃችን ላይ ላለው መታመን ስንጀምር አይምሯችን በራሱ ሰዓት ማሰብ ይጀምራል። አንተ ተኝተህ እሱ ያስባል። ያንተን ህልም እሱ ይጨነቅበታል። ከየትም ቆፍሮ ህልምህ እንዲህ ነው ሊልህም ይችላል።

ስለዚህ ህልሜ ምንድን ነው፣ እኔ ምንድን ነው የምሆነው ብለህ መጨነቅ የለብህም። እጅህ ላይ ላለው ታመን። መሥራት ያለብህን ነገር ወጥረህ ሥራ። የራስህን ሪከርድ አሻሽል። በመጨረሻ ደግሞ አይምሮህን ደጋግመህ ጠይቀው። ህልምህ ምንም ሊሆን ይችላል። አሁን ስታወራው አጠገብህ ያሉ ሰዎች ሊስቁብህም ይችላሉ። እንደውም ጥሩ ህልመኛ ነህ ማለት ነው ሰው ከሳቀብህ። ለምን? አይቻልም የሚባለውን ነገር ለማድረግ ራሱ አቅምህን እንድትጠቀም ያደርግሃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ በሰላማዊና ሕጋዊ አማራጮች በቀይ ባሕር የመጠቀም መብቷን ለማረጋገጥ አበክራ ትሠራለች!

ኢትዮጵያን ያለ ቀይባህር ፤ ቀይባህርንም ያለኢትዮጵያ ማሰብ ከባድ ነው። ኢትዮጵያ በታሪኳ ያሳለፈቻቸው መነሳቶችም ሆነ መውደቅ በቀጥታ ከቀይ ባህር ጋር ይያያዛል። ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ላይ የበላይነት ይዛ በቆየችባቸው ዘመናት ገናና እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆና ቆይታለች። በአንጻሩ ከቀይባህር አካባቢ ከተገለለች በኋላ አቅሟ የደበዘዘ፣ ኢኮኖሚዋ የተዳከመ እና ሰላም የራቃት ሀገር ለመሆን በቅታለች።

ኢትዮጵያን ከቀይባህር የማራቁ ስልት ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ነው። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የአረብ እና የቀጣናው ሀገሮች ኢትዮጵያን ከነጭራሹ ከአካባቢው ገሸሽ የሚያደርጉ ስምምነቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል። የቀይ ባህር ጥምረት (Red sea Alliaince) ወይም ደግሞ የጂቡቲ የሥነ ምግባር ደንብ (Code of conduct) እና የቀይ ባህር ደህንነት ተለዋዋጭነት መድረክ (Red sea security dynamics forum)ን የመሳሰሉ ኢትዮጵያን ያገለሉ ስምምነቶች ተመስርተዋል።

በተለይም ኢትዮጵያንና እስራኤልን ያገለለ የቀይ ባህር ደህንነት ተለዋዋጭነት መድረክ (Red sea security dynamics forum) ተመስርቷል። ይህ መድረክ ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር ጋር ያላትን ትስስር የካደና ከነጭራሹም የዘነጋ ነው። ይህ እና ሌሎች ከላይ የተፈረሙት ስምምነቶች ኢትዮጵያውያን በቀይ ባህር ላይ ያላቸውን መብቶች በአንድነት ለማስከበር እስካልተነሱ ድረስ ሀገሪቱን ከቀይ ባህር የማራቁ ጉዳይ የበለጠ እየተጠናከረ እንደሚሄድ አመላካች ነው ።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ወደብ አልባ ከሆኑ 16 ሀገራት አንዷ ብትሆንም ወደብ አልባ የሆነችባቸው አመክንዮዎች ግን ታሪካዊም ሆነ ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው ናቸው። ኢትዮጵያ በውሃ ሀብት በዓለም ላይ ከሚታወቁት ሀገራት አንዷ ስትሆን አፈጣጠሯም ከውሃ ጋር የተያያዘ ነው። የዓባይ ወንዝ መነሻና በቀይባህር ዳርቻ መገኘቷ የዚሁ አመክንዮ ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የባህር በር ከሌላቸው 44 ሀገራት አንዷ ነች። በአፍሪካም ካሉት 16 የባህር በር ከሌላቸው ሀገራትም ተርታ ትሰለፋለች። ሆኖም ኢትዮጵያ ከእነዚሁ ሀገራት የሚለዩዋት በርካታ ነገሮች አሉ። አንደኛው የሕዝብ ቁጥሯ ነው። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ 126 ሚሊዮን ደርሷል። በአጠቃላይም በኢትዮጵያ የሚኖረው ሕዝብ የባህር በር የሌላቸውን ሀገራት ሕዝብ 1/3ኛውን ይሸፍናል።

ይሄንን የሚያህል ሕዝብ ይዞ የባህር በርና ወደብ የተነፈገ ሀገር ደግሞ የለም። ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ኢትዮጵያ በባህር በር የተከበበች ሀገር መሆኗ ነው። በሴራ እና በተሳሳተ ትርክት ከቀይ ባህር እንድትርቅ ከመደረጓ በስተቀር በአፈጣጠሯ ለቀይ ባህር የቀረበ ነው። በሦስተኛ ደረጃ በታሪክም በቀይ ባህር ላይ ለዘመናት የበላይ ሆና መቆየቷን የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ያሏት ሀገር ናት።

ስለዚህም ኢትዮጵያ በግፍ ከይዞታዋ እንድትነቀል ከመደረጓ ውጪ ባለቤትነቷን የሚከለክላት አንዳችም ዓለም አቀፍ ሕግ የለም። ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችበትም ሆነ ከቀይ ባህር እንድትወገድ የተደረገበት አካሄድ ምንም አይነት ሕጋዊ መሠረት እንደሌለው ብዙ ምሁራን ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንድትርቅ የተደረገው 1900፤ 1902 እና 1908 ከቅኝ ገዥዎች በተደረጉ ውሎች አማካኝነት ነው። እነዚህ ውሎች ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት መመስረቻ ቻርተር ሕጋዊነታቸውን አጥተዋል። ስለዚህም ኢትዮጵያ የባህር በርም ሆነ ወደብ እንዳታገኝ የሚከለክላት አንዳችም ዓለም አቀፍ ሕግ የለም።

ይህን የተረዳው መንግሥትም ኢትዮጵያ ፊቷን ወደ ቀይባህር እንድታዞር አድርጓል። የባህር በር ጥያቄን ዋነኛ ብሔራዊ አጀንዳ እንዲሆን በመሥራትም ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያ ወደብ እና ባህር አልባ በመሆኗ እያስከተሉባት ያሉ ጉዳቶች እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በቁጭት እንዲነሳ አድርጎታል።

በተለይም ወደብ አልባ ሆና በዘለቀችባቸው ያለፉት 33 ዓመታት በኢኮኖሚም ሆነ በድህነት ዘርፍ በርካታ ጉዳቶችን አስተናግዳለች። በየዓመቱ ለወደብ ከምታወጣው 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር በተጨማሪ የሉአላዊነት አደጋ ባጋጠማት ወቅት እንኳን ራሷን ለመከላከል የሚያስችሏትን ስትራቴጂክ የሆኑ መሳሪያዎችን በምስጢር ለማስገባት ስትፈልግ የግድ የወደብ አከራዩን ሀገር መልካም ፍቃድ ማግኘት ይጠበቅባታል።

ስለዚህም ኢትዮጵያ ለዘመናት ሉአላዊና ነጻ ሀገር መሆኗ የታወጀ ቢሆንም በባህር በርና በወደብ አልባነቷ ምክንያት ለዘመናት ይዛ የቆየችው ነጻነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። ስለዚህም የባህር በር ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን የህልውና ጥያቄም ጭምር መሆኑን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተረድቷል።

ታኅሣሥ 23 ቀን 2016 ከራስ ገዟ ሶማሊላንድ ጋር የተደረሰው ስምምነትም የኢትዮጵያን ተስፋ ያለመለመ እና ኢትዮጵያን ወደ ታሪካዊ የቀይባህር አካባቢ እንድትመለስ ጥርጊያ መንገድ የከፈተ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሙሉ ልብ የደገፈው ነው። ስምምነቱም ኢትዮጵያ በቀጣይ ሰላማዊ በሆነ መንገድ የባህር በር እና የወደብ አማራጮችን እንድታሰፋ በር የከፈተ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፦ 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የፈጠራ ሥራ፣ ጥናትና ምርምር ከመደርደሪያ ወርዶ እንዲተገበር

ኃይለማርያም ወንድሙ

የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ተማሪዎችን ከማስተማር ጎን ለጎን ጥናትና ምርምር በማድረግ እና ለኅብረተሰቡ ሥራ አጋዥ የሆኑ አዳዲስ ፈጠራዎች ጊዜ እና ጉልበትን የሚቆጥቡ ሥራዎች ይሠራሉ።

ነገር ግን የሚወጡ ጥናትና ምርምሮች ተማሪዎቹ ለመመረቂያ ጽሑፍ ከማሟላት በዘለለ ኅብረተሰቡን ሊያግዙ በሚችሉ መልኩ ሲተገበሩ አይታይም። በብዛት የሚወጡ ጥናትና ምርምሮች በመደርደሪያ ተቆልለው የተረሱ ናቸው። ጥናትና ምርምሮቹ ካልተተገበሩ ሰዎች ሊያነቡዋቸው የሚችሉበት መንገድ ካልተመቻቸ «የጋን ውስጥ መብራት» ሆነው ይቀራሉ ማለት ነው።

እንደ ምሳሌ በአንድ ወቅት በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በተካሔደ ዐውደ ጥናት እንቦጭ እንደ ከሰል ሊያገለግል እንደሚችል እና ጣና ሐይቅ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች እንደከሰል ሊጠቀሙበት እንደሚችል በምርምር ጠቁመው ነበር። ነገር ግን ይህንን ምርምር በመተግበር ስጋት የሆነው እንቦጭ ለማስወገድ የቻለ ድርጅት የለም። ሰውየው በጋዜጠኞች ሲጠየቁም፤ የእኛ ድርሻ ጥናትና ምርምሩን ማቅረብ ነው። አቅም ያላቸው ደግሞ በገንዘብ ይሠሩታል ብለው ነበር።

እንደዚህ ዓይነት ሕዝብንና ሀገርን የሚጠቅም የምርምር ሥራ ሲሠራ «ፕሮፓዛሉ»ን ይዞ ባንክ ብድር ሰጥቶ ሊተገበር ቢችል ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል በፈጠረ ነበር። ችግሩ የጥናት ፕሮፖዛል ተመርኩዞ አዋጭነትን አጥንቶ የሚያበድር ባንክ የለንም። የምዕራባውያን ባንኮች ግን የዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ተመራቂዎችን እና ጥናት አቅራቢ ምሁራንን ጽሑፍ ገምግመው አዋጭነቱንና ለሀገር የሚበጅ መሆኑን ተረድተው ብድር እንደሚሰጡ ሰነዶች ያሳያሉ። የፈጠራ ሥራዎች በግለሰብ ሲሠሩ ባንኮች አዋጪነታቸውን ገምግመው ያበድራሉ።

**የምዕራባውያን ባንኮች ግን የዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ተመራቂዎችን እና ጥናት አቅራቢ ምሁራንን ጽሑፍ ገምግመው አዋጭነቱንና ለሀገር የሚበጅ መሆኑን ተረድተው ብድር እንደሚሰጡ ሰነዶች ያሳያሉ**

«ፈረስና ፈረሰኞች» በሚል በአዲስ ዘመን የወጣ ዘገባ፤ ኢትዮጵያ ፈረስ በማርባት ከአፍሪካ ቀዳሚ መሆኗዋን ይጠቅስና በዓለም ለማዳ ያልሆኑ ፈረሶች (feral horses) በአሜሪካ አትላንቲክ ጠረፍ፣ በአውስትራሊያ፣ በፖርቱጋልና ስኮትላንድ፣በአፍሪካ በናሚቢያ ብቻ ይገኛሉ ቢባልም በኢትዮጵያም በምሥራቅ ሐረርጌ 3000 ሜትር ከፍታ ባለው በቁንዱዶ ተራራ የዱር ፈረሶች መገኘታቸውን፤ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ዶክተር ከፈና ኢፋ በጥናታቸው ማውጣታቸውን በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ተዘግቦ ነበር።

ከላይ የጠቀስናቸው የጥናት ጽሑፎች ታትመው ወይም በመገናኛ ብዙኃን ካልተዘገቡ ጥናትና ምርምሩ የጋን ውስጥ መብራት ይሆናል። ማንም ኢትዮጵያዊ የዱር ፈረስ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ ወይ? ቢባል በሙሉ ልቡ የለም ነው የሚለው። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ በተለያዩ ወቅቶች የጥናት ምርምር ሥራዎች እያሳተመ ገበያ ይሠራጭ ነበር። ጥናትን ምርምሩ ለተማሪዎችና ለመምህራን ብሎም ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ መሆናቸው እሙን ነው።

እርግጥ ነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አልፎ አልፎ ሲያሳትማቸው የነበሩ የምርምር ጽሑፎች ነበሩ። አሁንም ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ምሁራን የተጻፉ ጥናታዊ ጽሑፎች የማሳተም ልምዱ ቢቀንስም፤ የሚታተሙ መጽሐፎች አሉ። ሌሎች የሀገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎችም ይህን ልምድ በማየት ጥናታዊ ጽሑፎችን ለማሳተም መጣር አለባቸው። ጥናታዊ ጽሑፎቹ ሲወጡ ከፍተኛ አበርክቶ ይኖራቸዋል።

ከላይ እንደ መግቢያ የጠቀስናቸው ሆኑ ሌሎች የጥናትና ምርምር ሥራዎች፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች ለአካባቢያቸው ማሕበረሰብ ብሎም ለሀገሪቱ የምርምር አበርክቶ ሲኖራቸው አዎንታዊ ሚና እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው።

መንግሥት ይህንኑ ከግምት በመከተት፤ የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፱፻፺፫/፱ሺ፲፰ አውጥቷል። ሥራው የበለጠ ከኅብረተሰቡና ከኢንዱስትሪዎች ከባለሀብቶች ጋር ትስስር እንዲኖረውና እንዲተገበርም የሚረዳና በትምህርት ሚኒስቴርና በመንግሥትም የተሰጠውንም ትኩረት የሚያሳይ ነው።

አዋጁ በኢንዱስትሪዎች፣ በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፣ በምርምር ተቋማት እና በሌሎች በመንግሥትና በግል ተቋማት መካከል የሚደረግ የሙያ፣ የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ፣ የአመራረት ዘይቤዎችን፣ ምርት ናሙናዎችን የመለዋወጥ ሂደት ሆኖ በውጤቱም ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂካዊ ዕድገቶች ለተጠቃሚ የሚደርሱበትና ተጠቃሚውም ቴክኖሎጂውን ወደ አዲስ ምርት፣ ሂደት፣ ጥቅም፣ ቁሳቁስ ወይም አገልግሎት የሚቀይርበት «የቴክኖሎጂ ሽግግር» ሂደት መሆኑንም ይኸው አዋጅ ያስረዳል።

ሰሞኑን በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ ዘገባ የጥናትና የምርምር ሥራዎች ወደ ተግባር የሚቀየሩበት አቅጣጫ መቀመጡን ያስረዳል። የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሠሩ አብዛኛው የምርምርና የጥናት ሥራዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተው እየተሠራ መሆኑን አስታውቋል።

በዩኒቨርሲቲዎች በርካታ የምርምርና የጥናት ሥራዎች ቢሠሩም አብዛኞቹ ተግባር ላይ እንደማይውሉ ሚኒስቴሩ ጠቅሶ፤ ዩኒቨርሲቲዎቹ ልምድ ካላቸው የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር እንዲሠሩ እየተደረገ እንደሚገኝ ተገልጿል።

የሚታተሙ ጥናቶች ለፖሊሲ ግብዓት የሚውሉና ለውሳኔ ሰጪዎች የሚያገለግሉ ከማድረግ አኳያ ጥሩ ጅምር ቢኖርም ከሚፈለገው አንጻር ዝቅተኛ የሚኒስቴሩ መግለጫ ያሳያል። ይህንንም ውስንነት ለመቅረፍ የምርምር ውጤቶች ወደ ማበልፀጊያ ማዕከላት ገብተው ወደ ተጨባጭ ውጤት እንዲቀየሩ እየተደረገ ይገኛል።

ከላይ እንደተጠቀሰው፤ የፈጠራ ሥራዎች ጥናት ምርምሮች ከመመረቂያ ባለፈ ሀገርና ሕዝብ ሊጠቀምበት የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል። በማንኛውም ደረጃ ያሉ የብድርና ቁጠባ ተቋማትም ሆኑ ባንኮች ቢተገበሩ አዋጪ ሊሆኑ ለሚችሉ ጥናትና ምርምር ለፈጠራ ሥራዎች ብድር ሊሰጡ የሚችሉበትን አሰራር ቢዘረጉ ሀገራዊ ፋይዳው የጎላ ነው።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተሳምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## እጅ ያጠረው ዕድሜ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ያለፉት ሰማንያ ዓመታት ለእማማ ሁሉአገርሽ ተሰማ በጎና ምቹ አልነበሩም። በእነዚህ ጊዚያት አብዛኛው የህይወት መንገድ ጎርባጣና ሻካራማ ነበር። ወይዘሮዋ ያለፈውን በትዝታ መልሰው ሲያወጉት ከልብ ይከፉቸዋል፣ ያዝናሉ፣ ይተክዛሉ። እንደዋዛ ሰማንያ ዓመታት ነጉደዋል፡፤ እንደቀልድ ስምንት አስርት አመታት አልፈዋል። የእሳቸው የሳቅ ደስታ ዘመን ግን በጣም ጥቂቱ ነበር።

ዛሬ እመት ሁሉአገርሽ ድፍን ሰማንያ ዓመት ሞልቷቸዋል። እሳቸው ይህን ይበሉ እንጂ ዕድሚያቸው ከአካላቸው ሲናበብ ስልሳዎቹን የተሻገሩ አይመስልም። ገጽታቸው የነቃ፣ አካላቸው የጠበቀ ነው። ቁመናቸው የዕድሜ ጥላ ያንዣበበት አይመስልም። ዛሬም ለመኖር ይታገላሉ ፣ ለህይወት ይሮጣሉ።

### ስምንት አስርት ዓመታት ወደኋላ

የልጅ ልጃቸውን አብዝተው የሚወዱት መነኩሴዋ አያት ህጻኗን ከእሳቸው መለየት አይሹም። በየሄዱበት አዝለዋት ይዞራሉ። እሳቸው ልጆቻቸውን በልፋት ድካም አሳድገዋል። ዛሬ ሁሉም ራሱን ችሎ የራሱን ህይወት ይመራል፣ እማሆይ ጉልበታቸው እየደከመ ትከሻቸው እየተፈተነ ነው። እንዲያም ሆኖ ለልጅ ልጃቸው የሚሆን አቅም አላጡም። ህጻኗን በየሄዱበት ከትከሻቸው አዝለዋት ይጓዛሉ።

የእሳቸውን ልፋትና ድካም ከልጅ ልጃቸው ፍቅር አጣምረው የሚያዩ ዘመዶች ታዲያ ሁሌም ይገረማሉ። አንዳንዶች ደግሞ ለእሷ የሚመጥን ስም እንዲያወጡላት ይጠይቃሉ። አያት ሀሳባቸውን አልናቁም። ለልጅ ልጃቸው ስም መረጡ፣ አማረጡ። ዘወትር ከትከሻቸው አዝለው በየቦታው የሚያዞርዋትን ህጻን ‹‹ሁሉ አገርሽ›› ሲሉ ጠሯት።

ሁሉአገርሽ ከአያታቸው ትከሻ ታዝለው ብዙ ቦታን አይተዋል ።ደጀሰላም ገዳሙን፣ አገር መንደሩን፣ ቀዬ ገበያውን ጎብኝተዋል ። ይህ አጋጣሚ ለሁኔታው ፈቅዷልና ሁሉ አገራቸው ቢባል አያስደንቅም። ስማቸው በሌሎች ተወዷል። ትርጓሜው በሁሉም ጸድቋል።

በአያታቸው እጅ ያደጉት ሁሉ አገርሽ ከትከሻቸው ወርደው መራመድ እንደያዙ የህይወትን ግዴታ ‹ሀ..› ብለው ጀመሩት። ልጅነታቸው እንደ እኩዮቻቸው ነበር። እናት አባታቸው ቤት ካፈራው፣ ሁሉ አይነፍጓቸውም። ከቀዬው እየቦረቁ፣ ከባልንጀሮቻቸው እየተጫወቱ አድገዋል።

ከአካባቢው ጥቂት የሚባሉት በያዙት ዕውቀት ሥማቸው ይጠራል። እሳቸው ግን ትምህርትን የማግኘት ዕድል አልነበራቸውም ። እንደሴት ልጅ ወግ ከእናታቸው ጉያ ሳይርቁ ቤተሰቡን በጉልበት አግዘዋል። የታዘዙትን ከውነዋል።

**ኮረዳነት**አሁን ሁሉ አገርሽ ከልጅነት ዕድሜ አይደሉም። ህጻንነታቸው አልፎ ፣ሩጫ ዝላዩን ትተዋል። እንደፊቱ ቀና ብለው አይሄዱም። ሲያናግሯቸው ያፍራሉ። ለእርምጃ ጉዟቸው ይጠነቀቃሉ። በእሳቸው ዕድሜ ያሉ እኩዮቻቸው ዕጣ ፈንታ ባል ማግባት ትዳር መያዝ ነው። ሁሉአገርም ቢሆኑ ለዓይን የሚስቡ ልጃገረድ ሆነዋል። አስራአምስተኛ ዓመታቸውን ከያዙ ጀምሮ ‹‹ልጃችሁን አጋቡን፣ ዳሩልን›› የሚሉ በዝተዋል።

እናት አባት ለጋብቻ የሚመጡ ጥያቄዎቹን አልገፉም። ልጃቸው ባል አግብታ፣ ትዳር ይዛ ወግ ማዕረግ ብታይ ይወዳሉ። ቆይቶ ጋብቻውን ከጠየቁት መሀል ለአንደኛው ልባቸው አጋደለ። ቀልባቸው ለፈቀደው ሰው ሁሉአገርሽን ሊድሩ ተስማሙ።

ሁሉአገርሽ በአስራአምስተኛ ዓመታቸው በወላጆቻቸው ይሁንታ በሰርግ ተዳሩ። የልጅነት፣ ዕቃዕቃ ጨዋታ ተረሳ። ዝላይ ፈንጠዝያው ቀረ። ሁሉም አለፈና ወይዘሮ ተባሉ ። ‹‹ሙሽሪት ልመጂ›› የተባለላቸው ወጣት የእናት አባታቸውን ቤት ትተው ባላቸውን ተከተሉ። አዲሱ ጎጆ በአዲስ ሙሽሮች ድምጽ ሞቀ ፣ደመቀ ። አዲስ ህይወት ቀጠለ።

ትዳር እንደጀመሩ የመንግሥት ሰራተኛው ባለቤታቸው ለስራ ከአካባቢው ሊርቁ ሆነ ። ትዳር ነውና ሁሉአገርሽ ከእሳቸው መነጠል አልቻሉም። ባለቤታቸውን ተከትለው ወደ አሰብ አቀኑ።

በወለጋ መስመር ጅባትና ሜጫ ‹‹ጨሊያ›› የተወለዱት ወይዘሮ ዕድገታቸው ከአካባቢው የራቀ አይደለም። ከስፍራው ወጥተው ባያውቁም ባላቸውን ለመከተል ዓይን አላሹም። ‹‹ጨርቄን ማቄን›› ሳይሉ አብረዋቸው ተጓዙ።

አገራቸው ላይ እናት አባታቸውን ትተዋል። ‹‹የራሴ›› የሚሉት ሀብት ንብረትም አላቸው። ይህ ሁሉ ግን ከባላቸው አልነጠላቸውም። አሰብ ገብተው ትዳራቸውን ቀጠሉ። አሰብ ላይ ሁሉም ሮጦ ተግባብቶ ያድራል። ማነህ ? ከየት ነህ ? ምንድነህ ? ይሉት ጉዳይ የለም። ሁሉም በግሉ ሰርቶ በጋራ ይበላል። ልዩነት አይታወቅም፡ እንደቤተሰብ ቋንቋው አንድ ነው። በፍቅር ተዋዶ፣ ተከባብሮ ይኖራል።

ባለቤታቸው በአሰብ ነዳጅ ማጣሪያ ድርጅት ይሰራሉ። እሳቸውን ጨምሮ በርካቶች የድርጅቱ ነዳጅ ማጣሪያ ላይ ህይወታቸው ተወስኗል።ሁሉ አገርሽ ለቤት ለኑሯቸው የባላቸውን እጅ አልጠበቁም። ለሊቱን እንጀራ እየጋገሩ ሲነጋ በሽያጭ ያስረክባሉ።

ጊዜው በአጼ ሀይለስላሴ ዘመን ነው። የዛኔ እንዳሁኑ ህዝብ አልበዛም።ኑሮ አልተወደደም። እንዲያም ሆኖ ራስን ለማሸነፍ ሌት ተቀን መልፋት ግድ ነው። ሁሉአገርሽ ለእሳቸው፣ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸው መኖር እየታገሉ ነው። ሙቀት እያጋያቸው፣ በጉልበታቸው ድካም በላባቸው ወዝ ያድራሉ።

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# እጅ ያጠረው...

ከገጽ 16 የዞረ

ጥቂት አይሏቸው ዓመታት በአሰብ ህይወትና ኑሮ ተገፉ። በእነዚህ ጊዚያት ልጆች ተወልደው አደጉ። ጊዜዎች ነጎዱ ፣ ዕድሜ ጨመረ። ከጊዚያት በኋላ የንጉሱ ወንበር በስልጣን ነቅናቂዎች ተገርስሶ ወደቀ። በመላው ሀገሪቱ ለውጥ መጣ፣ ኑሮ ተለወጠ።

አብዮትና ፖለቲካ ይሉት ጦስ የብዙዎችን ቤት አንኳኳ። የነበረው ባልነበረው ጥግ ሲጓዝ እንደነ ሁሉአገርሽ ያሉ ሰርቶ አዳሪዎች ኑሯቸው ተንገጫገጨ። ሁኔታዎች ተረጋግተው ቦታቸውን እስኪይዙ ጥቂት ችገራቸው። ቆይቶ ግን ህይወት እንደቀድሞው ቀጠለ። ዓመታትን በስፍራው የገፉት ቤተሰቦች የአቅማችውን እየሰሩ እስከ 1983 ዓ.ም ዘለቁ። ከዚህ ዓመት በኋላ ግን ሁሉም ነገር ተቀየረ። አዲስ የመንግሥት ለውጥ መጣ።ስልጣን በሌሎች ሀይሎች በተተካ ጊዜ ሰራዊቱ ተበተነ፣ ይህኔ በየስፍራው ያለ ነዋሪ ስለደህንነቱ ዋስትና አጣ። ስደት፣ መፈናቀል፣ ስራአጥነት በረከተ።

የአሰብ ነዳጅ ማጣሪያና በውስጡ ያሉ በርካታ ሰራተኞች ከዚህ ችግር አልዳኑም። በሌሎች የሆነው ሁሉ በእነሱም ደረሰ። አብዛኞቹ የነበሩበትን ለቀው ወደ መሀል አገር ተሰደዱ። ጥቂት የማይባሉት ቤት ንብረታቸውን ትተው ተፈናቀሉ። ህጻናት ሴቶችና አረጋውያን ፣ጉዳትና እንግልት አገኛቸው።

### ጥቁር እንግዳ

ወይዘሮ ሁሉአገርሽና ቤተሰቦቻቸው የአሰብን ምድር ለቀው ወጥተዋል። አሁን በሀገሪቱ አዲስ ለውጥ ሆኗል። አብዛኞች በያዙት ለመቀጠል፣ በትናንቱ ለመኖር ተቸግረዋል። ሁሉም ህይወቱን ለማትረፍ ይበጃል ያለውን እያደረገ ነው። አቅም ያለው አገሩን ትቶ ወጥቷል። ስደት ብርቅ አልሆነም።ችግር እግር በእግር ተከትሎ የብዘዎችን ማንነት መፈተን ይዟል።

ሁሉአገርሽ አዲስ አበባ ደርሰዋል። ብቻቸውን አይደሉም። ከእሳቸው ጋር ልጆችና ባለቤታቸው አሉ። አሁን ‹‹ለአገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ›› ይሉት ስሜት በውሰጣቸው ነግሷል። በእጃቸው እዚህ ግባ የሚባል ጥሪት የለም። ድንገቴው ለውጥ ብዙ ነገራቸውን ቀይሯል።

ከእጅ ባጡ፣በነጡ ጊዜ ከዘመድ መጠጋት፣ እንግዳ መሆን ያሳቅቃል። ሌላውን ለመጠየቅ፣ ለመጠያየቁ ያወጡት፣ ይመነዝሩት ሲኖር ፣ ደስ ይላል። ባዶ እጅ ደርሶ ያስጨንቃል፣ ያሳፍራል። ሁሉ አገርሽና ቤተሰቦቻቸው ምርጫ አላገኙም። ተፈናቅለው አዲስአበባ ከመጡ ጀምሮ ማረፊያቸው ከዘመድ ቤት ሆኗል።

ያረፉት ከባለቤታቸው እህቶች ዘንድ ነው። እነሱ የራሳችን ይሉት ቤትና መጠጊያ አላገኙም። ቀን አልፎ ችግር እስኪርቅ እንዲህ ሊሆኑ ግድ ብሏል። ሁሉአገርሽ ግን ተጨንቀዋል። ካደጉበት አገር የራሳቸው ቤትና ንብረት ነበራቸው። እሱን ትተውት ከራቁ ዓመታት አልፈዋል። ይህን ሲያስቡ ወላጆቻቸው ትውስ ይሏቸዋል። እስከዛሬ ተመላልሰው ጠይቀዋል።አሁን ግን ሁለቱም በህይወት የሉም ። ውስጣቸው ባዶነት እየተሰማው ነው ። ትናንት ለሌሎች ይተርፍ የነበረው እጃቸው ዛሬ ለእርዳታ ተዘርግቷል ። አሁን የሚያዙበት ዕልፍኝ እንዳሻቸው የሚቆርሱበት ማጀት የላቸውም። እንዲህ መሆኑ አስከፍቷቸዋል።

ጥቂት ጊዚያት ቆይቶ ወይዘሮዋ ራሳቸውን ለመቻል መሮጥ ያዙ። በወቅቱ ለሌሎች መሰሎቻቸው የሆነውን እርዳታ አላገኙም። በተፈናቃይ ስም የጠየቁት የቀበሌ ቤትም አልተሳካም። መቀመጥ አልፈለጉም። ጉልት ለመሸጥ ጥቂት ነገሮች ይዘው ከመንገድ ተቀመጡ።በውሏቸው ያገኙትን ቋጥረው ቤት መመለስ ልምዳቸው ሆነ።

ውሎ አድሮ መላው ቤተሰብ የአዲስ አበባን ህይወት ለመደው። ባለቤታቸው እያረጁ ነው። ወይዘሮዋ ባላቸው የጡረታ አበል እንዳላቸው ሰምተዋል። ሽማግሌው ግን ለአንድምቀን አሳይተው፣ ሰጥተዋቸው አያውቁም። ልጆቻቸው ቢደርሱም ሊያግዙ ሊደግፏቸው አይፈቅዱም ። ዘወትር ለየራሳቸው ኑሮ ይሮጣሉ።

ከዓመታት በፊት በሴት ልጃቸው እጅ የነበረን የንግድ ሱቅ ተከራይተው ነበር ። በእሱ ጥቂት እየሰሩም ቀን ገፍተዋል። ቆይቶ ግን ‹‹ቦታው ይፈለጋል›› በሚል ሰበብ መተዳደሪያቸው ተነጠቀ። ይህ ከሆነ ወዲህ ቤት ከመዋል ያለፈ መላ አላገኙም።

ሁሉአገርሽና አዛውንቱ ባለቤታቸው ዛሬም በአንድነት ይኖራሉ። አባወራው በህመም ምክንያት ከአልጋ ከዋሉ ቆይቷል። መነሳት፣ መንቀሳቀስ ተስኗቸዋል ። እሳቸውን የማገዝ የማኖር ጫናው ከአዛውንቷ ሁሉ አገርሽ እጅ አላለፈም። ህመምተኛውን በደከመ አቅማቸው እያነሱ ያገላብጧቸዋል፣ ያገኙትን እያቀመሱ መድሀኒታቸውን እየሰጡ ያስተኟቸዋል።

ዛሬ አብሮአደጎቹ ባልና ሚስት ከአባወራው እናት አባት በተላለፈ የቀበሌ ቤት ይኖራሉ። ከአጠገባቸው የሰውዬው የቅርብ ዘመዶችና እህቶቻቸው አሉ ። የእነሱ መኖር ግን ለሁሉአገርሽ ኑሮ የጠቀመ አይመስልም። ሰላማቸውን ካጡ ቆይቷል ።

የእሳቸው ውስጠት በገለልተኝነት ስሜት ተይዟል። ሁሌም ብቸኛ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። ሁሉም የሚናገሩትን የሚያምኗቸው ፣ የሚሉትን የሚቀበሏቸው አልመስል ካላቸው ሰንብቷል። አንዳንዴ ባለቤታቸው ጭምር ከዘመዶቻቸው አብረው ይናገሯቸዋል። ያስከፏቸዋል።ይህ እውነት ‹‹ብቸኛ ነኝ›› ለሚሉት ሴት ልዩ ትርጉም አለው።

በዕድሜ ብዛት መፍረስ የጀመረው ቤታቸው ክረምቱን ዝናብና ጎርፍ ያስገባል።እንዲህ መሆኑ ወይዘሮዋን ጤና አሳጥቷል። በድካም እየተንገላቱ የሚያቀኑትን ጎጆ የሚጎበኘው የለም።ወዲህ ችግሩ፣ እልፍ ሲልም እጅ ማጠሩ ሲያሳስባቸው ይውላል።

### የሰባት እናት

ወይዘሮዋ ዕድሜያቸው እየገፋ አቅማቸው እየደከመ ነው። ማንም ግን ‹‹እናቴ፣እረፊ፣ እንጡርሽ፣እንደግፍሽ›› አይላቸውም። ባለቤታቸው ከሌላ እናት የወለዷቸው ልጆች አሉ።አንዳንዴ አባታቸውን ያስባሉ፣ ይጠይቃሉ። ሁሉአገርሽ ግን ከሰባቱ ልጆቻቸው አንዳች የሚያገኙት የለም።

ይህን ባሰቡ ጊዜ ከልብ ይከፋሉ። ዕንባቸው በአንገታቸው ይወርዳል። በዕድሜያቸው ማምሻ አብረዋቸው የኖሩ አጋራቸውን መተው፣ መራቅ አይሹም።ሁሌም ጉዳት ህመማቸው ይሰማቸዋል ። መቼም ቢሆን ችግራቸው የእሳቸውም ችግር ሆኖ ይዘልቃል።

ዛሬ ለጎደለው ኑሯቸው ከጎናቸው የሚቆም ልጅ የለም። ሰባት ልጆችን ወልደው፣ አሳድገዋል። አንዳቸውም ግን ‹‹እናታችን የት ነሽ ?› ብለዋቸው አያውቁም። እሱንም ቢሆን ‹‹ተመስገን›› ብለው ትተውታል። አንዳንዴ ግን በባለቤታቸው ዘመዶች የሚደርስባቸው በደል ከአቅም በላይ ሲሆን ውስጣቸው ይነካል። እነሱ ቤት ለዋሉት ሽማግሌ ባይሆኑም ለእሳቸው ሲሆን ይበረታሉ። እንዲህ መሆኑ ጠዋት ማታ እጅ ለሚያጥራቸው ፣ ጓዳቸው በችግር ለሚፈተነው ሴት ኑሮን አከብዷል።

በግቢው ያሉ ነዋሪዎችም ውሰጣቸውን አላዩላቸውም። ሁሌም እንደሚሉት በእነሱም ዘንድ ፊት ተነስተዋል ። እንዲያም ሆኖ ቂም ለመያዝ ፣ክፋት ለማሰብ ተዘጋጅተው አያውቁም። ለማይረዷቸው ልጆችና ዘወትር ለሚያስቀይሟቸው ሁሉ ውስጣቸው ይቅርባይነትን ለምዷል።

ዛሬ እመት ሁሉአገርሽ በማምሻ ዕድሜያቸው ላጠረ እጃቸው የፈጠነ ዕድል አላገኙም። እስከዛሬ ጾም ውሎ ላለማደር የአቅማቸውን ሞክረዋል፤ ያገኙትን ሰርተዋል።ዛሬ ግን እንደትናትናው አይደሉም። ተስፋ መቁረጥ ከችግር ተዳምሮ ሲያስከፋ ፣አንገት ሲያስደፋቸው ይውላል።

### ችግርን በምስጋና

በቅርቡ ውስጣቸውን የተረዱ አንዳንድ የወረዳ አመራሮች ከግቢው ደርሰው ቤታቸውን አንኳኩ። በአካባቢው ከሚገኝ የምገባ ማዕከል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በጠየቋቸው ጊዜ አላንገራገሩም። ጠያቂዎቹ የርሀባቸው ማስታገሻ ፣ የችግራቸው መላ መሆናቸውን አመኑ። ውለው አላደሩም። በየቀኑ አንድ እንጀራ በወጥ እየተቀበሉ ለራሳቸውና ለህመምተኛው አባወራ ሆድ ደረሱ። በሆነው፣ በተደረገው ሁሉ ደስ አላቸው። በዚህ ዕድሜ ተቸግረው እጅ ቢያጥራቸውም አብልቶ ላሳደራቸው ፈጣሪ የተለመደውን ቃል አይነፍጉም። ዘወትር ‹‹ተመስገን›› ይላሉ። ‹‹**ተመስገን**››

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የኮንስትራክሽን ኢግዚቢሽኑን ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ትብብር

በኃይሉ አበራ

የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት እድገት ቁልፍ ሚና እንዳለው ይታመናል። በሀገሪቱ በመንገድ፣ በጤናና ትምህርት፣ በኢንዱስትሪ ፓርክ፣ በመስኖ መሠረተ ልማት፣ በአየር ማረፊያ፣ ወዘተ... መሠረተ ልማቶች ግንባታዎች ለታዩ ለውጦችም ተጠቃሹ ይሄው ዘርፍ ነው።

የሕዝቡን እንግልት የሚቀንሱ፣ ኢኮኖሚውን የሚያሳድጉ መሠረተ ልማቶችን፣ መኖሪያ ቤቶችን፣ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ወዘተ የመገንባት አጀንዳ ሲነሳ ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አብሮ ይነሳል። ሀገሪቱ በቀጣይ ልትደርስበት የምትፈልገው የመሠረተ ልማት አቅም ሲታሰብም እንዲሁ ዘርፉ ይጠቀሳል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ይህ ኢንዱስትሪ ከሀገሪቱ የካፒታል በጀት 60 በመቶውን የሚያንቀሳቅስ፣ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ከ23 በመቶ በላዩን የሚይዝ፣ ከግብርናው ቀጥሎ ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ይታወቃል።

በሀገር በቀል ኢኮኖሚው ማሻሻያው የአስር ዓመቱ መሪ እቅድም በዘርፉ በርካታ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ታቅደው እየተሰሩ ናቸው። ከእነዚህ መካከልም በመንገድና በቤቶች ልማት የተያዙትን እቅዶች በአብነት መጥቀስ ይቻላል። የሀገሪቱን የመንገድ ሽፋን ከ166 ሺ. ወደ 246 ሺ. ለማሳደግ ታቅዶ እየተሰራ ነው፤ ከ400ሺ. በላይ የመኖሪያ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዷል።

ይህ ኢንዱስትሪ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ ኮቪድ ወረርሽኝ፣ ከሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነትና ያንን ተከትሎ በሀገሪቱ ላይ ከተፈጠሩ አንዳንድ ጫናዎች እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ከተከሰተው የጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ ኢንዱስትሪው ተቀዛቅዞ ቆይቷል።

ፈቱንም ቢሆን በግንባታና ባለሙያ ጥራት ጉድለት፣ በፕሮጀክት ማኔጅመንትና በሥነ ምግባር ችግሮች፣ በውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ተወዳዳሪ አለመሆን፣ ከግዥና ክፍያ ወዘተ ጋር በተያያዙ ችግሮች ይፈተን በነበረው በዚህ ኢንዱስትሪ ላይ እነዚህ ፈተናዎች የወለዷቸው ችግሮች ሲደማመሩ ኢንዱስትሪውን በአያሌ ተግዳሮቶች የተተበተበ አድርገውታል። እነዚህ ሁሉ ችግሮች ተደማምረው ህልውናው አደጋ ውስጥ የወደቀ እስከ መባል አድርሰውታል።

ችግሮቹን በመገንዘብ ዘርፉን ለመታደግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉም ቆይተዋል፤ እየተደረጉም ይገኛሉ። የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የኢንዱስትሪውን ችግሮች ለመፍታት ከተከናወኑ ተግባሮች መካከል የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ተቋቁሞ እየሰራ መሆኑ፣ አዲስ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መዘጋጀቱ ይጠቀሳሉ። የዘርፉን የልህቀት ማእከል ለመገንባትም እየተሰራ ነው።

የዘርፉ ችግሮች በኢንዱስትሪው ተዋንያን ተለይተዋል፤ መንግሥትም የኢንዱስትሪውን ችግሮች በጥናት ላይ ተመስርቶ መፍታት እንደሚያስፈልግ በማመን ይህንኑ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የትራንስፖርት፣ ከተማ ልማትና መሠረት ልማት ቋሚ ኮሚቴ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን መልካም እድሎች፣ ችግሮችና መፍትሔያቸውን ያመላከቱ ጥናቶችን በዘርፉ ባለሙያዎች አሰርቶ በቅርቡ ያካሄደው አንድ መድረክም ለዚህ ማሳያ ነው።

የዘርፉ ምሁራን፣ የኢንዱስትሪው ባለድርሻዎች፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በተሳተፉበት በዚህ መድረክ ላይ እንደተጠቆመው፤ የዘርፉ ችግሮች ተለይተዋል፤ ችግሮቹን በጋራ መፍታት እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል።

በመድረኩ የተገኙት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ችግሮቹን የግሉ ዘርፍ ወደ መንግሥት፣ መንግሥትም ወደ ግሉ ዘርፍ ሳይገፋ በጋራ እየመከሩ መፍታት እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ በበኩላቸው፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፣ ነባር ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ



እንዲሁም አዳዲስ የግንባታ ሞዴሎችን ማምጣት ላይ መሰራት እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል።

በመድረኩ ከተነሱት ችግሮች መካከል ኢንዱስትሪው የሚከተለው ኋላቀር አሰራር አንዱ ነው። ኢንዱስትሪው በቴክኖሎጂ ላይ ተመስርቶ መስራት ያለበት መሆኑ ተጠቁሞ፣ ቴክኖሎጂ ላይ ተመስርቶ መስራት ካልተቻለ ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠል እንደማይቻልም ተመልክቷል።

ቴክኖሎጂን ለመታጠቅ ብዙ የሚያስፈልጉ ነገሮች ቢኖሩም፣ የውጭ ምንዛሬ ወሳኙ ነው። ዘመኑ ያፈራቸውን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ማሽነሪዎችንና ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በርግጥም የውጭ ምንዛሬ ያስፈልጋል።

ከዚህ ውጭ ደግሞ በዘርፉ ከፍተኛ ደረጃ ከደረሱ በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ እየሰሩ ከሚገኙ የውጭና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ልምድና ተሞክሮ መቅሰምም ያስፈልጋል። ኢንዱስትሪውን አስመልክቶ ከሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ሀገር አቀፍ ኢግዚቢሽንና ባዛሮችም ልምድና ተሞክሮ መቅሰም፣ ትስስር መፍጠር ሌሎች የዘርፉን ችግሮች መሻገሪያ መንገዶችና እድሎችን መጠቀሚያ መሳሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

የዘርፉን ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ለማዋል በተለይ የዘርፉ ዓለም አቀፍ ኢግዚቢሽኖች ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል። በሀገራችን የሚካሄዱ ኢግዚቢሽኖች በርካታ ድንበር ዘለል የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች፣ ቴክኖሎጂ አቅራቢዎች፣ ወዘተ የሚገኙባቸው እንደመሆናቸው የኛ ተቋራጮች ራሳቸውን እንዲመለከቱ፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ በሽርክና እንዲሰሩም ፋይዳቸው የጎላ ይሆናል።

እንደ ሀገር ተወዳዳሪ ኩባንያዎችን መገንባት እንደሚያስፈልግ ይታመናል። ለእዚህ ደግሞ ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን መድረኮች፣ የልምድ ልውውጦች፣ ወዘተ ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ‹‹ኢትዮጵያን እንገንባ›› በሚል መሪ ሃሳብ ከትናንት በስቲያ በሚሊኒየም አዳራሽ የተከፈተው ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢግዚቢሽን /ቢግ ፋ5 ኮንትራት ኢትዮጵያ/ ለእዚህ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ በመንግሥትም በዘርፉ አካላትም ታምኖበታል።

ኢግዚቢሽኑን የከፈቱት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ እንዳስገነዘቡትም፤ በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶች በፍጥነት በማደግ ላይ ያለውን የከተሞችን እድገት ለመምራት እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገቱን ለመደገፍ ያስፈልጋሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ መንግሥት በ10 ዓመቱ ብሔራዊ የልማት እቅድ መሠረት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚፈጸሙ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ተግባራት አቅዶ እየሰራ ነው። የመንገድ ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ግንባታ፣ የባቡር፣ የመኖሪያ እና የከተማ ልማት ግንባታ፣ የኃይል አቅርቦት እና መገልገያዎች ግንባታ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ምስረታ፣ የአቅም ግንባታ እና የክህሎት ልማት፣ የቴክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን ልማት፣ የመንግሥት እና የግል ትብብር ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ቁልፍ መሠረተ ልማቶቿን ለመገንባት በተመጣጣኝ ወጪ መኖሪያ ቤቶችን ለዜጎች ለማቅረብ እንዲሁም የተሻሉ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ዘላቂ ተባባሪ ወዳጆችን እንደምትፈልግም አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ በተዘጋጀው ዓለም አቀፍ ኢግዚቢሽን የመጪው ዘመን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መልክን እያስያዙ ያሉ የዘርፉ መሪዎች፣ አምራቾች፣ የሃሳብ አመንጪዎችና ባለሙያዎች እየተሳተፉ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ኢግዚቢሽኑ አዳዲስ ትብብሮችን የሚፈጥርና የሁለትዮሽ ጠቀሜታን የሚያጎለበት እንዲሁም በዘርፉ ዘላቂ ወዳጆችን መፍጠር የሚያስችል መሆኑንም ተናግረዋል።

የቢግ አምስት ኮንትራክት ኢግዚቢሽን ከሚካሄድባቸው ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብጽ እና ኬንያ መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗን ጠቅሰው፣ ይህ በራሱ ትልቅ እምርታ መሆኑን አስታውቀዋል። ይህም ሀገሪቱ የሚመጣውን ከመቀበል ባሻገር ብዙ የምትሰጠው እንዳላት ያመላክታል።

በኮንስትራክሽን ዘርፍ የምታደረጋቸው ጥረቶች የዚህ ዓይነት ትላልቅ ኢግዚቢሽኖችን በላቀ ሁኔታ ለማስተናገድ የምትችልበትን አቅም እየፈጠረላት ነው። ኢግዚቢሽኖቹ ለተጀመረው የቱሪዝም ልማትም መንገድ ከፋች ናቸው ሲሉ ጠቅሰው፣ በዚህ መድረክም ከባለፈው ዓመት በበለጠ ከ8300 በላይ ባለድርሻዎች መካፈላቸው ኢትዮጵያ በዘርፉ ያላትን እምቅ አቅም ያመላከተ መሆኑን ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ኢግዚቢሽኑ ንግድ ድርጅቶችን ከባለሀብቶች ጋር በማገናኘት በመሠረተ ልማት፣ በከተማ ልማት እና በሪል እስቴት ልማት ላይ ለታቀዱ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ምቹ መድረክ ይፈጥራል። በፍጥነት እያደገ ያለውን የኢትዮጵያ የግንባታ ዘርፍ የገበያ ክፍተት ለመሙላት በርካታ አቅም ያላቸው ኩባንያዎች ግንዛቤ ኖሯቸው በዘርፉ በስፋት እንዲሳተፉ ያስችላል።

ለሀገር ውስጥ አቅራቢዎች አማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች ልምድ የመቅሰሚያ እድል ከመፍጠሩ በዘለለ የንግድ ትስስር የሚፈጠርባቸው መድረኮች ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው ሲሉም ጠቅሰው፣ መድረኩ ከግንባታ ማዘመን እስከ አገልግሎት ያለውን ሂደት በማሳደግ ስማርት ሲቲን ለመገንባት የሚያስችል ልምድ እና እውቀት የሚገኝበት መሆኑንም አመላክተዋል።

የዓለም አቀፉ ዲኤምጂ ኢቨንትስ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ቤን ግሪንሽ በበኩላቸው ኢግዚቢሽኑ በኢትዮጵያ መካሄዱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዕድገት እንደሚያፋጥነው ገልጸዋል። ከፍተኛ የንግድ ትስስርን፣ ኢንቨስትመንትን፣ ቱሪዝምን እና የገበያ ዕድልን ይዞ እንደመጣ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኢግዚቢሽኑ በውጭ ሀገራት አምራቾችም ሆነ በሀገር ውስጥ የግብዓት አምራችና አቅራቢዎች መካከል መልካም የግንኙነት መደላድል በመፍጠር የኢትዮጵያን ዘላቂ የልማትና ኢንቨስትመንት ዕድገት ያፋጥናል። በአጠቃላይ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ከግንባታ አገልግሎት እስከ ስማርት ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎች ይሳተፉበታል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንደተናገሩት፤ ሀገራችን ቀጣይነት ያለው እድገት እና ብልጽግናን እውን ማድረግ እንድትችል የሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ስኬት ድርሻ የጎላ ነው።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በርካታ ባለድርሻዎችን የሚያሳትፍና ሰፊ ሀብት የሚጠይቅ የኢኮኖሚ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢንዱስትሪውም በዘርፉ ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት እና እድሎችንም በአግባቡ ለመጠቀም የሁሉንም ተዋንያን ቅንጅት እና የጋራ ርብርብን ይጠይቃል ብለዋል።

ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ ካደጉ ሀገራት ጋር ጭምር በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግ ያመለከቱት ሚኒስትሯ፣ ኢግዚቢሽኑ በሌሎች ሀገራት ያለውን የቴክኖሎጂ አቅምና ልምድ ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት የተሻለ ሥራ ለማከናወን እንደሚረዳ ገልጸዋል። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማነቃቃት፣ የዘርፉን ዋነኛ ተዋንያኖች እርስ በእርስ ለማስተዋወቅና አብሮ የመሥራት ባሕልን ለማዳበር እንደሚያግዝም ጠቁመዋል።

ሚኒስትሯ እንዳስታወቁት፤ ከኢግዚቢሽኑ ጎን ለጎን የኮንስትራክሽን ዘርፉን በዕውቀት በምርምርና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ የሚያስችሉ አውደ ጥናቶች ይካሄዳሉ። የኮንስትራክሽን ግብዓት አማራጮችን ለማግኘት፣ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የመጡ ኩባንያዎችን ከኢትዮጵያዊያን ኩባንያዎች ጋር በቴክኖሎጂ፣ በዕውቀት ሽግግር፣ በንግድና ኢንቨስትመንት ለማስተሳሰርም ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል።

ኢግዚቢሽኑ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን እድገት ወደ ተሻለ ደረጃ በማድረስ የብልጽግና ጉዞአችንን ስኬት ለማስመዝገብ የሚያስችለን ነው ያሉት ሚኒስትሯ፣ በዘርፉ የሚስተዋሉትን የፋይናንስ፣ የግብዓትና፣ የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ እና የክህሎት ተግዳሮቶችን በመለየት የውጭ ባለሀብቶችንና የሀገር ውስጥ የግብዓት አምራቾችን በከፍተኛ ደረጃ በማስተሳሰር ሀገራችንን ወደላቀ ደረጃ ማሸጋገር እንደሚያስችል አመላክተዋል።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ ተከታታይነት ያለው ሙያዊ ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፣ የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን የኢንዱስትሪ ባለሙያዎች እውቀታቸውን እንዲያሰፉ ኢግዚቢሽኑ ትልቅ የልምድ ማዕከል እንደሚሆን ይታመናል ብለዋል።

ሚኒስትሯ እንደተናገሩት፤ ባለፈው ዓመት በተዘጋጀው ተመሳሳይ መድረክ ከ28 ሀገራት በላይ ተሳትፈዋል፤ ከ153 በላይ የኤግዚቢሽን አቅራቢ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን እንዲሁም አገልግሎታቸውን ማቅረብ ችለዋል። ከ20 በላይ ይዘታቸው የተረጋገጠላቸው የፓናል ጽሑፎች በከፍተኛ ባለሙያዎች፣ በዘርፉ ተመራማሪዎች ቀርበዋል። ከ10 ሺዎች በላይም ኤግዚቢሽኑን የመጎብኘት እድል አግኝተዋል። ከ10 ሚሊየን በላይ ዜጎችም መረጃዎች ተደራሽ የተደረጉበት ነው።

በዚህ ዘንድሮ እየተካሄደ በሚገኘው ቢግ 5 ኮንስትራክት ኢትዮጵያ ኢግዚቢሽንም ከ150 የዓለም ሀገራት የመጡ የኤግዚቢሽን አቅራቢዎች ይሳተፉበታል፤ ከእነዚህም መካከል ከ40 በላይ የሚሆኑት የሀገር በቀል ኩባንያዎች ናቸው።

በኢግዚቢሽኑ ላይ ለበርካታ ዓመታት በምርምር ዘርፍ በተለይ በምህንድስና፣ በፕሮጀክት አስተዳደር፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በመሠረተ- ልማትና ሕንፃ ግንባታ ላይ ያተኮሩ፣ ጥናታዊ ጽሑፎች፣ የፓናል ውይይቶች፣ ከፍተኛ ልምድና ተሞክሮ ባላቸው ምሁራን እንደሚቀርቡ፣ በተለያዩ ሀገራት የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እንደሚገበያዩ መርሃ-ግብሩን አስመልክቶ በወጡ መረጃዎች ተመልክቷል።

# ስፖርት





# ኢትዮጵያውያን የነገሱበት የኦስሎ ዳይመንድ ሊግ


**ብርሃን ፈይሳ**

ስድስተኛው የዳይመንድ ሊግ መዳረሻ በሆነው ኦስሎ ከተካሄዱ ውድድሮች መካከል በተለይ የስፖርት ቤተሰቡን ቀልብ የያዘው የ5ሺ ሜትር ሩጫ እንደተጠበቀው ድንቅ ፉክክር አስተናግዷል። ባለድሉ አትሌት ሃጎስ ገብረህይወት የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን ዳግም ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያደረገው ጥረትም በሁለት ሰከንዶች ባይሳካም የኢትዮጵያን ክብረወሰን ግን ሰብሯል። ይኸውም የአትሌቱን ችሎታ በኦሊምፒክ መድረክ ላይ በድጋሚ ለማየት ዓለም በይበልጥ እንዲጓጓ ያደረገ ሆኗል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በርቀቱ ነግሰው የቆዩት ዩጋንዳውያን አትሌቶችም ኦስሎ ላይ ለኢትዮጵያውያኑ እጅ መስጠታቸው የርቀቱ ክብር ወደ ሀገሩ ሊመለስ እንደሚችል አመላካች ነው። እንደሚታወቀው እአአ ከ1990ዎቹ አጋማሽ አንስቶ ለረጅም ዓመታት የ5ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰን በሁለት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ነው ተይዞ የቆየው። በእርግጥ ሁለት ኬንያዊያን አትሌቶች የክብረወሰን ባለቤቶቹን ኃይሌ ገብረስላሴ እና ቀነኒሳ በቀለን ሰዓት ለማሻሻል ሞክረዋል፤ ይሁንና ከወራት የዘለለ እድሜ ሳይኖራቸው በራሳቸው በኢትዮጵያውያኑ በድጋሚ ተወስደዋል። እአአ ከ2020 አንስቶ ግን የርቀቱ ክብረወሰን በኡጋንዳዊው ጆሽዋ ቺፕቴጊ እጅ ገብቶ ይገኛል። በዚህ ርቀት ተፎካካሪዎች እነዚሁ የምሥራቅ አፍሪካ አትሌቶች መሆናቸውም ክብረወሰኑ ከሌሎች ሀገራት አትሌቶች እንዳይጠበቅ አድርጓል።

የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ የርቀቱ የቀድሞው ክብረወሰን በጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ሄንግሎ ላይ የተመዘገበው ልክ በዕለቱ ከ20 ዓመት በፊት 2004 ላይ ሲሆን፤ ሰአቱም 12:37.35 ነበር። ከዓመታት በኋላም ኡጋንዳዊው አትሌት ጆሽዋ ቺፕቴጊ 12:35.36 በሆነ ሰዓት በማሻሻል ክብረወሰኑን የግሉ አድርጎት ቆይቷል። ከትናንት በስቲያ ምሽት በተደረገው የዳይመንድሊግ ውድድርም ሃጎስ አስደናቂ ብቃት ቢያሳይም 12:36.73 በሆነ ሰዓት በመሮጥ ለጥቂት ክብረወሰኑን ሳይሰብር ቀርቷል። ነገር ግን በርቀቱ ሁለተኛው ፈጣን ሰዓት ሆኖ ሲመዘገብ ሁለት ወር ብቻ ለሚቀረው የፓሪሱ ኦሊምፒክም በርቀቱ ቅድሚያ ተጠባቂ ከሆኑ አትሌቶች መካከል እንዲሰለፍ አድርጎታል።

በ5ሺ ሜትር ርቀት በመሮጥ የሚታወቀው አትሌቱ እአአ 2013ቱ የሞስኮ ዓለም ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ሲያገኝ፤ በቀጣዩ የቤጂንግ ቻምፒዮና ደግሞ የነሐስ ሜዳሊያ አጥልቋል። በ2016ቱ የሪዮ ኦሊምፒክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሀገሩን የወከለው አትሌቱ የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤት እንደነበር ይታወሳል። ተስፈኛው አትሌት ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ተደጋጋሚ ጉዳት በማስተናገዱ ምክንያት ብቃቱን ለማሳየት ባይችልም፤ ባለፈው ዓመት ሪጋ




**ሐጎስ ገብረህይወት ሁለተኛውን የ5ሺ ሜትር ፈጣን ሰዓት አስመዝግቧል፤**

ላይ በተደረገ የጎዳና ላይ ቻምፒዮና የ5ኪሎ ሜትር አሸናፊ በመሆን ወደ አቋሙ መመለሱን አስመስክሮ ነበር። የተያዘውን የውድድር ዓመት ደግሞ በአፍሪካ ጨዋታዎች የጀመረ ሲሆን፤ የ5ሺ ሜትር ቻምፒዮናም ነበር። በዳይመንድ ሊጉ የመጀመሪያ ተሳትፎው ደግሞ የስፖርት ቤተሰቡን ያስደነቀ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል።

ውድድሩን ተከትሎ አትሌቱ ከዓለም አትሌቲክስ ጋር በነበረው ቆይታ «ባስመዘገብኩት ሰዓት እጅግ ደስተኛ ነኝ። ከዚህ ቀደም ኦስሎ ላይ የግሌን ምርጥ ሰዓት ሮጬ ነበር፤ ይሄኛው ግን የተሻለው ነው። በውድድሩ ስፍራ የነበረው የአየር ሁኔታ እና የስፖርት ቤተሰቡ ድጋፍ ጥሩ ነበር። ፈጣኑ ሩጫ ቢፈትነኝም መጨረሻው መልካም ሆኗል። አሁን በፓሪስ ኦሊምፒክ በ10ሺ ሜትር ለመሳተፍ የሚያስችለኝን ጥረት አደርጋለሁ» ሲልም ፍላጎቱን አሳይቷል።

አምና በኦስሎ ዳይመንድ ሊግ አሸናፊ የነበረው ዮሚፍ ቀጄልቻ ድጋሚ ባለድል ባይሆንም በጠንካራ ፉክክር ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ማጠናቀቅ ችሏል። ከሁለት ወር በፊት ስፔን ላይ በ10 ኪሎ ሜትር ውድድር አሸናፊ የነበረው አትሌቱ በሌሎች ውድድሮች ላይ አልታየም። ይኸውም ትኩረቱን በዝግጅት ላይ አድርጎ መቆየቱን የሚያመላክት ሲሆን፤ የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የበላይነት በታየበት ውድድር የራሱን ምርጥ ሰዓት በ12:38:95 በማስመዝገብ ሁለተኛ ሆኖ አጠናቋል።

ኡጋንዳዊው የርቀቱ የቀድሞ የዓለም ቻምፒዮን ጃኮብ ኪፕሊሞ 12:40:96 በሆነ ሰዓት ሶስተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ የርቀቱ የሪከርድ ባለቤትና የኦሊምፒክ ቻምፒዮኑ ጆሹዋ ቺፕቴጌ በ12:51:94 ሰዓት ዘጠነኛ ሆኖ ፈጽሟል። ይህም ከሁለት ወራት በኋላ በሚካሄደው የ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች 2008 የቤጂንግ ኦሊምፒክ የቀነኒሳ ድል በኋላ የወርቅ ሜዳሊያ ተስፋ እንዲጣልባቸው አድርጓል።